የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

# መሠረተ ሃይማኖት

እና

# የካህናት ተልእኮ

ሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ/ም

አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
ቅዱስ ሲኖዶስ
የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ
በትምህርተ አበ ነፍስ (ፓስተራል ኬር) አገልግሎት
ክፍል ተዘጋጀ ።

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው ።

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

## መሠረተ ሃይማኖት ፤

በሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

ተዘጋጀ

www.ethiopianorthodox.org

# ይዘቶች


| ይዘቶች | ገጽ |
|---|---|
| መቅድም | ፱—፲ |
| መግቢያ ፤ | ፲፩—፲፪ |
| ፩. የእግዚአብሔር መኖር (ህልዎት) | ፲፫—፲፯ |
| ሀ/ ስለ እግዚአብሔር መኖር ማስረጃዎች | |
| ፩/ ሥነ ፍጥረት | |
| ፪/ ሥነ ምግባር (ሕሊና) (ሞራል) | |
| ፫/ ታሪክ | |
| ለ/ የእግዚአብሔር ጠባይዓት | |
| ፩/ ዘለዓለማዊነቱ | |
| ፪/ ሁሉን ቻይነቱ | |
| ፫/ ሁሉን ዐዋቂነቱ | |
| ፬/ ምሉዕ በኵለሄነቱ | |
| ፭/ ቅድስናው | |
| ፮/ ጻድቅነቱ | |
| ፯/ ፍቅር መሆኑ | |
| ፪/ ምሥጢረ ሥላሴ | ፲፯—፲፰ |
| ፫/ ሥነ ፍጥረት | ፲፰—፲፱ |
| ፬/ የእግዚአብሔር መግቦት | ፲፱—፳ |
| ፭/ መላእክት | ፳—፳፩ |
| ፮/ ሰይጣናት | ፳፩ |
| ፯/ የሰው ተፈጥሮና አወዳደቁ | ፳፪—፳፬ |


www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

፩/ ተፈጥሮው

፪/ አወዳደቁ

፰/ ምሥጢረ ሥጋዌ . . . . . . ፳፬—፳፭

፱/ የክርስቶስ ሕማም ሞት ፣ ትንሣኤና ዕርገት . . . ፳፮—፳፰

፩/ ሕማሙ

፪/ ሞቱ

፫/ ትንሣኤው

፬/ ዕርገቱ

፲/ ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ . . . ፳፰—፴

፲፩/ ቤተ ክርስቲያን . . . . . . ፴—፴፪

፲፪/ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን . . . . . ፴፪—፵፯

፩/ ምሥጢረ ጥምቀት

፪/ ምሥጢረ ሜሮን

፫/ ምሥጢረ ቊርባን

፬/ ምሥጢረ ክህነት

፭/ ምሥጢረ ንስሐ

፮/ ምሥጢረ ተክሊል

፯/ ምሥጢረ ቀንዲል

፲፫/ ትንሣኤ ሙታን ፣ የክርስቶስ ዳግም ምጽአትና
የመጨረሻው ፍርድ. . . . . . . ፵፰—፶፪

፩/ ትንሣኤ ሙታን

፪/ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት


# መ ቅ ድ ም

በገጠርም ሆነ በከተማ የሚኖሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናት ኅብረተሰቡን በትምህርተ ሃይማኖትና በምግባረ ሠናይ ለማገልገል ለሚያደርጉት ጥረት ለሥራቸው መቃናት ይረዳል ተብሎ ይህ አነስተኛ መጽሐፍ ተዘጋጅቷል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊት ፣ ታሪካዊት ፣ ሐዋርያዊትና ፣ ብሔራዊት እንደመሆኗ በየጊዜው ለሕያው እግዚአብሔር ክብርና ለሰዎች ደኅንነት ፣ እኩልነት ስለሕያዋንና ስለሙታን፣ በምርኮ ስላሉትና መሪር በሆነ አገዛዝ ስለተያዙት ፣ ስለተከፉና ስለተሰደዱ እግዚአብሔር አምላካችን ምሕረቱንና ቸርነቱን እንዲያደርግላቸው፣ ስለዝናመ ምሕረት ፣ እክለ በረከትና ስለመሳሰሉት ዘወትር ትጸልያለች ታስተምራለች ፤ በዚህ ዓለም እግዚአብሔርን ከማመስገን ፣ ሰዎችንም ከመርዳት የበለጠ ቅዱስ ተግባር የለም ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ በሕይወታቸው የተቸገሩትን የተጨቆኑትን ቀርቦ የሚያይና የሚመለከት አበ ነፍስ አገልግሎት ሰጭ ክፍል አለው ፤ በዚህ ክፍል አማካኝነት መምሪያው ተገቢውን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ይሰጣል ፤ ትምህርተ አበ ነፍስ በሌላ አነጋገር ኖላዊ (ፓስተራልኬር) ተብሎ ይጠራል ፤ ኖላዊ (ፓስተር) ማለት ጠባቂ ነው ፤ የተገኘውም ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው ፤ መዝ ፡ ፳፪ ፡ ፩—፯ ሕዝቅ ፡ ፴፬ ፡ ፩—፲ በመጽሐፍ ቅዱስ ቤተ እሥራኤል የእግዚአብሔር መንጋ ሲባሉ ካህናትና ነቢያተ እግዚአብሔርም ጠባቂዎች ተብለዋል ፤ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መልካም እረኛ እኔ ነኝ ይላል ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፩—፲፰ ። እንዲሁም ጴጥሮስን በጎቼን ጠብቅ አለው ዮሐ ፡ ፳፩፡ ፲፭—፲፯ ።

ጴጥሮስም ይህ ቃል ትዝ እያለው በመልእክቱ ውስጥ ቤተ ክርስቲያንን መንጋ ቀሳውስትን እረኞች አድርጎ ይናገራል፤ ፩ኛ ጴጥ ፭፡፩—፬ ። መጠበቅ ማለት መመገብ ፣ መምራት ፣ መገሠጽ ፣ ከአውሬ መጠበቅ ማለት ነው ፤ ይህ ሁሉ የአበ ነፍስ ሥራ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ መምሪያው «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ ሃይማኖትና የካህናት ተልእኮ» በሚል ርእስ ይህን መጽሐፍ ያዘጋጀበት ምክንያት ፣

፩ኛ/ በመጀመሪያ ደረጃ ካህናቱ ስለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ጠንቅቀው በማወቅ ለሐዋርያነት ሥራቸው እንዲረዳቸው ፣ ሐዋርያት ከሦስት ዓመታት በላይ የመምህራቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርቱንና ተአምራቱን ካዩና ከተመለከቱ እንዲሁም ከተረዱ በኋላ ነው ፤ ሒዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ በአብ ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው የተባሉ (ማቴ ፡ ፳፰ ፡ ፲፱ ) ።

፪ኛ/ በአምላካዊ ትእዛዝ መሠረት ካህናት ለሐዋርያዊ ተልእኮ ለስብከተ ወንጌል ተግባር እንዲፋጠኑና መንፈሳዊ ግዴታቸውንም በሚገባ እንዲወጡ ይረዳቸው ዘንድ መምሪያው ይህን መጽሐፍ በማዘጋጀት ለአገልግሎት አቅርቧል ።



## መ ግ ቢ ያ

ሃይማኖት እግዚአብሔር ለሰው ልጆች በመግለጡ የተገኘ ነው ፤ ሰው ምንም እንኳ የማምለክና የማመን ጠባይዕ ቢኖረውም እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ ራሱን ባይገልጥለት ኖሮ የቀናውን የሃይማኖት ጎዳና እንደማያገኝ የታወቀ ነው ፤ እግዚአብሔር ሰውን በመልኩና በምሳሌው መፍጠሩ እንዲያመልከውና እንዲያምነው እንዲያመሰግነውም ስለሆነ ይህ ለሰው የተደረገ ልዩ አምላካዊ ስጦታ ነው ፤ በመሆኑም ሃይማኖት የአምላክ ስጦታ መሆኑን ያረጋግጣል ።

ሰው በኃጢአት ከወደቀ በኋላም እግዚአብሔር ተገልጦ ከውድቀቱ እንደሚያነሣው ተስፋውን ነገረው ፤ በኋላም በየጊዜው በራእይና በሕልም በተአምራትም በተለያየ መልክ ተገልጦ ሰዎች ወደ እርሱ የሚቀርቡበትን መንገድ አሳያቸው በመጨረሻም የባሕርይ ልጁ በሥጋ ተገልጦ «ወደ እኔ ኑ በእኔ እመኑ ፤ በአባቴም እመኑ» በማለት በአስተማራቸው ጊዜ ሃይማኖትን ገልጦላቸዋል ፤ (ማቴ ፡ ፲፩፡ ፳፰) ዮሐ ፡ ፲፬ ፡ ፩ ፤ )ስለዚህ ሃይማኖት በሥነ ፍጥረት በነቢያት በመጻሕፍት ኋላም በአንድ ልጁ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሆነው የእግዚአብሔር መገለጥ መሆኑን ማስተዋል ይቻላል ።

የትምህርተ ሃይማኖት ምንጮች ሁለት ናቸው ፤ እነሱም ቅዱስ መጽሐፍና ትውፊት ናቸው ፤ እግዚአብሔር ለሰዎች የተናጋሪውና ያደረገው ሁሉ በእነዚህ በሁለቱ ምንጮች ይገኛል ።

እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ቀኖና ቅዱስ መጽሐፍ ፹፩ መጻሕፍትን ይዞአል መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፈና ምንም ስሕተት የሌለበት የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ቤተ ክርስቲያናችን ታምናለች ። ፪፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፲፮—፲፯ ፤ ፪፡ ጴጥ፡ ፩ ፡ ፳—፳፩ ።

ትውፊት ማለትም ጌታም ሐዋርያትም ተናግረውት በመጽሐፍ ያልተጻፈ ነገር ግን ከቃል ወደ ቃል ሲያያዝ የመጣ ማለት ነው ፤ የቃሉ ትክክለኛ ትርጉም ቅብብል ማለት ነው ፤ (ተውፈየ ተቀበለ ካለው የተገኘ ቃል ነው) ።



www.ethiopianorthodox.org

ጌታችን ያስተማረው ትምህርትና ያደረገው ተአምራት ሁሉ በሙሉ
በሐዲስ ኪዳን አለመመዝገቡ ተገልጦአል ፤ ዮሐ ፡ ፳፩ ፡ ፳፭ ፤ ስለዚህም
ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላል « አሁንም ወንድሞቼ ሆይ ጸንታችሁ ቁሙ ፤
በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን የተማራችሁትን ትው
ፊት ያዙ» ፪፡ ተሰ፡ ፪፡ ፲፭ ፤ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሊቃውንትም በጉ
ባኤ የወሰኑት ትምህርተ ሃይማኖት በቅዱስ መጽሐፍ ላይ የተመ
ሠረተ ቢሆንም አብዛኛው በቃል ተጠብቆ ከቆየው የተወረሰ ነው ።
ሐዲስ ኪዳን ቅሉ የተጻፈ ጌታን ከሰሙት ቅዱሳን ሰዎች አፍ እየተነገረ
ነው ፤ ስለዚህም ቅዱስ መጽሐፍና ትውፊት ለትምህርተ ሃይማኖታችን
እውነተኛ ምንጮች ናቸው ፤ ከእነዚህ ከሁለቱ ምንጮች የተቀዳ ትም
ህርተ ሃይማኖትም አይለወጥም፡አይሻሻልም ፤ እንዳለ ተጠብቆ ይኖ
ራል እንጂ ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማ
ኖት በእነዚህ በሁለቱ መሠረቶች ላይ የተገነባ ነው ፤ ከዚህም ጋር በ፫
ጉባኤያት በኒቅያ (፫፻፳፭) ፤ በቍስጥንጥንያና (፫፻፹፩) ፤ በኤፌሶን (፬፻፴፩)
የተወሰነውን የሃይማኖት ቀኖና ቤተ ክርስቲያናችን ትቀበላለች ።

የቤተ ክርስቲያናችን መሠረተ እምነት በተለያየ ርእስ በተለይም
«አምስቱ አዕማደ ምሥጢር» በሚል ርእስ በየጊዜው በልዩ ልዩ የአቀ
ራረብ ዘዴ በሊቃውንት መምህራን እየተዘጋጀ ቀርቦአል ፤ ይህም
«የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ ሃይማኖት»
በሚል ስያሜ የቀረበው ዝግጅት ከይዘቱና ከአቀራረብ ዘዴው በቀር
« በከመ መሀሩነ አለ ቀደሙነ የቀደሙን አባቶቻችን እንደአስተማሩን »
ትምህርተ ሃይማኖት ነው ፤ በቀደሙን አባቶቻችን መምህራን መሠረት
ላይ ታንጸናልና ከእነርሱ የሰማነውን እናስተምራለን ።



## ፩. የእግዚአብሔር መኖር (ህልዎት)

የማይታይና የማይመረመር ሁሉን ማድረግ የሚችል ሁሉን የፈጠረ
መጀመሪያ ያልነበረው መጨረሻም የማይኖረው ለዘለዓለም የሚኖር አንድ
አምላክ መኖሩን ማመን ለሰው ልጆች መሠረታዊ ነገር ነው ።

የሰው ልጅ ስለእግዚአብሔር ያለው ዕውቀት ሁለት ዓይነት ነው ፤

፩ኛ. ሰው በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ ስለተፈጠረ በተፈጥሮ የተሰ
ጠው ዕውቀት እያደገ ሲሄድ ፈጣሪውን ተመራምሮ የማወቅ ችሎታ
አለው ።

፪ኛ. ሰው ፈጣሪውን ለማወቅ በተፈጥሮ ያገኘው ዕውቀት ቢኖረውም
በተጨማሪ በእግዚአብሔር ልዩ መገለጥ ፈጣሪውን ያውቃል ፤
ይሁን እንጂ ሰው ስለእግዚአብሔር ያለው ዕውቀት የተወሰነ ነው ፤
ምክንያቱም እግዚአብሔር የማይመዘንና የማይለካ በመሣሪያም
የማይመረመር ስለሆነ ነው ፤ የሰውም ዕውቀት እጅግ የተወ
ሰነ በመሆኑ ነው ፤ ሰው በዓይኑ አይቶና በእጁ ዳስሶ በመሣሪያም
መርምሮ ማረጋገጥ የሚችለው የተፈጠረውን ግዙፍ ነገር ብቻ
ነው ።

### ሀ. ስለእግዚአብሔር መኖር ማስረጃዎች ፤

እግዚአብሔር በተለያዩ መንገዶች ራሱን ባይገልጥ ኖሮ ሃይማኖት
ሊኖር ባልቻለም ነበር ፤ እግዚአብሔር ራሱን ለሰው ልጆች ባያሳውቅ ሰው
ስለ እግዚአብሔር የሚያውቀው አንዳችም ነገር አይኖርም ነበር ፤ በመ
ሆኑም ሰው ስለ ፈጣሪው መጠነኛ መረጃ ያገኘባቸው ከራሱ ከእግዚአብ
ሔር ለሰው የተሰጡ ነገሮች የሚከተሉት ናቸው ።

#### ፩. ሥነ ፍጥረት ፤

የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን ህልውና (መኖር) ለመረዳት ምር
ምር ካደረገባቸው ነገሮች ዋናው ሥነ ፍጥረት ነው ፤ ማንኛውም ነገር
ያለ ምክንያት አይገኝም፤አንቀሳቃሽ የሌለው ተንቀሳቃሽ የለም ፤ ለምሳሌ
ያለ ጠራቢ ወንበር ያለ ሸማኔ ሸማ ያለ አናጢ ቤት ሌላው ሥራ ሁሉ ያለ
ሠራተኛ ሊገኝ አይችልም ፤ በዚህም መሠረት ይህ እጅግ ውብና ድንቅ



www.ethiopianorthodox.org

የሆነው ዓለም በውስጡም ያለው ሥነ ፍጥረት ሁሉ ራሱ በራሱ አልተፈ
ጠረም ፤ በአጋጣሚ ወይም በድንገት የተገኘ አይደለም ፤ ከሁሉ በላይ
ዐዋቂና ጠቢብ በሆነው በፈጣሪ እግዚአብሔር ተፈጥሮአል ፤ ከመጨረ
ሻዋ ዝቅተኛ የሥነ ፍጥረት አካል ጀምሮ እስከ ታላቁ ፍጥረት ድረስ
ያለው ሁሉ ወደ እግዚአብሔር መኖር ይመራል ፤ ስለዚህም ዳዊት በመዝ
ሙሩ እንዲህ ይላል «ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ ጠፈርም
የእጁን ሥራ ይመሰክራል» ፤ (መዝ ፡ ፲፰ ፡ ፩ ፤) ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎ
ስም እግዚአብሔር በሥነ ፍጥረቱ በኩል ለፍጥረቱ መታወቁን ሲያስ
ረዳ የሚከተለውን ይናገራል ፤ «የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘለዓ
ለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ
ግልጥ ሆኖ ይታያል» (ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፳) ፤ እንግዲህ ይህ የማይለወጥና
የማይዛባ የሥነ ፍጥረት ሥርዐት ያለው ዓለም ለእግዚአብሔር መኖር
ታላቅ ምስክር ነው ።

## ፪/ ሥነ ምግባር (ሕሊና) ፤ (ሞራል)

ማንም ሰው በውስጡ አንድ መንፈሳዊ ሕግ እንዳለው ያውቃል ፤
እርሱም ሕሊና ነው ፤ ሰው በተፈጥሮ ባገኘው ሥነ ምግባራዊ ዕውቀት
ወይም በሕሊናው አነሣሽነት መልካም ይሠራል ፤ ከክፉም ይርቃል ተላ
ልፎ ክፉ ቢሠራም እንኳ ያው ሕሊናው እንዲጸጸት ያስገድደዋል ፤ እንደ
ዚሁም ክፉ የሠራ እንደሚቀጣ መልካም የሠራም ዋጋ እንደሚያገኝ
ያውቅ ዘንድ ሰውን ሕሊናው ይወቅሰዋል ፤ ይህ የሚያመለክተው ለጻ
ድቁም ሆነ ለክፉው እንደ ሥራው ዋጋ የሚከፍልና ሳያዳላ በትክክል የሚ
ፈርድ ከሁሉ በላይ የሆነ አንድ አምላክ መኖሩን ነው ፤ ይህንም ለማስረ
ዳት ቅዱስ ጳውሎስ የሚከተለውን ጽፎአል ፤ «ሕግ የሌላቸው አሕዛብ
ከባሕርያቸው የሕግን ትእዛዝ ሲያደርጉ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው እንኳ
ለራሳቸው ሕግ ናቸውና ፤ እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው አሳባ
ቸውም እርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸውም የተጻፈ
ውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ ፤» (ሮሜ ፡ ፪ ፡ ፲፬ - ፲፭) ።

## ፫/ ታሪክ ፤

የአምልኮቱ ሥርዓት ይለያይ እንጂ በዚህ ዓለም ላይ ያለ አምላክ
የኖረ ሕዝብ እንደሌለ ታሪክ ያስረዳል ፤ ሰው ፈጣሪውን ለመፈለግ ወደ
ላይ ከመመልከት ያቋረጠበት ክፍለ ዘመን ፈጽሞ የለም ፤ ከጥንት ጀምሮ



እስካለንበት ዘመን ያሉት ሕዝቦች ሁሉ አንድ አምላክ ወይም ብዙዎች
አማልክትን ማምለካቸው አንድ ፈጣሪ መኖሩን በትክክል ያመለክታል ፤
ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የዓለም ሕዝብ ሁሉ በተመሳሳይም ሆነ በተለያየ
መንገድ አንድ ፈጣሪ አለ ብሎ ማመኑ ለሕሊናም ለአእምሮም ተስማሚ
ሆኖ ተገኝቶአል ፤ በእርግጥ አምላክ ባይኖር ኖሮ የሰውን አእምሮ
ወደ አምልኮት የሚስበው ጠባይ እንደማይኖር የታወቀ ነው ።

ከዚህም ሌላ እግዚአብሔር አስቀድሞ በነቢያት በመ ጨረሻም በአ
ንድ የባሕርይ ልጁ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ገልጦአል ፤
ይህንም በዕብራውያን መልእክት ፩፡ ፩፡ በተጻፈው ቃል መረዳት እንችላ
ለን ፤ «ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጐዳና ለአባ
ቶቻችን በነቢያት ተናግሮ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን
በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን» ይህም የመ
ጨረሻው የእግዚአብሔር መገለጥና መታወቅ ነው ፤ ራሱ እግዚአብሔር
ወልድ «እኔን ያየ አብን አየ» በማለት አረጋግጦአልና ። (ዮሐ ፡ ፲፬፡ ፱)

## ለ. የእግዚአብሔር ጠባይዓት

እግዚአብሔር ረቂቅ አምላክ ነው ሰውም እግዚአብሔርን ለማወቅ
ያለው ችሎታ እጅግ የተወሰነ ነው ፤ በመሆኑም የእግዚአብሔርን ባሕ
ርይ ወይም ጠባይ ለመመርመር አይችልም ፤ በሥነ ፍጥረት በታሪክና
በሕሊና (ሥነ ምግባር) በኩል በተገኘው የመመራመር ዕውቀት እግዚ
አብሔርን ፈጽሞ ለመረዳት አይበቃም «በዚህ ዓለም ሳለን እግዚአብሔርን
የምናውቀው በከፊል ነው፤በወዲያኛው ዓለም ግን ፊት ለፊት እናየዋለን»
ይላል ቅዱስ ጳውሎስ (፩ ቆሮ ፡ ፲፫ ፡ ፲፪) ።

እግዚአብሔር መንፈስ በመሆኑ ባሕርዩን ለመመርመር ባንችልም
የቀደሙን አባቶች እንዳስተማሩን ስለ እግዚአብሔር ጠባይዕ ይገልጣሉ
ከተባሉት ነገሮች አንዳንዶችን ቀጥሎ እንመለከታለን ።

### ፩. እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ነው

እግዚአብሔር ከጊዜ ውጭ ነው ፤ ማለት ጊዜ ሳይኖር ነበር የጊዜ
ፈጣሪ እርሱ ነውና ዘመናትንም አሳልፎ ለዘለዓለም ይኖራል ፤ የእግዚአብ
ሔርን ዘለዓለማዊነት ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ያስረዳሉ «ተራሮች ሳይወ
ለዱ ምድርም ዓለምም ሳይሠሩ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ አንተ
ነህ» (መዝ ፡ ፹፱፡ ፪ ፤ ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፲፯ ፤) እግዚአብሔር ራሱ በራሱ



www.ethiopianorthodox.org

የነበረና ያለ የሚኖርም ስለሆነ ጊዜ አይወስነውም ፤ ጊዜ አይለውጠውም ፤ በጊዜ የሚወሰን ለመገኘቱ ምክንያት ያለው ብቻ ነው ፤ እግዚአብሔር ግን አስገኝ ስለሌለው ጊዜ አይወስነውም።

፪. ሁሉን ቻይ ነው

እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው ሁሉን ነገር ማድረግ ይችላል ፤ የሚሳነው ነገር የለም ፤ በወንጌል እንደተጻፈ በሰዎች ዘንድ የማይቻሉ ነገሮች በእግዚአብሔር ዘንድ ይቻላሉ (ሉቃ ፡ ፲፰ ፡ ፳፯ ፡ ዘፍ ፡ ፲፯ ፡ ፩ ። ፲፰ ፡ ፲፬) ።

፫. ሁሉን ዐዋቂ ነው

እግዚአብሔር ሁሉን ያውቃል ፤ ከእርሱ የተሰወረ የለም ። ያለፈውን ያሁኑንና የሚመጣውን ያልተነገሩ ሐሳቦችን ቃላትንና ተግባራትን ከመሆናቸው አስቀድሞ በአንድ ጊዜ ያውቃል ፤ ይህንንም ዳዊት «አንተ መቀመጤንና መነሣቴን ዐውቀህ አሳቤን ሁሉ ከሩቅ አስተዋልህ - - - መንገደቼን ሁሉቀድመህዐወቅህ» በማለት ያስረዳል ። (መዝ፡፩፻፴፰፡፩-፬)

፬. በሁሉ ሙሉነው

እግዚአብሔር በዓለም ሁሉ ምሉዕ ነው ፤ እዚህ አለ ፡ እዚያ የለም ፡ ወይም እዚያ አለ እዚህ የለም አይባልም ፤ ስለክብሩና ስለልዕልናው በሰማይ ይኖራል ፤ ወይም በማይመረመር ብርሃን ውስጥ ይቀመጣል በ.ባልም እግዚአብሔር በቦታ አይወሰንም እርሱ ከዓለም በላይ ፡ በዓለም ውስጥ ፡ ከዓለምም ውጭ ነው ፤ ቅዱሳት መጻሕፍትም «ወደ ሰማይ ብወጣ ፡ አንተ በዚያ አለህ ፡ ወደ ጥልቁም ብወርድ አንተ በዚያ አለህ» (መዝ ፡ ፩፻፴፰ ፡ ፰ —፲) በማለት ምሉዕ በኩልሄነቱን ያስረዳሉ ።

፭. ቅዱስ ነው

እግዚአብሔር ቅዱስ ነው ፤ ከክፉና ከርኩስ ነገር ጋር ምንም ግንኙነት የለውም ፤ ፍጹም ንጹሕ ልዩና ክቡር ነው ፤ እርሱ ቅዱስ እንደሆነ ፍጥረቱም ቅዱስ እንዲሆን ይፈልጋል ፤ «እኔ ቅዱስ እንደሆንሁ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ» ይላል ። (ዘሌዋ ፡ ፲፱ ፡ ፪)



፮. ጻድቅ ነው

እግዚአብሔር ጻድቅ ነው ማለት እውነተኛ ነው ። የሥነ ምግባር ሕግ እንዲጠበቅ ይወዳል ፤ በጽድቅ ይፈርዳል ፤ ለማንም አያዳላም ፤ ፍርዱ እውነትና ተገቢ ነው ። (ራእ ፡ ፲፮ ፡ ፯)

፯. ፍቅር ነው

«እግዚአብሔር ፍቅር ነው» (፩ ዮሐ፡ ፬ ፡ ፰ ፤) እግዚአብሔር ማንኛውንም መልካም ነገር ለፍጥረቱ ሁሉ ያለንፍገት በልግስና ስለሚሰጥ ፍቅሩ ይገለጣል ፤ በተለይም ለሰው ልጅ ያደረገው ፍቅሩ ወሰን የለውም ፤ «እግዚአብሔር አንድ ልጁን ለሁሉ ቤዛ አድርጎ እስከመስጠት ድረስ ይህን ዓለም ወድዶታል» (ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፲፮ ፤)ስለዚህ ፍቅሩ ከሌሎች ጠባይዓቱ የበለጠ ነው ።

## ፪. ምሥጢረ ሥላሴ ፤

እግዚአብሔር በባሕርይ በመለኮት በፈቃድ በሥልጣን አንድ ነው ፤ ግን በስም በአካልና በግብር ሦስትነት አለው ፤ የስም ሦስትነት አብ ፡ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ነው ።

የአካል ሦስትነት ፡— አብ ፍጹም አካል አለው ፤ ወልድ ፍጹም አካል አለው እንደዚሁም መንፈስ ቅዱስ ፍጹም አካል አለው ።

የግብር ሦስትነት ፡— አብ ወላዲ አስራጺ ነው ፤ ወልድ ተወላዲ ነው ፤ መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ ነው ፤ ስምና ግብር አይፋለሱም ፤ አብ ፡ ወልድ ወይም መንፈስ ቅዱስ አይባልም ወልድም አብ ወይም መንፈስ ቅዱስ አይባልም ፤ መንፈስ ቅዱስም አብ ወይም ወልድ አይባልም ፤ እንደዚሁም አብ ተወላዲ ሠራጺ አይባልም ፤ ወልድም ወላዲ አሥራጺና ሠራጺ አይባልም ፤ መንፈስ ቅዱስ ወላዲ አሥራጺና ተወላዲም አይባልም ።

ምሥጢረ ሥላሴ በብሉይ ኪዳን ግልጥ ባይሆንም መሠረተ ሐሳቡ በአያሌ ቦታዎች ተጠቅሶአል ።

«እግዚአብሔርም አለ ሰውን በምሳሌያችን ፡ በመልካችን እንፍጠር» (ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፳፮—፳፯ ፤) «እግዚአብሔር አምላክም አለ እነሆ አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ»(ዘፍ ፡ ፫ ፡ ፳፪)«ኑ እንውረድ ቋንቋቸውንም ከዚያ እንደባልቀው»(ዘፍ ፡ ፲፩ ፡ ፯)እንደዚሁም (ኢሳ ፡ ፮ ፡ ፰ ። ሆሴዕ፡ ፲፪ ፡ ፬፡)



www.ethiopianorthodox.org

ላይ ያሉት ጥቅሶች ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ናቸው ፤ በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ «እኛ» የሚሉት ቃላት ሦስትነትን ያመለክታሉ ፤ ከዚህም ሌላ መዝ፡ ፴፫ ፡ ፮ና የመሳሰሉት ጥቅሶች ለሦስትነቱ ማረስጃዎች እንደሆኑ በሊቃውንት ተጠቅሰዋል ።

በሐዲስ ኪዳን ግን ምሥጢረ ሥላሴ በሰፊው ተብራርቶ ተነግሮአል ፤ (ማቴ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ፡ ፳፰ ፡ ፲፱ ፤ ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፲፫ ፡ ፲፫ ፤) ሊቃውንትም ይህን የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃል መሠረት በማድረግ ምሥጢረ ሥላሴን አሟልተው ፡ አስፍተውና አጉልተው ተርጕመዋል ።

በሦስቱ አካላት መቀዳደምና መበላለጥ የለም ። አብ አባትና አሥራጺ ስለተባለ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ አይበልጥም ፤ አይቀድምም ፤ ወልድም ተወላዲ ስለተባለ ከአብ አያንስም ፡ ከመንፈስ ቅዱስም አይበልጥም አያንስም ፤ መንፈስ ቅዱስም ሠራጺ ስለተባለ ከአብና ከወልድ አያንስም ፤ የሦስቱ አካላት አንዋዋር አንድ ነውና ።

የምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት ለሰው አእምሮ የረቀቀ በግልጽ ማስረጃም ሊረዳ የማይችል በመሆኑ ምሥጢር ተብሎአል ፤ በእርግጥ ልብ ፡ ቃልና እስትንፋስ ፀሐይና እሳት ለእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት ምሳሌዎች ሆነው ተነግረዋል ፤ ነገር ግን በእነዚህም የሚሰጠው ማብራሪያ የረቀቀ ነው ፤ ስለሆነም ትምህርተ ሥላሴ ምን ጊዜም ምሥጢር ነው ።

## ፫. ሥነ ፍጥረት ፤

ይህ የሚታየው ዓለምና በውስጡ ያለው ሁሉ በእግዚአብሔር የተፈጠረ ነው ፤ ከዚህ ከሚታየው ዓለም ውጭም ሌላ የማይታይ ረቂቅ ዓለም በውስጡም ያሉት ረቂቃን ፍጥረታት በእግዚአብሔር ተፈጥረዋል ፤ እግዚአብሔር ግዙፉንና ረቂቁን ዓለማት የፈጠረ አስቀድሞ ከነበረ ግብር ሳይሆን እምኀበ አልቦ ነው ፤ ሥነ ፍጥረት እምኀበ አልቦ መፈጠሩን ቅዱሳት መጻሕፍት በሰፊው አብራርተው ያስረዳሉ ፤ «ልጄ ሆይ ሰማይና ምድርን በውስጣቸውም ያለውን ሁሉ ትመለከት ዘንድ እግዚአብሔርም ከሌሉበት አምጥቶ እንደፈጠራቸው ታስተውል ዘንድ እለምንሃለሁ» (፪ ፡ መቃብያን ፡ ፯ ፡ ፳፰) ከዚህም ጋር መዝ ፡ ፴፫ ፡ ፱፤ የሐዋ ፡ ፲፯ ፡ ፳፬ ፤ ሮሜ ፡ ፬ ፡ ፲፯ ፤ ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፫ ፤ ጥበብ ፲፩ ፡ ፲፯ ፤ የፍጥረትን እምኀበ አልቦ መፈጠር ያስረዳሉ ።

ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ ከራሱ ከእግዚአብሔር በቀር አንዳችም ነገር አልነበረም ፤ ራሱ እግዚአብሔር በራሱ ብቻ ይኖር ነበር ፤ ፈጣሪ



ማለት ቅሉ አስቀድሞ በምንም ዓይነትና ቅርጽ ሕልውና ያልነበረውን ነገር ወደ መኖር ያመጣ ቅርጽና ዓይነትም ሰጥቶ የገለጠ ማለት ነው ፤ እግዚአብሔር ፍጥረትን መፍጠሩ በባሕርዩ ጉድለት ኖሮበት የሚያስፈልገው ሆኖ አይደለም ፤ እግዚአብሔር ራሱ በራሱ ለመኖር የሚችል ስለሆነ ፍጹም ነው ፤ በመሆኑም ለሕልውናው ሌላ ድጋፍ አያስፈልገውም።

ይሁን እንጂ ፍጥረታት ዓላማ አላቸው ፤ ይኸውም እግዚአብሔርን ማመስገን ነው ፤ መላእክትና ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ እንስሳትና ሌሎችም ሕይወት የሌላቸው ፍጥረቶች ሁሉ እግዚአብሔርን ለማመስገን ተፈጥረዋል ፤ (መዝ ፡ ፩፻፵፰ ፡ ፩—፯) በተለይም ሰው ክብሩን ለመውረስ የተፈጠረ ነው ፤ በጠቅላላ ሥነ ፍጥረት ለእግዚአብሔር ሀልውና ምስክር ከመሆኑም በላይ ለሰው ልጅም አገልግሎት እንዲውል ተፈጥሮአል ።

ፍጥረት ሁሉ በ፮ ቀናት ተፈጥሮ መከናወኑን ቅዱስ መጽሐፍ ይናገራል፤ ነገር ግን አንዳንድ ሊቃውንት ይህ ስድስት ቀን ረዥም ዘመንን እንጂ ቀናትን እንደማያመለክት ይናገራሉ ፤ ይሁን እንጂ በኦሪት ዘፍጥረት ፩ ፡ ፭፡ ላይ «ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ አንድ ቀን»ተብሎ ስለተጻፈ ፍጥረት የተፈጠረበት ጊዜ በቀናት እንጂ በረዥም ዘመናት አይቆጠርም ፤ ስድስት ቀን የተባለው በዘመን ከተተረጐመ ፍጥረት በማዝገም ለውጥ (ኢቮልዩሽን ) አሁን ካለበት ደረጃ ደረሰ ወደሚለው ፍልስፍና ይመራል ፤ ስለዚህ ፍጥረት በስድስት ቀናት ውስጥ ተፈጥሮአል የሚለው ሐሳብ የጸና ነው (ዘጸአ ፡ ፳ ፡ ፱—፲፩ ፤ በየቀኑም የተፈጠሩት ፍጥረታት የተለያዩ ናቸው ፤ በመጀመሪያው ቀን ፰ ፡ በሁለተኛው ቀን ፩ ፤ በሦስተኛው ቀን ፬፮፡ በአራተኛው ቀን ፫ ፡ በአምስተኛው ቀን ፫ ፡ በስድስተኛው ቀን ፬ ፍጥረታት ተፈጥረዋል ፤ በድምሩ ፳፪ ይሆናሉ (ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፩—፴፩) ።

## ፬. የእግዚአብሔር መግቦት

እግዚአብሔር ይህን ዓለም ከፈጠረ በኋላ አልተለየውም ፤ መመሪያ ሕግ በመስጠት ከዓለሙ ርቆ የሚኖር አይደለም ፤ የፈጠረውን ፍጥረት ይመራል ፤ ያስተዳድራል ፤ ዓለም ራሱ በራሱ የተገኘ ሳይሆን በእግዚአብሔር የተፈጠረ እንደ መሆኑ ሁልጊዜ የእግዚአብሔር ጥበቃና ርዳታ ያስፈልገዋል ።

ዓለም በእግዚአብሔር ተጠብቆ እንደሚኖር ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚከተለው ያስረዳሉ ፤ «በእርሱ ሕያዋን ነንና እንንቀሳቀሳለን ፡ በእርሱም እንኖራለን»(የሐዋ ፡ ፲፯ ፡ ፳፰ ፤) ስለዚህ እግዚአብሔር የፈጠረውን



www.ethiopianorthodox.org

ዓለም ቸል አይለውም ሁል ጊዜ ይመለከተዋል ፤ ይጠብቀዋል ፤ መጠበ ቅም ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ፍጡር ወደ ተፈጠረበት ዓላማ እንዲደርስ ይመራዋል ፤ ይህም የሰውን ነፃ ፈቃድ አይቃወምም ።

## ፫. መላእክት

ከዚህ በፊት እንደገለጥነው እግዚአብሔር የሚታይና የማይታይ ሁለት ዓለማትን ፈጥሯል ፤ በሚታየው በግዙፉ ዓለም በተፈጥሮው ነፃ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ሲኖር በማይታየው በረቂቁ ዓለም ደግሞ እንደ ሰው ሙሉ ነፃ ፈቃድ ያላቸው መንፈሳውያን (ረቂቃን) መላእክት ይኖራሉ ይህንም መረዳት የተቻለው በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ መላእክት በራ እይ መገለጣቸው በታወቀ ጊዜ ነው ፤ መላእክት ከግብር (ማቴሪያል) የተፈጠሩ አይደሉም ፤ ነገር ግን በመዝሙረ ዳዊት ፩፻፫ ፡ ፬ «መላእክቱን መናፍስት ፥ አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል የሚያደርግ እርሱ ነው» የሚለውን በመመልከት ተፈጥሮአቸው ከእሳትና ከነፋስ ነው የሚሉ አሉ ፤ ይህንም የኢትዮጵያው መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ ፲፫ ፡ ፲፩ ሲያስረዳ እንዲህ ይላል «ከእሳትና ከነፋስ የፈጠራቸው እርሱ እንደሆነ ስላወቁ መላእክት በትሑት ልቡና ፈጣሪያቸውን ያመሰግናሉ ፤ » መላእክት መቼ እንደተፈጠሩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተመ ዘገበው የሥነ ፍጥረት ታሪክ ውስጥ አልተጠቀሰም ፤ ይሁን እንጂ በመ ጀመሪያው ቀን እንደተፈጠሩ በቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት ይታመ ናል ፤ መላእክት የማይሞቱ ሕያዋን ናቸው(ሉቃ ፡ ፳ ፡ ፴፮ ) - መላእክት ጾታ የለሽ ናቸው ፤(ማር ፡ ፲፪ ፡ ፳፭ ፤) መላእክት በፍጥረታቸው ረቂቃን መልካቸውም ይህን ይመስላል ሊባል የማይቻል ሲሆን ሥዕላቸው በምል ክት ይገለጣል ፤ ሲገለጡም አንዳንድ ጊዜ በሰው መልክ ይታያሉ ፤ ባለ ክንፍ፡ክንፍ የሌላቸውም ሆነው ይታያሉ (ማር ፡ ፲፮ ፡ ፭፡ ሉቃ ፳፬ ፡ ፬ ፡ ኢሳ ፮ ፡ ፪ ፤ ሕዝ ፡ ፩ ፡ ፮ ፤ ዳን ፡ ፯ ፡ ፳፩ ፤)የመላእክት ቁጥር የማይወሰን እጅግ ብዙ ሲሆን በስም የሚታወቁ ጥቂቶች ናቸው ፤ ሚካኤልና ገብር ኤል በብሉይና በሐዲስ ተጠቅሰዋል፤(ዳን ፱ ፡ ፲፪ ፡ ፲፪ ። ፩ ፡ ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፲፱፡ ይሁዳ ፱ ፤) ከእነዚህም ሌላ ሩፋኤል ዑራኤል ራጉኤል ፋኑኤል በጦቢትና በሄኖክ መጻሕፍት ተጠቅሰዋል ።

### ግብራቸው (ሥራቸው)

መላእክት ስማቸው እንደሚያመለክተው ሥራቸው ተልእኮ ነው ፤ ከእግዚአብሔር ወደ ሰዎች ለምሕረትም ለመዓትም ይላካሉ (ሉቃ ፡ ፩ ፡



፲፱—፳፯) ባለማቋረጥ እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ ፤(መዝ ፩፻፴፫ ፡ ፱ ዳን ፡ ፫፡ ፺፰) ድኅነት የሚገባቸው የሰው ልጆችን ሁሉ ይጠብቃሉ፤ (ዕብ፡ ፩ ፡ ፲፬ ፤ መዝ ፡ ፺ ፡ ፲፩፤) ክፉዎችን ይቃወማሉ (ራዕ ፡ ፲፪ ፡ ፯፤)የቅዱሳንን ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ያደርሳሉ(ራእ ፡ ፰ ፡ ፫—፬ ፤)የምእመናንን ነፍ ሳት ወደ ዕረፍት ይወስዳሉ፤ (ሉቃ ፡ ፲፮ ፡ ፳፪፤) የእግዚአብሔርን አገልጋ ዮች በማናቸውም ችግራቸው ጊዜ ይረዳሉ (የሐዋ፡ ፭ ፡ ፲፱ ፤ ፲፪፡ ፯ ፤) ለእያንዳንዱ ሰው ጠባቂ መልአክ ሆነው ይጠብቃሉ ፤ ሰው ክፉም ሆነ ደግ ቢሠራ ይመሰክራሉ(ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፲፤) በፍርድ ቀን ከጌታ ጋር ይመጣሉ፤ ያን ጊዜም አገልግሎት ይሰጣሉ (ማቴ፡ ፳፭ ፡ ፫ ፤ ፩ ፡ ተሰ ፡ ፬፡ ፲፮ ፤) በጠቅላላ መላእክት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል መልእክተኞች መሆናቸው በቅዱሳት መጻሕፍት የታወቀ ነው ።

## ፬. ሰይጣናት

እግዚአብሔር የፈጠረው ፍጥረት ሁሉ መልካም እንደሆነ በዘፍ ጥረት እንረዳለን ፤ ነገር ግን መላእክት ሁላቸው መልካም ተፈጥሮታ ቸውን አልጠበቁም ፤ ከእነርሱ አንዱ ዲያብሎስ በነፃ ፈቃዱ ወደ ክፋት አዘንብሏል ፤ ዲያብሎስ የግሪክ አጠራር ሲሆን በዕብራይስጥ ሰይጣን ይባ ላል ፤ ትርጉሙም ተቃዋሚ ማለት ነው ፤ መላእክት ወደ ሰይጣንነት የተ ለወጡት በትዕቢታቸው ነው ፤ እግዚአብሔር ግን እንደ ሌላው ፍጥረት ሁሉ መልካም አድርጎ ፈጥሮአቸው ነበር ፤ (ዘፍ ፩ ፡ ፴፩) ።

ሰይጣን ሁል ጊዜ ሰዎችን ይፈትናል ፤ ወደ ክፉ ይመራል ፤ የእግዚአ ብሔርን ሕግ እንዲተላለፉ ያደርጋል ፤ ሰይጣን ወይም ዲያብሎስ «ከመ ጀመሪያ ጀምሮ ነፍሰ ገዳይ ነው» (ዮሐ ፡ ፰ ፡ ፵፬) ተብሎ እንደተጻፈ ሰዎችን ይገድላል ፤ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰው ጠባቂ መልአክን በሚልክበት ጊዜ ሰይጣን ደግሞ የሰውን ሕይወት ለመፈታተንና ለማጥ ፋት ከሠራዊቱ አንድ አንዱን ይልካል ።

ሰይጣናት ለእግዚአብሔር ስለማይታዘዙ በንስሐ ለመመለስም ስለ ማይፈቅዱ ካሣም እንዳይከፈልላቸው ባሕርያቸው ተስማሚ ስላይደለ በዘለዓለማዊ ፍርድ ወደ ጨለማ ተጥለዋል፤ (ማቴ ፡ ፳፭ ፡ ፵፩ ፤ ይሁዳ ፡ ፮፡) ምእመናንን የመፈታተን የማሳሳትና የመቃወም ሥራቸው እንዳለ ነው ፤ መልካቸውን እየለዋወጡ ሰዎችን ሲቃወሙ ይኖራሉ ፤ ( ፪፡ ቆሮ፡ ፲፩ ፡ ፲፬ ።)



www.ethiopianorthodox.org

## ፯. የሰው ተፈጥሮና አወዳደቁ

### ፩· ተፈጥሮው

በዚህ በሚታየው ግዙፍ ዓለም ውስጥ እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ እጅግ የከበረና የፍጥረት ሁሉ አክሊል (ቁንጮ) የሆነ ሰው ብቻ ነው ፤ ሰው ሲባል ነፍስና ሥጋ ወይም መንፈስና ሥጋ ያሉት ነው (ማቴ፡ ፲፡ ፳፰ ፤ መክብብ ፡ ፲፪ ፡ ፯፤ ፩ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፫—፭ ፤) አንዳንዶች ሰው ነፍስ መንፈስና ሥጋ ያሉት የሦስት ግብራት ቅንብር እንደሆነ ይናገራሉ ፤ ለዚህም (፩፡ተሰ፡ ፭፡ ፳፫) ይጠቅሳሉ ፤ ይሁን እንጂ ሁለቱ ነፍስና መንፈስ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ እየተለዋወጡ ይገኛሉ እንጂ በአንድነት አይገኙም ፤ ስለሞት በተነገረበት አንቀጽ ሞት አንዳንድ ጊዜ የነፍስና የሥጋ መለየት ሆኖ ተገልጦአል (ዘፍ ፡ ፴፭፡ ፲፰፤ ፩ኛ ነገሥ ፡ ፲፯ ፡ ፳፩፤) አንዳንድ ጊዜም የመንፈስና የሥጋ መለየት ሆኖ ተነግሮአል ፤ (ማቴ ፡ ፳፯ ፡ ፶) ።

ሰው ረቂቅ ነፍስ ብትኖረውም መልአክ አይደለም ፤ ግዙፍ አካል ቢኖረውም እንስሳ አይደለም ፤ ከመልአክም ከእንስሳም የተለየ ነው ፤ ሥጋዊና መዋቲ በመሆኑ ከመልአክ ይለያል ፤ ነባቢት ፥ ለባዊትና ሕያዊት ነፍስ ያላቸው በመሆኑም ከእንስሳ ይለያል ።

ለመጀመሪያ ጊዜ የሥጋ ተፈጥሮ ከመሬት ሲሆን ነፍስ ግን ከእግዚአብሔር የተሰጠች ናት፤ (መክ ፡ ፲፪፡ ፯) ፤ ከዚያ በኋላ ነፍስ ከእናትና አባት ትከፈላለች እንጂ ሁልጊዜ አትፈጠርም ፤ ከመዝገበ ነፍሳትም አትላክም ።

የሰው ተፈጥሮ «ለይኩን» በሚል ቃል ሳይሆን በእጅ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል ፤ ይህም ከፍጥረታት ሁሉ የከበረ መሆኑን ያመለክታል (ኢዮብ፡፲፡፰) የመጀመሪያው ሰው በዕብራይስጥ «አዳም» ይባላል ፤ ይህም ከመሬት መፈጠሩንና የመልኩን ቅላት ያመለክታል፤ በዕብራይስጥ «አዳም» መሬት «አዶም » ቀይ ማለት ነውና ።

ሰው በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ የተፈጠረ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል ፤ (ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፳፮—፳፯) የእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ ማለትም ቅርጽና መጠን አይነትም ሳይሆን ዕውቀት ፥ ቅድስና ፥ ሥልጣን የእግዚአብሔር እንደራሴ ሆኖ በምድር ላይ የፍጥረታት ገዥ መሆን ነፃ ፈቃድ ፥ ነፃ አእምሮና ዘለዓለማዊ ሕይወት ነው ፤ ስለዚህ ክፉም ሆነ መልካም ለመሥራት ለሰው ነፃ ፈቃድ አለው ።



ሰው ከመጀመሪያ ጀምሮ አሁን ባለው መልኩና ቅርጹ ፍጹም ሆኖ የተፈጠረ ነው፤ መጀመሪያ በሌላ መልኩ ከተፈጠረ በኋላ ቀስ በቀስ ዛሬ ካለበት መልክና ቅርጽ ደረሰ የሚለው አስተሳሰብ በክርስትና ሃይማኖት ትምህርታችን ተቀባይነት የለውም፤ ቅዱሳት መጻሕፍትም ሰው ከልዩ ተፈጥሮ ተነሥቶ ከዚህ ደረሰ በማለት አያስተምሩንም ፤ ሰው ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ፍጥረት በያይነቱና በየመልኩ እንደተፈጠረ ዘፍጥረት ያስተምረናል ፤ (ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፩—፴፩) ።

ሰው ብቻውን ይኖር ዘንድ መልካም ስላይደለ እግዚአብሔር ከአዳም ጐን ሔዋንን ፈጠረለት ሔዋን ማለትም የሕያዋን ሁሉ እናት ማለት ነው የመጀመሪያዋ ሴት ናትና፥(ዘፍ ፡ ፫፡ ፳) ከጐኑ መፈጠርዋ ወንድና ሴት (ባልና ሚስት) አንድ አካል ናቸው ከተባሉበት ምክንያት አንዱን ያሳያል እንደዚሁም የሰው ዘርዕ ሁሉ ከአንድ ምንጭ እንደመጣ ያመለክታል፤ ከዚህ በኋላ የሰው ዘር ሁሉ ከእነዚህ ከሁለቱ ከአዳምና ሔዋን ተገኝቶአል ።

### ፪/ አወዳደቁ ፤

ሰው በተፈጥሮው ነፃ ፈቃድ ያለውና ነፃ ፈቃዱንም ማንም የማይቃወመው መሆኑን ተመልክተናል ፤ ይህ ከሆነ ዘንድ በነፃ ፈቃዱ አመዛዝኖ ከእግዚአብሔር ይልቅ ለሰይጣን መታዘዝን መረጠ ፤ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተላለፈ ይህም ኃጢአት ለዘርዑ ሁሉ ተላልፎአል ፤ በኃጢአት ከወደቀና ከተረገመ ለሰይጣን ተገዥ ከሆነ በኋላ ወልዶአቸዋልና ልጆቹ ሁሉ እንደርሱ ኃጢአተኞች ሆነዋል ፤ (ዘፍ ፡ ፭ ፡ ፫) የአዳም በደል የመጀመሪያ እንደመሆኑ «ጥንተ አብሶ» ሲባል ለሁሉ በመተላለፉ ደግሞ «የውርስ ኃጢአት» እየተባለ ይጠራል ፤ ይህንም ሲያብራራ ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላል ፤ «በአንድ ሰው ምክንያት ኃጢአት ወደ ዓለም ገባ ፤ በኃጢአትም ምክያት ሞት መጣ ፤ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ - - - » (ሮሜ፡ ፭ ፡ ፲፪) ።

ሰው በኃጢአት ከወደቀ በኋላ ከገነት ወጣ ልጅነቱን አጣ ፥ ጸጋው ተገፈፈ ፥ ንጽሐ ጠባይውም አደፈ ፤ የመጀመሪያው ሰው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ቢጠብቅ ኖሮ ለዘለዓለም በሕይወት ይኖር ነበር ነገር ግን የፈጣሪውን ትእዛዝ በመተላለፉ ሞተ ሥጋና ሞተ ነፍስ ፥ ርደተ መቃብርና ርደተ ገሃነም ተፈረደበት (ዘፍ ፡ ፫ ፡ ፲፱ ፤ ሮሜ ፡ ፮ ፡ ፳፫) ።



www.ethiopianorthodox.org

ይሁን እንጂ ሰው እግዚአብሔርን ቢተው እግዚአብሔር ሰውን አልተወውም የዘመኑ ፍጻሜ ሲደርስ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው አንድ የባሕርይ ልጁን ልኮ ከመርገምና ከሙስና እንደሚያድነው ተስፋ ሰጥቷታል (ዘፍ ፣ ፫ ፣ ፲፭ ፣ ፲፱ ፣ ፫ ፤ ገላ ፣ ፬ ፣ ፬)፤ ትንቢትም አናግሮለታል ፤ (ኢሳ ፣ ፯ ፣ ፲፬ ፤ ሚክ ፭ ፣ ፪)።

## ፰. ምሥጢረ ሥጋዌ

ሰው ከፍጥረት ሁሉ የከበረና የላቀ ሆኖ በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ ተፈጥሮ በገነት ከኖረ በኋላ ከፈጣሪው ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ትእዛዝ በመተላለፉ ከገነት መውጣቱን ጸጋው መገፈፉን ንጽሐ ጠባይው ማደፉን ተመልክተናል ፤ ይሁን እንጂ በተፈጥሮ የተሰጠው ዕውቀቱና ነፃ ፈቃዱ ስላልተለየው እግዚአብሔር በፈታሒነቱ ቢፈርድበትም በመሐሪነቱ እንደሚምረው ስላወቀ በኃጢአቱ ተጸጸተ (ንስሐ ገባ) እግዚአብሔርም በፍርዱ አንጻር ምሕረቱ አለና ንስሓውን ተቀብሎ በእግረ አጋንንት መጠቅጠቁን በመንጸፈ ደይን መውደቁን ተመልክቶ ከሰይጣን ባርነት ከኃጢአት ቁራኛነት ነፃ ያወጣው ዘንድ ፈቀደ ።

ስለዚህም «የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ» ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ በተለየ አካሉ በፍጹም አካላዊና ባሕርያዊ ተዋሕዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍስዋ ነፍስን ነሥቶ ሰው ሆኖ ተወለደ ፤ ተወልዶም ከኃጢአት በቀር የሰውነትን ሥራ ሁሉ እየሠራ አደገ በሠላሳ ዓመቱ ተጠመቀ፤ በጰንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን ስለ እኛ ታመመ ፣ ሞተ ፣ ተቀበረ ፣ በሦስተኛውም ቀን ተነሣ ፤ በ፵ኛው ቀን ወደባሕርይ አባቱ በክብር አረገ ። በተነሣ በ~~አምስተኛው~~ ቀን መንፈስ ቅዱስን ለደቀ መዛሙርቱ ላከላቸው ። ሃምሳኛው

ምሥጢረ ሥጋዌ ረቂቅ ቢሆንም የሰው አእምሮ ሊያስተውለው የሚገባውን ያህል በቅዱሳት መጻሕፍትና በትምህርተ አበው ተገልጦአል ፤ የምሥጢረ ሥጋዌ መሠረቱ «ቃል በቅድምና ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ - - - ያም ቃል ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ» የሚለው ነው ፤ (ዮሐ፣ ፩ ፣ ፩—፲፬)፤አበው ሊቃውንትም ይህን የወንጌላዊውን ቃል መሠረት በማድረግ ስለ ምሥጢረ ሥጋዌ አምልተውና አስፍተው ተናግረዋል ፤ ቅዱስ ቄርሎስ ምሥጢረ ሥጋዌንና ተዋሕዶን ሲገልጥ እንዲህ ይላል ፤ «እንደ ተጻፈ ቃል ሥጋ ሆነ በማይመረመርም የተዋሕዶ ምሥጢር አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆነ ፤ መለኮትና ትስብእትም እርስበርሳቸው ሳይቀላቀሉ ሳይለያዩም አንድ ሆኑ» (ሃይ፣ ፸፫ ፣ ፲፮ ፣ ፴) ።

ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ሁለት ልደታት እንዳሉት እናምናለን ፤ ፩ኛ/ ቅድመ ዓለም ከአብ አካል ከአካል ባሕርይ ከባሕርይ የተወለደው ልደት ነው ፤ ፪ኛው አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ከቅድስት ድንግል ማርያም በሥጋ ያለአባት የተወለደው ልደት ነው ።

አምላክ ሰው በሆነ ጊዜ ሰውም በተዋሕዶ አምላክ ሆነ ፤ የቃል ገንዘብ ለሥጋ ፣ የሥጋም ገንዘብ ለቃል ሆነ ፤ የቃል ገንዘብ ማለት አምላክነት የባሕርይ ምስጋና ቀዳማዊነት ገቢረ ተአምራት ፣ ሕያውነት ለሥጋ ገንዘቡ ሆነዋል ፤ እንደዚሁም የሥጋ ገንዘብ ማለት ትሕትና ድካም መራብ መጠማት ሕማም ሞት ሌሎችም ካሣ የተፈጸመባቸው ግብራት ሁሉ ለቃል ገንዘቡ ሆነዋል ፤ እንደዚሁም ቅድመ ዓለም ከአብ አካል ዘእምአካል ፣ ባሕርይ ዘእምባሕርይ የተወለደው ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ድኅረ ዓለም በሥጋ ወልደ ማርያም መባልን ገንዘብ አደረገ ፤ ድኅረ ዓለም ከእመቤታችን የተገኘው ሥጋም በቃል ወልደ አብ መባልን ገንዘብ አደረገ፤ (መዝ፣ ፹፮ ፣) ወልደ አብ ወልደ ማርያም በተዋሕዶ ከበረ ፤ ቃል ከሥጋ ጋር በተዋሐደ ጊዜ በተዋሕዶው ፍልጠት ፣ ቡዓዴ ውላጤና ሚጠት የለበትም ፤ ተዋሕዶው እንደ ነፍስና ሥጋ ነው ፤ ሥጋ ግዘፉን ሳይለቅ ነፍስም ርቀትዋን ሳትለቅ ተዋሕደው አንድ ሰው እንዲባል ቃል ርቀቱን ትቶ ሳይገዝፍ ምልዓቱንና ስፋቱንም ትቶ ሳይወሰን ትስብእትም ግዘፉን ለቆ ሳይረቅ ሳይዋጥና ሳይጠፋ ውሱንነቱንም ለቆ ምሉዕና ስፉሕ ሳይሆን ነው ።

ሥጋ በመለኮት ቢዋጥ ቢጠፋ መለኮት ሊሞት አይችልምና ድኅነት ባልተገኘም ነበር ፤ ይሁን እንጂ በተዋሕዶው ምንታዌ የለበትም ፤ ከተዋሕዶ በኋላ ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ እንጂ ሁለት አካላት ሁለት ባሕርያት ወይም አንድ አካል ሁለት ባሕርያት አሉት አይባልም ፤ እንደዚሁም አንድ ፈቃድና አንድ ግብር እንጂ ሁለት ፈቃዳትና ሁለት ግብራት የሉትም ።

ሥጋ በተዋሕዶ አምላክ ቢሆንም ጥንት አለው ፤ ፍጻሜ ግን የለውም ከአምላክ ጋር ተዋሕዶአልና አለ ፤ ይኖራልም ፤ እንዲሁም ቃል ድኅረ ዓለም ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋና ነፍስን ተዋሕዶ ሰው ቢሆንም ጥንት የለውም ፍጻሜም የለውም የነበረ ያለና የሚኖር ዘለዓለማዊ ነው ፤ ህላዌው (ለፈ እማርያም) ከማርያም ወዲህ አይደለምና ።




www.ethiopianorthodox.org

## ፱. የክርስቶስ ሕማም ፣ ሞት ፣ ትንሣኤና ዕርገት

፩. <u>ሕማሙ፡—</u> መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መምጣቱ ስለ ዓለም ቤዛ በመስቀል ላይ ተሰቅሎና ሞቶ ዓለምን ለማዳን ነው ፤ በመሆኑም በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈ በሃይማኖታችንም ቀኖና እንደተገለጠ «ስለእኛ ስለ ሰዎች ስለመዳናችን - - - በጳንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን ተሰቀለ መከራ ተቀበለ» ሰው መሆኑ በሰውነቱ ሕማምና ሞትን ለመቀበል እንዲችል ነው ፤ በመለኮቱ ሕማም ወይም ሞት የለበትምና ፤ በሃይማኖት ትምህርታችን ክርስቶስ ታመመ መከራ ተቀበለ ሲባል በእውነት ፍጹም ሰው መሆኑንና ሰውነቱ ምትሐት አለመሆኑን ለመግለጥ ነው ፤ ከዚህም ሌላ ሰው በሆነ ጊዜ ከኃጢአት ብቻ በቀር የሰውን ባሕርይ ሁሉ ማለት በሥጋ የመታመም የመድከም የመራብ ባሕርይን ፣ በነፍስ የሁከት የመተከዝ ፣ የመፍራትና የድንጋጤ ባሕርይን ገንዘብ ማድረጉን ለማስረዳት ነው ።

ጌታችን በመስቀል ላይ መከራ መቀበሉና መሞቱ ትንቢቱ ይደርስ ዘንድ ይፈጸም ዘንድ ነው ፤ (ዘዳግ ፳፩ ፣ ፳፫ ፤ ገላ ፣ ፫ ፣ ፲፫ ፤ ኢሳ ፣ ፶፫ ) ።

፪. <u>ሞቱ ፡—</u> ጌታችን የመጣለት ዓላማና ትንቢቱ ሁሉ መፈጸሙን ዐውቆ «ሁሉ ተፈጸመ» ካለ በኋላ ቅድስት ነፍሱን ከቅድስት ሥጋው በመለኮታዊ ሥልጣኑ ለየ ።

የክርስቶስ ሞት የነፍስና የሥጋ መለየት ነው ፤ በሃይማኖት ትምህርታችን ክርስቶስ ሞተ ባልን ጊዜ ሥጋ ብቻ ሳይሆን መለኮትም «በሥጋ ሞተ» ብለን እናምናለን ፤ የዕሩቅ ብእሲ ሞት ብቻ ሊያድን አይችልምና ፣ (፩. ጴጥ፡፫ ፣ ፲፰ ። )

የክርስቶስ ሞት በእውነት ፍጹም ሰው መሆኑን ያረጋግጣል ፤ ሞቱ ለበደላችን ሁሉ ካሣ (ቤዛ) ነው (ማቴ ፳ ፣ ፳፰ ፤)ሞቱ ሞትን ደምስሶልናል ፤ መድኃኒታችን በመስቀል ላይ ከሞተበት ሰዓት ጀምሮ ሥጋው ፫ መዓልትና ፫ ሌሊት በከርሠ መቃብር ቆይቶአል ፤ ይህም የሚያረጋግጠው ፩ኛ በእውነት መሞቱን ፣ ፪ኛ/ ትንሣኤው እውነተኛ መሆኑን ነው ፤ የተነሣ ፣ ያው የሞተውና የተቀበረው ነውና ፣ ጌታችን በመቃብር ፫ መዓልትና ፫ ሌሊት ቢቆይም ሙስና መቃብር አላገኘውም ፤ (መዝ.፲፭ . ፲ ፣ የሐዋ . ፪ . ፳፯ ፣ ፴፩ ፣ ፲፫ ፣ ፴፬—፴፭ ። )



የክርስቶስ ሥጋው በመቃብር ሳለ ቅድስት ነፍሱ ወደ ሲኦል ወርዳለች ፤ (ኤፌ ፣ ፬ ፣ ፰—፱)፤ ወደ ሲኦል መውረዱ ሥቃይ ለመቀበል አይደለም ፤ በሲኦል ለነበሩ ነፍሳት ወንጌልን ለመስበክና ለማዳንም አልነበረም በሲኦል ያሉ ነፍሳት ለማመንና ንስሓ ለመግባት ዕድል የላቸውምና ፤ ነገር ግን ክርስቶስ ወደሲኦል የወረደው ሰው ሁኖ ለማዳን መምጣቱን ያምኑ ለነበሩ ጻድቃን ብሲት ድል አድራጊነቱን ፣ ነፃ አውጭነቱንና በሲኦል ላይ ኃይል ያለው መሆኑን ለማወጅ እነርሱንም ለማውጣት ነው ፤ (፩፡ ጴጥ ፣ ፫ ፣ ፲፰—፳ )።

፫. <u>ትንሣኤው፡—</u> ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሞተ በሦስተኛው ቀን መቃብር ክፈቱልኝ መግነዝ ፍቱልኝ ድንጋይ አንሡልኝ ሳይል በመለኮታዊ ሥልጣኑ ተነሥቶአል ።

ትንሣኤው የነፍስና የሥጋ መዋሐድና በሕይወት ቆሞ መታየት ብቻ አልነበረም ፤ የተነሣው አካል በመስቀል የተሰቀለውና የተቸነከረው ቢሆንም ያው አካል በተሐድሶ ተነሥቶአል፤ምክንያቱም በፈቀደ ጊዜ ይታይ ነበረ እንጂ በቦታ የተወሰነ አልነበረም ፤ በተዘጋ ቤት ይገባ ነበር፤ (ዮሐ፡ ፳ ፣ ፲፱፤) ከሰዎች ፊት ይሰወር ነበር(ሉቃ ፳፬ ፣ ፴፩፤) ከተነሣ በኋላ ምግብ ሲመገብ ቢታይም በምግብ ምክንያት ኃይልን ለመንሣት አልነበረም ፤ (ሉቃ ፣ ፳፬ ፣ ፵፪—፵፫፤) የክርስቶስ ትንሣኤ ከአልአዛርና ከሌሎችም ሰዎች ትንሣኤ የተለየ ነው ፤ የእነዚያ ትንሣኤ በብሉይ ሥጋ ነው፤ ቆይተውም ሞተዋል ፤ እርሱ ግን ዳግም ሞት የለበትም ፤ (ራእ ፣ ፩ ፣ ፲፰ ፤) ስለዚህም በኩረ ሙታን ይባላል ፤ (፩፡ ቆሮ፡ ፲፭ ፣ ፳ ፤ ቆላ ፣ ፩ ፣ ፲፰ ።)

የክርስቶስ ትንሣኤበአራቱ ወንጌሎችና በሌሎችም የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ ተገልጦአል ፤ ከዚያም አስቀድሞ በትንቢት ተነግሮ ነበር ፤ (ኢሳ ፣ ፶፫ ፣ ፰ ፤ መዝ ፣ ፲፭ ፣ ፲ ።)

በክርስቶስ ትንሣኤ ሞትና ሰይጣን ድል ሆነዋል፤(፩፡ ቆሮ ፣ ፲፭ ፣ ፲፯ ፣ ፳ ፤ ሮሜ ፣ ፮፡ ፫—፲፩ ፤ ኤፌ ፣ ፪፡ ፬—፯) የሰው ልጅ ድኅነት ተፈጽሞአል ፤ (ሮሜ ፣ ፬ ፣ ፳፭፤)ትንሣኤው የክብሩና የኃይሉ መገለጫ ነው፤ (፩ ፣ ቆሮ ፣ ፲፭ ፣ ፵፪—፵፬ ፤) የእኛንም ትንሣኤ ያረጋግጣል ፤ እርሱ በክብር እንደተነሣ እኛም እንደርሱ በክብር እንነሣለን (፩፡ቆሮ፡ ፲፭፡ ፳—፳፪፤) ትንሣኤው ለክርስትና እምነት መሠረት መሆኑን ቅዱስ ጳውሎስ ሲያስረዳ የሚከተለውን ያስተምረናል «ክርስቶስ ካልተነሣ እምነታችሁ ከንቱ ነው» (፩፡ ቆሮ፡፲፭፡ ፲፯—፲፰ ) ።



www.ethiopianorthodox.org

፬/ ዕርገቱ፡— ጌታችን ከተነሣ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ አንዳንድ ጊዜ እየታየ ለ፵ ቀናት ከቆየ በኋላ በክብር ወደሰማይ ዐረገ ፤ የክርስቶስ ዕርገትና በአብ ቀኝ መቀመጥ የአድኅኖቱ ሥራ ፍጻሜ ነው ፤ ስለ ዕርገቱ ቅዱሳት መጻሕፍት በሰፊው ይናገራሉ ፤ (ሉቃ፡፳፬ ፶—፶፫ ፤ የሐዋ፡ ፩፡ ፮—፲፩፤ ኤፌ፡ ፩፡ ፳፡ ፬፡ ፰—፲፤ ፩፡ ጢሞ፡ ፫፡ ፲፮፤ ዕብ ፡ ፩ ፡ ፫-፬ ፡ ፲፬ ፮፡፳ ፡ ፱ ፡ ፳፬)፤ «ዐረገ» ማለትም ልዕልናውን ክብሩን ለመግለጥ ነው እንጂ በሰማይ ሲኖር በምድር የለም ለማለት አይደለም ፤ ከዚህም ሌላ ዕርገቱ የጻድቃንን ክብርና ልዕልና ያመለክታል (ኤፌ ፡ ፪፡ ፮፤ ዮሐ ፡ ፲፯ ፡ ፳፬ )።

ከዐረገም በኋላ «በአብ ቀኝ ተቀመጠ» (ኤፌ ፩ ፡ ፳ ፤ ዕብ ፡ ፲ ፡ ፲፪፤) በቀኝ ተቀመጠ የሚለው አነጋገር ፊደል በፊደል የሚተረጐም ብቻ ሳይሆን ኃይልንና ሥልጣንን ክብርንም የሚያመለክት ነው፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ቀኝና ግራ ፡ ፊትና ኋላ የለምና ፤ ስለዚህ ነ ቢረ የማን ክርስቶስ ግብረ ትስብእትን ከፈጸመ በኋላ እንደገና የሰውነትን ሥራ የማይሠራ ነገር ግን ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በክብር መለኮታዊ ሥራውን እየሠራ የሚኖር መሆኑን የሚያስረዳ ቃል ነው ።

## ፲. ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ፤

ድንግል ማርያም ከቤተ ዳዊት የተወለደች ናት ፤ ወላጆችዋም ቅዱሳን ኢያቄምና ሐና ይባላሉ ፤ ከሕፃንነትዋ ጀምራ ለእግዚአብሔር የተሰጠች ስለነበረች በቤተ መቅደስ አደገች ፤ በ፲፭ ዓመት ዕድሜዋ በብሥራተ መልአክ በግብረ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ወልድን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ወለደች ።

ቅድስት ማርያም ዘለዓለማዊት ድንግል ናት ፤ ከመፅነስ በፊት በመፅነስ ጊዜ ከመፅነስ በኋላም ድንግል ናት ፤ ከመውለድ በፊት ፡ በመውለድ ጊዜ ፡ ከመውለድ በኋላም ድንግል ናት ፤ ስለዚህም ዘወትርድንግል ወይም ዘለዓለማዊት ድንግል ትባላለች ፤ ስለ ዘለዓለማዊ ድንግልናዋም ቅዱሳት መጻሕፍትና ሊቃውንት አበው ይመሰክራሉ ፤(ኢሳ ፡ ፯ ፡ ፲፬ ፤ ሕዝ ፡ ፵፬፡ ፩—፫ ፤ ማቴ ፩ ፡ ፳ ፤ ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፴፬፤)«እርሱን አምላክን ከወለደች በኋላ በድንግልና እንደ ወትሮው ኖረች » (ኤፍሬም ፡ ፬ ፡ ፳ ፤)

ቅድስት ማርያም በሥጋ ብቻ ሳይሆን በሐሳብም ድንግል ናት ፤ በሐሳብዋ ድንግል ናት ማለትም ከኃጢአት ፍጽምት ንጽሕት ናት



ማለት ነው ፤ በዚህም መሠረት እመቤታችን በሐልዮ በነቢብ በገቢር ማለት በሐሳብም በቃልም በግብርም ኃጢአት የሌለባት ፍጽምት ንጽሕት ናት ፤ ይህም ከእግዚአብሔር የተሰጣት ጸጋ ነው፤(ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፳፰፤) አንዳንዶች እመቤታችን አድፎ የነበረው የአዳም ጠባይ ወይም ጥንተ አብሶ እንደሌለባት ያስተምራሉ ፤ ነገር ግን ይህ ትምህርት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ተቀባይነት የለውም ፤ ምክንያቱም እመቤታችን ከኢያቄምና ከሐና በሩካቤ ዘበሕግ የተገኘች ናት እንጂ ከሰማይ የወረደች የመላእክት ወገን አይደለችምና ፤ ካሣ የማያስፈልጋትም ሳትሆን ክርስቶስ በደሙ ከዋጃቸው ካሣም ከተከፈለላቸው ወገን ናት ፤ ሆኖም እንደ አዳምና ሔዋን የምኞት የመናገርና የገቢር ኃጢአት ፈጽሞ የለባትም ።

ንጽሕት ድንግል ማርያም ክብር ምስጋና የሚገባት (ብፅዕት) ናት ፤ መላእክትም ፡ ሰዎችም አክብረዋታል አመስግነዋታልም ።

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል «ጸጋን የተመላሽ ሆይ ከሴቶች መካከል ተለይተሽ የተባረክሽ የከበርሽ ነሽ» በማለት አመሰግኖአታል ፤ (ሉቃ ፩ ፡ ፳፰—፳፱ ።)

ቅድስት ኤልሳቤጥም እንደ መልአኩ ቃል «አንች ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ - - - የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይገባኛል ? - - - ከጌታ የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና ያመነች ብፅዕት ናት» በማለት አክብራ አመስግናታለች ፤ (ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፵—፵፭ ።)

ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም አክብሮ ይታዘዝላት ይጠነቀቅላት ነበር ፤ (ሉቃ ፡ ፪ ፡ ፶፩ ፤ ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፭ ፤ ዮሐ ፡ ፲፱ ፡ ፳፮—፳፰ )።

እርስዋ ራስዋም በመንፈስ ቅዱስ ተመርታ «ከእንግዲህ ወዲህ ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑኛል ያከብሩኛል» በማለት ስለራስዋ ክብር ተናግራለች (ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፵፰—፵፱ )።

ስለዚህ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በቅዳሴ ፡ በመዝሙርና በማኅሌት በስብከትም በጸሎትም በጠቅላላ በቤተ ክርስቲያን በሚፈጸመው የአምልኮት ሥነ ሥርዓት ሁሉ ከፍተኛ ክብር አላት ፤ መትሕተ ፈጣሪ መልዕልተ ፍጡራን ናት ፤ በወርና በዓመት የተለየ የክብር (የበዓል) ቀን ተመድቦ በልዩ ሥነ ሥርዓት ትከብራለች ።

ድንግል ማርያም እመ አምላክ ወይም ወላዲተ አምላክ ተብላ ትጠራለች ፤ (ሉቃ፡ ፩፡ ፵፫ ፤) ክርስዋ በድንግልናዊ ልደት የተወለደው



www.ethiopianorthodox.org

ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ነውና ከአብ የተወለደው ከቅድስት ማርያም የተወለደው ነው ፤ ከአብ በመለኮታዊ ባሕርይ የተወለደው ከድንግል ማርያም በሰብአዊ ባሕርይ ተወልዶአል ፤ ያው አንዱ ወልደ እግዚአብሔር ከርስዋ በሥጋ ስለ ተወለደ ወላዲተ አምላክ እመ አምላክ ትባላለች ።

ድንግል ማርያምን ወላዲተ አምላክ ካላልናት ከርስዋ የተወለደው ክርስቶስ ሰው ብቻ እንጂ አምላክ አይደለም ያሰኝብናል ፤ ከርስዋ የተወለደውም ሰው ብቻ (ዕሩቅ ብእሲ) ከሆነ ሊያድነን ባልቻለም ነበር ፤ ስለዚህ ድኅነታችን የተመሠረተው ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ በመሆንዋ ላይ ነው ፤ ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ እንደሆነች የማያምን የክርስቶስን አምላክነትም አያምንም ።

ድንግል ማርያም በእግዚአብሔር ዘንድ ከፍተኛ ባለሙዋል ስለሆነች አማላጃችን ናት ፤ እርስዋ ለእኛ የአደራ እናት ናት ፤ እኛም ለእርስዋ የአደራ ልጆች ነን (ዮሐ ፥ ፲፱ ፥ ፳፯—፳፱ ፤ ) ስለዚህ ትማልድልናለች ።

ድንግል ማርያም ከጌታችን የአድኅኖት ሥራ የተለየችበት ጊዜ የለም፤ ክርስቶስ ዓለምን ያዳነው ከርስዋ በነሣው ሥጋ ነውና ፤ ስለዚህም አማላጅነትዋ የታመነ ነው ፤ በቃና ዘገሊላ በተደረገው ሠርግ ላይ ተገኝታ «እርሱ የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ» ማለትዋ ክርስቶስ ለሰዎች ሊያደርገው ያቀደውን ሁሉ የምታውቅና ሰዎች ለክርስቶስ በመታዘዝ እንዲድኑ የምትመራ መርሕ ለመንግሥተ ሰማያት መሆንዋን ያመለክታል ፤ (ዮሐ ፥ ፪ ፥ ፩ ።

በዚህ መሠረት እመቤታችን ቅድስት ማርያም «ንጽሕት ድንግል ወላዲተ አምላክ» ተብላ እንደምትጠራ ሰአሊተ ምሕረት ለውሉደ ሰብእ ለሰው ልጆች ምሕረት ለማኝ ተብላ ትጠራለች (ኤፍሬም ፥ ፮ ፥ ፩ ።)

ድንግል ማርያም ንጽሕትና ቅድስት መልዕልተ ፍጡራን ብትሆንም በ፷፬ ዕድሜዋ አዳማዊ ሞትን ሞታለች ፤ ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርሱ አይችሉምና (፩ ቆሮ ፥ ፲፭ ፥ ፶ ፤)ይሁን እንጂ ሙስና መቃብር አላገኛትም ፤ በሞተች በሦስተኛው ቀን በእግዚአብሔር ኃይል ተነሥታ በክብር ዐርጋለች ።

## ፲፩. ቤተ ክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያን ቃል በቃል ሲፈታ የክርስቲያን ቤት ማለት ነው ፤ ሲተረጐም ግን ክርስቲያኖች ለጸሎት ለአምልኮት የሚሰበሰቡበት ቤት



ማለት ነው ፤ እንደዚሁም አዲስ ሕዝበ እግዚአብሔር የተባሉ ክርስቲያኖችን ያመለክታል ፤ (፩ ፥ ቆሮ ፥ ፮ ፥ ፲፱፤) በተጨማሪም በክርስቶስ የተመሠረተና የተቋቋመ ማኅበረ ምእመናንን የሚያመለክት ቃል ነው ፤ በቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት የዜማ ድርሰት « - - - አቅሌስያ ቤተ ክርስቲያን ዘንሰምያ» የሚል ንባብ አለ ፤ አቅሌስያን ቤተ ክርስቲያን ለማለት ነው ፤ ቃሉ የግሪክ ነው ፤ ትርጓሜውም የተጠራች የተመረጠች ማለት ነው ፤ እንደገናም ጉባኤ ማለት ይሆናል ፤ ማኅበረ ምእመናንም በክርስቶስ የተጠሩና የተመረጡ ስለሆኑ ይህ ስያሜ ተሰጥቶአቸዋል ፤ (፩፥ ጴጥ፥ ፪፥ ፱—፲ ) ።

የብሉይ ኪዳን ሕዝበ እግዚአብሔር ፥ ቤተ እስራኤል ነበሩ ፤ በሐዲስ ኪዳን ግን ሕዝበ እግዚአብሔር የሚባሉ ቤተ ክርስቲያን ወይም ማኅበረ ምእመናን ናቸው ፤ የብሉይ ኪዳን ሕዝበ እግዚአብሔር በደመ እንስሳ የታተሙ ነበሩ ፤ የሐዲስ ኪዳን ሕዝበ እግዚአብሔር ግን በደመ ክርስቶስ የታተሙ ናቸው ፤ የብሉይ ኪዳን ሕዝበ እግዚአብሔር ሕግን በሙሴ በኩል ተቀብለዋል ፤ የሐዲስ ኪዳን ሕዝበ እግዚአብሔር ግን ወንጌልን በቀጥታ ከክርስቶስ ተቀብለዋል ፤ ማኅበረ ምእመናን ወይም ክርስቲያኖች በማኅበረ እስራኤል ስለገቡ ስሙንም ክብሩንም ይዘዋል ።

በክርስቶስ ለተመሠረተችው እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን በጸሎተ ሃይማኖት ውስጥ የተገለጡ አራት መታወቂያዎች አሉአት ።

፩/ ቤተ ክርስቲያን «አንዲት ናት»፤ መሪዋ ራሱ ክርስቶስ አንድ ነውና ፤ በጭቃ በጨፈቃ ፥ በዕብነ በረድ በወርቅና በዕንቊ ብትሠራ ሥርዐተ አምልኮትዋ አንድ ነውና ።

፪/ ቤተ ክርስቲያን«ቅድስት ናት»ክርስቶስ በደሙ ቀድሶአታልና (የሐዋ ፥ ፳፥ ፳፰)፤ ክርስቶስ የሠራላትን ቅዱሳት ምሥጢራት ጠብቃ ምእመናንን እየቀደሰች ማለት እያከበረች ትኖራለችና ፤ ቅዱስ ቃሉን ታስተምራለችና ፤ እንደዚሁም የቅዱስ መንፈስ ማደሪያ ናትና «ቅድስት» ትባላለች (፩፥ቆሮ፥ ፮ ፥ ፲፱፤ ፪፥ቆሮ ፥ ፫ ፥ ፲ ) ፤ ከዚህም ጋር እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ቅዱሳን ከቤተ ክርስቲያን ይገኛሉና ቅድስት ናት ።

፫/ «ኵላዊት»(በሁሉ ያለች) ናት ፤ በግእዝ «እንተ ላዕለ ኵሉ» ተብሎአል ፤ ይህም በዓለም ሁሉ ያለች ማለት ነው ፤ ቤተ ክርስቲያን በዘር በቀለም ሳትወሰን በዓለም ውስጥ ለሚገኙ ለሰው ዘሮች ሁሉ ናት ፤ (ገላ ፥ ፫ ፥ ፳፭—፳፱)፤ ቤተ ክርስቲያን በዘመናት ሁሉ ያለችና የምትኖር ናት፤ (ማቴ፥ ፳፰ ፥ ፳)፤ ቤተ ክርስቲያን በዐጸደ ሥጋና በዐጸደ ነፍስ ላሉትም ሁሉ ናት ።



www.ethiopianorthodox.org

፬/ ቤተ ክርስቲያን «ሐዋርያዊት ናት» ፤ ከክርስቶስ በኋላ በሐዋርያት ትምህርትና ስብከት ተስፋፍታለችና (የሐዋ፡ ፪ ፡ ፵፩ ፤ ኤፌ ፡ ፪፡ ፳ ፤) የሐዋርያትን ትምህርትና ትውፊት ተቀብላ ስታስተምር ትኖራለችና ፤ የመሪዎችዋ የጳጳሳት ሥልጣነ ክህነት ሳይቋረጥ ከሐዋርያት የተያያዘ ነውና ሐዋርያት ወይም የሐዋርያት ጉባኤ ተብላ ትጠራለች ፤ እነዚህን አራቱን መታወቂያ ምልክቶች ያልያዘች ቤተ ክርስቲያን ፡ ቤተ ክርስቲያን አትባልም ።

## ፲፪. ምሥጢራት ቤተ ክርስቲያን

ምሥጢር የሚለው ቃል ግሪክ ነው ፤ በግእዝና በአማርኛም እንዳለ ተወስዶአል ፤ ትርጓሜውም የማይታይ ረቂቅ ማለት ነው ፤ ምሥጢራት ቤተ ክርስቲያን ማለትም በሚታይ ምልክት የማይታይ ጸጋ የሚሰጥባቸው በቤተ ክርስቲያን የሚፈጸሙ ሥርዐታት ማለት ነው ፤ በቤተ ክርስቲያን ቀኖና በግዙፍ ምልክት የሚሠሩ ነገር ግን በእምነት ዐይን ብቻ የሚታዩ ረቂቃን የሆኑ ነገሮች ሁሉ ምሥጢራት ይባላሉ ። ዕርገተ ጸሎት በዕጣን (መዝ ፩፻፵፩ ፡ ፪ ፤ ራእ ፰ ፡ ፫-፬) ፍትሐተ ሙታን በጸሎት (፪ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፲፯-፲፰) ምሥጢራት ናቸው ፤ በተለይ ምሥጢራት የሚባሉ በጳጳሳት ወይም እውነተኛ ሐዋርያዊ ሥልጣነ ክህነት ባላቸው ቀሳውስት የሚፈጸሙት የማይታይ መለኮታዊ ጸጋ የሚሰጥባቸውና በግዙፍ ምልክት የሚሠሩት ናቸው ።

ምሥጢራት ቤተ ክርስቲያን በቍጥር ሰባት ናቸው ፤ እነርሱም ጥምቀት ፤ ሜሮን ፡ ቅዱስ ቍርባን ፡ ክህነት ፡ ንስሓ ፡ ተክሊል ፡ ቀንዲል ናቸው ፤ ይኸውም በመጽሐፈ ምሳሌ ፱ ፡ ፩ ላይ በተጠቀሱት አዕማድ ምሳሌነት ነው ፤ እንደዚሁም በትንቢተ ኢሳይያስ ፲፩ ፡ ፩—፪ የተጻፉትን ሰባት ሀብታት ስለሚያሰጡ ነው ፤ በእነዚህም የተለያየ ሀብት መንፈሳዊ ይሰጣል ፤ በጥምቀት መንፈሳዊ ልደት ፡ በሜሮን መንፈሳዊ ዕድገት፡በቅዱስ ቍርባን መንፈሳዊ ምግብ በክህነት ፡ የማስተማር ፡ የመምራትና የመቀደስ መንፈሳዊ ኃይል ፡ በንስሓ መንፈሳዊ ተሐድሶና ስርየተ ኃጢአት ፡ በተክሊል የጋብቻ ጽንዐትና ቅድስና በቀንዲል ሥጋዊና መንፈሳዊ ኃይል ይሰጣል ።

ከሰባቱ ምሥጢራት ቤተ ክርስቲያን ለምእመናን ሁሉ የሚያስፈልጉና የማያስፈልጉ አሉ ፤ ጥምቀት ሜሮን ቅዱስ ቍርባንና ንስሓ



ለሁሉም ያስፈልጋሉ ፤ ክህነት ፡ ቀንዲልና ተክሊል ግን ለሁሉም ግድ አያስፈልጉም ።

ከሰባቱ ምሥጢራት መካከል የማይደገሙና የሚደገሙ አሉ ፤ ጥምቀት፡ ሜሮን ፡ ክህነትና ተክሊል አይደገሙም ፤ የቀሩት ግን ይደገማሉ፤ ይልቁንም ይዘወተራሉ ፤ በአንድ ቀን የሚፈጸሙና የማይፈጸሙ አሉ ፤ እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዐተ ጥምቀት ሜሮንና ቅዱስ ቍርባን ለመጀመሪያ ጊዜ በአንድ ቀን ይፈጸማሉ ፤ ሌሎች ግን በሚያስፈልጉበት ጊዜ ይፈጸማሉ ።

ከሰባቱ ምሥጢራት መካከል ክህነት በጳጳስ ብቻ የሚሰጥ ሲሆን ሌሎቹ ግን በጳጳስ ወይም በቀሳውስት ሊሰጡ ይችላሉ ።

## ፩. ምሥጢረ ጥምቀት

ጥምቀት ማለት መጥለቅ ፡ መነከር ከራስ ጠጉር እስከ እግር ጥፍር በውሃ ውስጥ መግባት ማለት ነው ።

ከሰባቱ ምሥጢራት ሁሉ መጀመሪያው ጥምቀት ነው ። ጌታችን «ማንም ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት አይችልም» ብሎ በተናገረው መሠረት ፡ ጥምቀት ወደ ቤተ ክርስቲያንና ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር መግቢያ በር ነው ፤ (ዮሐ፡፫ ፡ ፭) ያልተጠመቀ የቤተ ክርስቲያን አባል አይሆንምና ፤ ወደ መንግሥተ ሰማያትም አይገባምና ።

ስለ ጥምቀት አስቀድሞ በብሉይ ኪዳን ምሳሌ ተመስሎአል ትንቢትም ተነግሮአል ፤

ምሳሌዎቹ የሚከተሉት ናቸው ።

ሀ/ የኖህ መርከብ ዘፍ ፯ ፡ ፲፯ ፤ ፩ ጴጥ፡፫ ፡ ፳—፳፪ ፡
ለ/ ግዝረት ቆላስይስ ፪ ፡ ፲፩—፲፪ ።
ሐ/ እስራኤላውያን ቀይ ባሕርን መሻገራቸው ፩፡ቆሮ ፲ ፡ ፩—፲፪ ፤
መ/ ጥምቀተ ዮሐንስ ማቴ፡፫ ፡ ፲፩ ፤ የሐዋ፡፩ ፤ ፭ ፡ ፲፱ ፡ ፩—፲፰ ፤

ትንቢቱም «ከኃጢአታችሁ ትነጹ ዘንድ በንጹሕ ውሃ እረጫችሁ አለሁ» ተብሎ የተነገረው ነው ፤ (ሕዝ ፡ ፴፮ ፡ ፳፭ ።)

### የጥምቀት አመሠራረት

ጥምቀት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ተመሥርቶአል ፤ ጌታችን ጥምቀትን በተግባርና በትእዛዝ መሥርቶታል ፤ በተግባር ማለት ራሱ



www.ethiopianorthodox.org

ጌታችን በማየ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ ተጠምቆአል ። (ማቴ ፫፡፲፫—፲፯ ፤) በትእዛዝ ማለት ከትንሣኤ በኋላ «ሑሩ ወመሀሩ ኵሎ አሕዛበ ወአጥምቅዎሙ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ ፤ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስም ስም አጥምቋቸው» (ማቴ ፳፰፡ ፲፰—፲፱) ፤ ብሎ ደቀ መዛሙርቱን አዝዞአቸዋል ፤ ነገር ግን በምሥጢረ ጥምቀት የሚገኘው ሙሉ ጸጋ የተሰጠ በአምሳኛው ቀን በመንፈስ ቅዱስ መውረድ ነው ፤ (የሐዋ ፤ ፪ ፡ ፩-፭ ፤ ፲፱ ፡ ፯) ።

## አፈጻጸሙ

ምሥጢረ ጥምቀት በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እውነተኛ ሐዋርያዊ ሥልጣነ ክህነት ባለው ካህን ወይም ጳጳስ የተመደበው ጸሎት ከተደረሰ በኋላ በውሃ ውስጥ በመጥለቅ ይፈጸማል ፤ በመጀመሪያ ጊዜ ዲያቆናት ያጠምቁ ነበር ፤ (የሐዋ ፤ ፰፡ ፴፰ )፤ በኋላ ግን በቄስ ወይም በጳጳስ ብቻ እንዲሆን ተወስኖአል ።

ጥምቀት በውሃ መሆኑ ፡- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በውሃ ስለተጠመቀ ነው ማቴ ፫ ፡ ፲፫-፲፯)፤ «ማንም ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ በቀር ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር መግባት አይችልም» ስለተባለ ነው (ዮሐ፡፫፡ ፭)፤ሐዋርያትም በውሃ ያጠምቁ ነበር (የሐዋ፡ ፫፡፴፯-፴፰፡ ፰ ፡ ፴፰ )፤ ውሃ መንጽሒ ነው ጥምቀትም ከኃጢአት ያነጻል ውሃ ለሁሉ የሚገኝ ነው ጥምቀትም ለሁሉ የታዘዘ ነው ፤ ተጠማቂው በሚጠመቅበት ጊዜ ፫ ጊዜ በውሃ ውስጥ ብቅ ጥልቅ እንዲል ይደረጋል ፤ ጌታችን እንደዚሁ ተጠምቋልና (ማቴ፡ ፫ ፡ ፲፯ )፤ ሐዋርያትም በዚሁ አይነት ያጠምቁ ነበርና (የሐዋ ፰ ፡ ፴፰ )፤ ከዚህም ሌላ ጥምቀት የክርስቶስ የሞቱና የመቀበሩ ምሳሌ ነውና ምሳሌነቱ እንዲጸድቅ ተጠማቂው ሦስት ጊዜ በውሃው ውስጥ ብቅ ጥልቅ ይላል (ሮሜ ፮ ፡ ፫-፬) ።

## በምሥጢረ ጥምቀት የሚገኝ ጸጋ

በምሥጢረ ጥምቀት የውርስ ኃጢአትና ከጥምቀት በፊት የተሠሩ ኃጢአቶች ሁሉ ይሰረያሉ(የሐዋ፡ ፪ ፡ ፴፰—፴፱ ፤ ፳፪ ፡ ፲፮ ፤ ቆላ ፪ ፡ ፲፪—፲፫ ፤ ፩ ጴጥ ፫ ፡ ፳፩ )፤ መንፈሳዊ ልደትና ሐዲስ ሕይወት ይገኛሉ፤ (ዮሐ ፫ ፡ ፫—፭)፤ ክርስቶስን መምሰል (ገላ ፫ ፡ ፳፬—፳፯) ቅድስና (ንጽሕና) (ኤፌ፡ ፭ ፡ ፳፭—፳፯) ፤ ድኅነት (ማር ፡ ፲፮ ፡ ፲፮) ይገኛል ።

ጥምቀት ለሁሉም ነው ፤ ወንድ ሴት ሕፃን ሽማግሌ ካመኑ መጠመቅ አለባቸው ፤ ምክንያቱም በመጀመሪያው ሰው ምክንያት የሁሉም ንጽሐ ጠባይዕ አድፏልና ፤ (ኢዮብ ፲፬ ፡ ፬ ፤ መዝ ፡ ፶፩ ፡ ፯ ፤ ሮሜ ፭ ፡ ፲፪ ፤ ኤፌ ፪ ፡ ፫) ፤ ንጽሐ ጠባይዕ ያደፈባቸው ወይም የጥንተ አብሶ ውርስ ያለባቸው ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት አይችሉምና (፩ ፡ ቆሮ ፲፭ ፡ ፶ ፤ ራእ፡ ፳ ፡ ፳፯ )፤ በውሃ የሚፈጸም ክርስቲያናዊ ጥምቀት ብቻ ሰውን አዲስ ልደት እንዲወለድ በማድረግ ይህን የጥንተ አብሶ ውርስን ፡ ያስወግዳል (ዮሐ ፫ ፡ ፫—፯ ፤) ስለዚህ ሰው ሁሉ ለመዳን ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ መወለድ አለበት ።

## ጥምቀት አንዲት ናት

ምሥጢረ ጥምቀት አንድ ጊዜ ብቻ ነው ፤ አይደገምም (ኤፌ ፬ ፡ ፭) ሥጋዊ ልደት አንድ ጊዜ ብቻ እንደሆነ መንፈሳዊ ልደትም አንድ ጊዜ ብቻ ነው ፤ የጥምቀት ምሳሌ የሆነው ግዝረት አንድ ጊዜ እንደሆነ ጥምቀትም አንድ ጊዜ ይሰጣል ፤(ቈላ ፪፡ ፲፪ ፤) ጥምቀት በክርስቶስ ሞትና በትንሣኤ ተመስሎአል ፤ ስለዚህ ሞትም ትንሣኤም አንድ ጊዜ እንደ ሆነ ጥምቀትም አንድ ጊዜ ብቻ ይፈጸማል እንጂ አይደጋገምም (ሮሜ ፡ ፮ ፡ ፬።)

## ጥምቀተ ሕፃናት

ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ከክርስቲያን ቤተሰብ የተወለዱ ወንዶችን በ፵ ቀናቸው ሴቶችን በ፹ ቀናቸው እንዲጠመቁ ትፈቅዳለች ፤ የቀኑ ጉዳይ ከብሉይ ኪዳን የተወረሰ ነው ፤(ዘሌዋ ፡ ፲፪ ፩—፰) እንደዚሁም በመጽሐፈ ኩፋሌ አዳም በተፈጠረ በ፵ ቀኑ ሔዋንም በተፈጠረች በ፹ ቀንዋ ልጅነት እንደተቀበሉ ተገልጦአልና በዚያ መሠረት ወንድ በ፵ ቀኑ ሴት በ፹ ቀንዋ ይጠመቃሉ ፤ (ኩፋሌ ፬ ፡ ፱—፲፪) ።

ለሕፃናት ጥምቀት ያስፈለገበትም ምክንያት የጥንተ አብሶ ውርስ ስላለባቸው ከዚያ ለመንጻት እንዲችሉ ነው ፤ ጌታችንም ወደዚህ ዓለም የመጣው ሁሉንም ማለት ደቂቅን ፤ ሕፃናትን ፡ ወራዙትንና አዕሩግን ፡ ወንዶችና ሴቶችን ለማዳን ነው ፤ ስለዚህም ቅዱስ ያሬድ እንዲህ ይላል «እደ ወአንስተ ወሕፃናተ ከመ ይቤዙ ተወልደ ፡ ወንዶችንና ሴቶችን ሕፃናትንም ይዋጅ ዘንድ ተወለደ » (ያሬድ ሠለስት)

ከዚህም ሌላ ለጥምቀት ምሳሌ የነበረው ግዝረት ለሕፃናት ይፈጸም ነበር ፤ (ቆላ ፡ ፪ ፡ ፲፩—፲፫) በማየ ዓይኅ የዳኑት ኖኅና ልጆቹ ነበሩ (፩ ጴጥ ፫ ፡ ፳) ቀይ ባሕርን የተሻገሩ ሕፃናትም ነበሩ ፤ (፩ ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፩—፪)፤ ተስፋ መንፈስ ቅዱስ የተሰጠ ለአበው ብቻ ሳይሆን ለልጆችም ጭምር ነበር ፤ (የሐዋ ፡ ፪ ፡ ፴፰—፴፱) ቅዱሳን ሐዋርያትም ብዙ ቤተሰቦችን ከእነልጆ



www.ethiopianorthodox.org

ቻቸው ያጠምቁ ነበር (የሐዋ ፡ ፲፮ ፡ ፴፫፤ ፩ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፲፮፤ የሐዋ ፡ ፲፮ ፡ ፲፭ ፤ ፲ ፡ ፵፮—፵፰ ፤ የሐዋ ፡ ፰ ፡ ፭—፲፯)፤ እግዚአብሔር ጸጋውን ለሕፃናት አልነፈገም ፤ ኤርምያስና መጥምቁ ዮሐንስ በሕፃንነታቸው ጸጋውን አግኝተዋል ፤ (ኤር ፡ ፩ ፡ ፭ ፤ ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፲፭) ፤ በእነዚህ ምሳሌዎች መሠረት ቤተ ክርስቲያናችን ሕፃናትን ታጠምቃለች፤ ሕፃናት ያለጥምቀት እንዲሞቱ ማድረግ በክርስቲያን ወላጆች ላይ ታላቅ በደል መሆኑንም ቤተ ክርስቲያናችን ታስተምራለች ፤ ሕፃናት ከጥንተ አብሶ ውርስ በስተቀር የገቢር ኃጢአት ስለሌለባቸው በሚጠመቁበት ጊዜ ንስሓ አያስፈልጋቸውም ።

የሕፃናት ጥምቀት ፣ በወላጆቻቸው ወይም በአሳዳሪዎቻቸው ወይም በክርስትና አባትና እናታቸው እምነት ይፈጸማል ፤ የአንዱ እምነትም ሌላውን እንደሚጠቅም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወላጆቻቸው ወይም በአሳዳሪዎቻቸው እምነት ለበሽተኞች ተአምራትን ያደርግና ይፈውሳቸው ነበር ፤ (ማር ፡ ፪ ፡ ፭፤ ማቴ ፡ ፰ ፡ ፭—፲፫ ፡ ፲፭ ፡ ፳፩—፳፰) ።

<u>የተጠማቂው ግዴታ</u>

ተጠማቂው ትልቅ ከሆነ በቅድሚያ ትምህርተ ክርስትናን መማር በሚጠመቅበት ጊዜ እምነቱን ማሳወቅ (ማር ፡ ፲፮ ፡ ፲፮ ፤ ) ንስሓውን መግለጥ (የሐዋ ፡ ፪ ፡ ፴፰) አለበት ፤ የሚጠመቁት ሕፃናት ከሆኑ ግን በእነርሱ ፋንታ የክርስትና አባትና እናታቸው ሁሉን ነገር ይፈጽማሉ ።

## ፪. <u>ምሥጢረ ሜሮን</u>

ሜሮን ማለት ቅብዐት ማለት ነው ፤ ቃሉ የጽርዕ ነው ፤ በግእዝም ሆነ በአማርኛ እንዳለ ተወስዶአል ፤ ምሥጢረ ሜሮን አዲሱ ተጠማቂ በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንዲያድግና እንዲበረታ ጸጋ መንፈስ ቅዱስን የሚያሰጥ ምሥጢረ ቤተ ክርስቲያን ነው ፣ ሜሮን ከዘይት (ወይራ) ከበለስና ከተለያዩ ዕፅዋት በጳጳሳት ይፈላል (ይወጣል) ።

<u>አጀማመሩ</u>

ምሥጢረ ሜሮን ጌታ ለሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን በላከላቸው ጊዜ ተጀምሮአል ፤ (የሐዋ ፡ ፪ ፡ ፩—፬) ፤ ቀጥሎም ቅዱሳን ሐዋርያት ማንኛውንም አማኒ ከአጠመቁ በኋላ በተጠማቂው ራስ ላይ እጃቸውን በመጫን መንፈስ ቅዱስን ያሳድሩበት ነበር ፤ (የሐዋ ፡ ፲፱ ፡ ፭—፯) ፤ ያንጊዜ ቄስም ሆነ ዲያቆን ሥርዐተ ጥምቀትን ከፈጸመ በኋላ ለአንብሮተ እድ ሐዋርያ



ትን መጠበቅ ግዴታ ነበረበት (የሐዋ ፡ ፰ ፡ ፲፬—፲፯) ፤ ቤተ ክርስቲያን እየተስፋፋች በሄደች ጊዜ ግን ሐዋርያት ተጠማቂዎች ወደ አሉበት ተጠማቂዎችም ሐዋርያት ወደአሉበት ሄደው አንብሮተ እድ ለማድረግና ለመቀበል አስቸጋሪ በመሆኑ በአንብሮተ እድ ፈንታ ሜሮኑን በአንብሮተ እድ ባርከው አጥማቂው ካህን ለተጠማቂው እንዲቀባ ፈቅደዋል ። ስለ ዚህም በዚያው በዘመነ ሐዋርያት በአንብሮተ እድ ስለተተካው ምሥጢረ ቅብዐት (ሜሮን) በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅሶ ይገኛል ፤ (ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፲፫ ፤ ፬ ፡ ፴ ፤ ፪ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፳፩—፳፫ ፤ ፩ ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፳—፳፯) ።

<u>አፈጻጸሙ</u>

እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ተጠማቂው ሕፃንም ሆነ ሽማግሌ እንደተጠመቀ ሳይውል ሳያድር ሜሮን ይቀባል ፤ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ግን ለሕፃንም ሆነ ለዐዋቂ ሜሮኑን ከጥምቀት ነጥለው በማቆየት ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ ይቀባሉ ፤ እንደ እውነቱ ከሆነ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ዕድሜ አይወስነውም ፤ በማኅፀን ሳሉ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ የተቀበሉ አሉና (ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፲፭) ።

የሜሮን አቀባብ እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ግንባርን ብቻ ሳይሆን ከግንባር እስከ እግር የተወሰኑ የአካል ክፍሎች ይቀባሉ ፤ ምሥጢረ ሜሮን የሚፈጸመው ለተጠመቁ ብቻ ነው ፤ (የሐዋ ፡ ፰ ፡ ፲፬—፲፯) ፤ ምሥጢረ ሜሮንን መፈጸም የሚችሉ በመጀመሪያ ሐዋርያት ፤ ቀጥሎ ጳጳሳት ብቻ ነበሩ ፤ በኋላ ግን ሜሮን የማውጣቱ ወይም የማፍላቱ ሥልጣን ለጳጳሳት ሲሆን መቀባት ብቻ ለቀሳውስትም ተፈቅዶአል ፤ ስለዚህ ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን ቀሳውስትም ሜሮን ይቀባሉ ፤ በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ግን አሁንም ቢሆን ምሥጢረ ሜሮንን የሚፈጽሙ ጳጳሳት ብቻ ናቸው ።

<u>በምሥጢረ ሜሮን የሚገኝ ጸጋ</u>

ተጠማቂው ሜሮን በሚቀባበት ጊዜ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ይቀበላል ፤ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ በሜሮን ይረጋገጣል ፤ ለመንፈሳዊ ሕይወቱ ዕድገትንና ኃይልን ያገኛል ፤ ለዚህ ሁሉ ምሥጢረ ሜሮን እንደ ማሕተም ነው ፤ (ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፲፫ ፡ ፬ ፡ ፴) ።



www.ethiopianorthodox.org

## ፫. ምሥጢረ ቍርባን

ቍርባን ማለት መባዕ ሆኖ የሚቀርብ የሚሰጥ ማለት ነው ፤ በብሉይ ኪዳን ዘመን እስራኤላውያን ስለኃጢአታቸው ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ሁሉ ቍርባንና መሥዋዕት ይባል ነበር ፤ ቍርባን የእህሉ ፣ መሥዋዕት የእንስሳው ነው ፤ በሐዲስ ኪዳን ግን ቍርባን ወይም መሥዋዕት የሚባለው እግዚአብሔር ለሰዎች ያቀረበው ነው ፤ ከዚህም ጋር ሰዎች ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡበት እግዚአብሔርም ወደ ሰዎች የሚቀርብበት መንገድ መሆኑን ቃሉ ያመለክታል ።

ቅዱስ ቍርባን የሚባለው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ነው ፤ (፩፡ቆሮ፡ ፲፩፡ ፳፯፤) ቅዱስ ቍርባን ፡- መሥዋዕት ተብሎ ይጠራል ። (፩፡ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፯ ፤ ዕብ ፡ ፲፡ ፲፬ ።)

### አመሠራረቱ ፤

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመሞቱ አስቀድሞ በጸሎተ ሐሙስ በበዓለ ፋሲካ ቅዱስ ቍርባንን መሥርቶአል ፤ ይህንም ሦስቱ ወንጌላውያን ሁሉ አረጋግጠው ጽፈዋል ፤ (ማቴ ፡ ፳፮፤፳፮—፳፱፤ማር፡ ፲፬፡ ፳፪—፳፭ ፤ ሉቃ ፡ ፳፪ ፡ ፲፱—፳ ፤ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፳፫—፳፭ ።)

ስለ ምሥጢረ ቍርባን በብሉይ ኪዳን ምሳሌ ተመስሎአል፤ ትንቢትም ተነግሮአል ።

ምሳሌው ፡— መልከጼዴቅ ለአብርሃም ያበረከተው ኅብስትና ወይን (ዘፍ ፡ ፲፬ ፡ ፲፰) ፤ በኦሪት ዘሌዋውያን የተዘረዘሩት አምስቱ የመሥዋዕት አይነቶች (ዘሌዋ ምዕራፍ ፩፡ — ምዕራፍ ፯) እስራኤላውያን በነጻነት በዓላቸው በፋሲካ የሠውት የፋሲካ በግ፤ (ዘጸአ ፡ ፲፪ ፤ ፩ ፡ ቆሮ ፡፭ ፡ ፯) ፤ እስራኤላውያን በምድረ በዳ ለ፵ ዓመታት የተመገቡት መና ዘጸአ ፡፲፮፡ ፲፫—፲፮ ፤ ዮሐ ፡ ፮ ፡ ፶) የቅዱስ ቍርባን ምሳሌ ነበር ።

ትንቢቱም ፡— በመጽሐፈ ምሳሌ ፱፡ ፩—፮ ፤ «ጥበብ ቤትዋን ሠራች ሰባቱንም ምሰሶችዋን አቆመች ፍሪዳዋን አረደች የወይን ጠጅዋን ደባለቀች ማዕድዋን አዘጋጀች ባሪያዎችዋን ልካ በከተማይቱ ከፍተኛ ሥፍራ ላይ ጠራች ፤ ዕላዋቂ የሆነ ወደዚህ ፈቀቅ ይበል አእምሮ የጎደላቸውንም እንዲህ አለች ፤ ኑ እንጀራዬን ብሉ ፤ የደባለቅሁትንም የወይን ጠጅ ጠጡ ዕላዋቂነትን ትታችሁ በሕይወት ኑሩ» ተብሎ የተነገረውና በሌላም ክፍል ያለው ነው ።



### አፈጻጸሙ

በምሥጢረ ቍርባን አፈጻጸም ጊዜ የሚታዩ ሁለት ምልክቶች አሉ ፤ እነርሱም ኅብስትና ወይን ናቸው ፤ ኅብስቱ ከንጹሕ ስንዴ ይሠራል ፤ ስንዴው ከመጀመሪያ ጀምሮ ኅብስት እስከ ሚሆንበት ድረስ ያለው አሠራር ሁሉ ክርስቶስ ስለእኛ ለተቀበላቸው ጸዋትወ መከራ ምሳሌነት አለው ፤ ወይኑም ከንጹሕ የወይን ፍሬ (ዘቢብ ) ይዘጋጃል ፤ በወይኑና በስንዴው አንዳችም ነገር አይጨመርም ፤ ቤተ ክርስቲያናችን በማናቸውም ቦታ በሚዘጋጅና ልዩ ነገር በተጨመረበት ኅብስትና ወይን ቅዱስ ቍርባን እንዲፈጸም አትፈቅድም ።

ምሥጢረ ቍርባንን መፈጸም የሚችሉ በመጀመሪያ ሐዋርያት ነበሩ (የሐዋ - ፳ ፡ ፯) ፤ ከሐዋርያት በኋላ በእነርሱ እግር የተተኩ ጳጳሳት ምሥጢረ ቍርባንን እንዲፈጽሙ ሆነ ፤ ቤተ ክርስቲያን በየሀገሩ ከተቋቋመች በኋላ ግን ቀሳውስት ምሥጢረ ቍርባንን እንዲያከብሩና እንዲሰጡ ተፈቀደ ፤ ዲያቆናት ግን በአገልግሎት ይላላካሉ ፤ ያስተናብራሉ እንጂ ምሥጢረ ቍርባንን ለመቀደስ ሥልጣን የላቸውም ፤ እርግጥ በዕርፈ መስቀል ደሙን እንዲያቀብሉ ቤተ ክርስቲያናችን ትፈቅዳለች ።

### በምሥጢረ ቍርባን የሚገኝ የማይታይ ጸጋ ፤

በሚታየው በኅብስቱና በወይኑ የማይታየውን የክርስቶስን ሥጋና ደም እንቀበላለን ፤ ስርየተ ኃጢአትን እናገኛለን / (ማቴ ፡ ፳፮ ፡ ፳፮—፳፰) ።

ከክርስቶስ ጋር ኅብረትን እናገኛለን ፤ (ዮሐ ፡ ፮ ፡ ፶፮ ፡) ከምእመናን ሁሉ ጋርም አንድነት ይኖረናል ፤ (፩፡ ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፲፯) ፤ በሥጋውና በደሙ የዘለዓለም ሕይወትን እንወርሳለን ፤ (ዮሐ ፡ ፮ ፡ ፶፬ ፡ ፶፰) ።

### የኅብስቱና የወይኑ መለወጥ ፤

ካህኑ ነቅዕ የሌለበትን ንጹሕ ኅብስት በጻሕል እንደዚሁም የጠራውን ወይን በጽዋዕ አድርጎ ጸሎተ ቅዳሴውን ያደርሳል ፤ ከፍሬ ቅዳሴው መካከል «--- ንስእለከ እግዚኦ ወናስተበቍዐከ ከመ ትፈኑ ቅዱሰ መንፈሰ ወኀይለ ዲበ ዝንቱ ኅብስት ፤ ወላዕለ ዝንቱ ጽዋዕ ይረስዮ ሥጋሁ ወደሞ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለመ ዓለም ፡— የጌታችንና የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋውንና ደሙን



www.ethiopianorthodox.org

ያደርገው ዘንድ ቅዱስ መንፈስን ኃይልንም በዚህ ኅብስትና በዚህ ጽዋዕ እንድትልክ አቤቱ እንለምንሀለን፤እንማልድሀለን» የሚለውን ጸሎት በሚ ጸልይበት ጊዜ ፡—በግብረ መንፈስ ቅዱስ ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ አምላክ ወይኑም ተለውጦ ደመ አምላክ ይሆናል ፤ (ቅዳሴ ሐዋርያት) ኅብስ ቱና ወይኑ በሚለወጡበት ጊዜ መልካቸውና ጣዕማቸው እንዳለ ነው ፤ መለወጡን የምንመለከተው በእምነት ዓይን ነው ።

እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ትምህርተ ሃይማኖት ቅዱስ ቊርባን ፥ ፍጹም የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው እንጂ ምሳሌ አይደለም ፤ (ማቴ ፡፳፮፡ ፳፯—፳፰ ፤ ፩፡ቆሮ ፡ ፲፡ ፲፮ ፡ ፲፩ ፡ ፳፫—፳፯ ፤) እነዚህ ጥቅሶች ሁሉ የሚያመለክቱት የምንቀበለው ኅብስትና ወይን ፍጹም የክርስቶስ ሥጋና ደም መሆኑን ነው ፤ ይህን የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃል መሠረት በማድ ረግ የቤተ ክርቲያን አባቶች ኅብስቱና ወይኑ በካህኑ መሣሪያነት በመን ፈስ ቅዱስ ሥራ በቃለ እግዚአብሔር ተለውጦ የክርስቶስ ሥጋና ደም እንደሚሆን በሰፊው ተናግረዋል ፤ ጽፈዋልም ።

## ምሥጢረ ቊርባንን መቀበል የሚገባቸው ፤

በቤተ ክርስቲያናችን ትምህርተ ሃይማኖት መሠረት አምነው የተ ጠመቁ ሥጋውንና ደሙን መቀበል ይችላሉ ፤ ከዚያም በኋላ በየጊዜው ራሳቸውን በንስሐ እየመረመሩ ኃጢአታቸውን በመናዘዝ ቅዱስ ቊር ባንን እንዲቀበሉ ቤተ ክስርቲያናችን ትፈቅዳለች ፤ በንስሐ ሳይዘጋጁ በድፍረት የሚቀበሉ ቢኖሩ ግን ዕዳ እንደሚሆንባቸው ታውጃለች፤(፩፡ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፳፰—፳፱፤) ለሕፃናትም ጥምቀት እንደተፈቀደላቸው ሁሉ ቅዱስ ቊርባንንም እንዲቀበሉ ቤተ ክርስቲያናችን ትፈቅዳለች ።

ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ኅብስቱን በወይኑ ጠምተው ያቀብላሉ ፤ ቤተ ክርስቲያናችን ግን ኅብስቱን በቅድሚያ ፥ ወይኑን በኋላ ታቀብላ ለች ፥ ይህም መድኃኒታችን ለደቀ መዛሙርቱ ካደረገው ሥርዐት ጋር ይመሳሰላል ፤(ማቴ ፡ ፳፮ ፡ ፳፮—፳፰ ።)

# ፬. ምሥጢረ ክህነት

ክህነት ማለት አገልግሎት ማለት ነው ፤ በዚህም መሠረት ካህን ማለት አገልጋይ ማለት ነው ፤ ቃሉ «ኮሄን» ከሚለው ከዕብራይስጥ ቃል ጋር ተመሳሳይነት አለው ።



ምሥጢረ ክህነት ፡— ቃለ እግዚአብሔርን ለማስተማር ምሥጢ ራትን ለመፈጸምና ምእመናንን ለመምራት በጳጳሳት አንብሮተ እድና ጸሎት ለሚገባቸው የሚሰጥ ምሥጢር ነው ፤ ሰባቱን ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ለመፈጸም የሚያስችል ይህ ምሥጢረ ክህነት ነው ። (የሐዋ ፡ ፳፡ ፳፰ ።)

## አመሠራረቱ

ምሥጢረ ክህነትን የጀመረ ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ፤ ከሙታን ከተነሣ በኋላ በሚያርግበት ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን በአንብሮተ እድ ባርኮ ከዲቁና እስከ ጵጵስና ያለውን ማዕርገ ክህነት ሾሞአቸዋል ፤ (ማቴ. ፳፰ ፡ ፲፱—፳ ፤ ሉቃ ፡ ፳፬ ፡ ፶ ፤ ዮሐ ፡ ፳ ፡ ፳፩—፳፫ ፤ ኤፌ ፡ ፬ ፡ ፲፩—፲፬ ፤) ቀጥሎም ቅዱሳን ሐዋርያት ጳጳሳትን ሾመዋል፤ (የሐዋ፡ ፲፬ ፡ ፳፫ ፤ ፩፡ጢሞ . ፭ ፡ ፳፪ ፤) ከሐዋርያት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያል ተቋረጠ አንብሮተ እድ በቤተ ክርስቲያናችን አለ ፤ ጳጳሳት መሣሪያ ዎች ናቸው እንጂ ሥልጣኑን በጳጳሳት አድሮ የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ ነው ።

## የካህናት መዓርጋት

የካህናት መዓርጋት ሦስት ናቸው ፤ እነርሱም ጵጵስና ፥ ቅስናና ዲቁና ናቸው ።

፩/ **ጳጳስ** ፡— በቤተ ክርስቲያናችን ጵጵስና መሾም የሚችለው ድንግል መነኮስ ነው ፤ በሞት ወይም በበቂ ምክንያት ሚስቱ የተለየችው ካህን ቢመነኩስ ጵጵስና እንዲሾም በቤተ ክርስቲያናችን አይ ፈቀድለትም ፤ ጳጳስ በሁለት ወይም በሦስት ጳጳሳት ሊሾም ይች ላል ፤ ዕድሜው ከ፴ በላይ መሆን አለበት ፤ ጳጳስ የማስተማር ምሥ ጢራተ ቤተ ክርስቲያንን በሙሉ የመፈጸም ቤተ ክርስቲያንን የመም ራት ሥልጣን በምልዐት አለው፤ (ቲቶ፡ ፩፡ ፭፤) ሜሮን ማፍላት ጽላትና ሌሎች ሐዲሳን ንዋያተ ቅድሳትን ሁሉ የመባረክ ሥልጣን አለው ፤

፪/ **ቄስ** ፡—እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ዲያቆኑ በዲቁና ሲያገ ለግል ከቆየ በኋላ አግብቶ ወይም መንኩሶ ቅስና ይሾማል ፤ ነገር ግን ቅስና ቅድመ ጋብቻ ወይም ቅድመ ምንኩስና አይፈቀድም ቄስ በአንድ ጳጳስ በአንብሮተ እድ ይሾማል ፤(፩ ፡ ጢሞ. ፭ ፡ ፳፪ ፤



www.ethiopianorthodox.org

የሐዋ. ፲፬ ፡ ፳፫ ፤ ) ቄስ ከመሾሙ በፊት በቲቶ ፡ ፩ ፡ ፮ ፡ እንደ ተጻፈው መሆን አለበት ።

ቄስ የማስተማር ምሥጢራትን የመፈጸምና ምእመናንን የመምራት ሥልጣን ከጳጳሱ ይቀበላል ፤ ነገር ግን ሜሮን አያፈላም ክህነት አይሰጥም፤ ታቦት ፡ አዲስ ቤተ ክርስቲያንና መንበር አይባርክም ።

፫/ ዲያቆን ፡— ዲያቆን ከመሾሙ በፊት በ፩ ፡ ጢሞ. ፫ ፡ ፰—፲፫ እንደተጻፈው ሆኖ መገኘት እንዳለበት ቤተ ክርስቲያናችን ታስተምራለች ፤ እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ዲያቆን ቅድመ ጋብቻ ይሾማል ፤ በአንድ ጳጳስ በአንብሮተ እድ ይሾማል ፤ (የሐዋ. ፮ ፡ ፮) ሹመቱም ጳጳሱንና ቄሱን ለመርዳት ብቻ ነው ፤ ዲያቆን ምሥጢራትን መፈጸም አይችልም ፤ ነገር ግን ማንበብ ማስተማርና መስበክ ለዲያቆናት ይፈቀድላቸዋል ። (የሐዋ ፡ ፮ ፡ ፫—፮) ።

በ፩፡ ጴጥሮስ ፪ ፡ ፱—፲ ላይ ያለውን ቃል በመመልከት ክህነት ለሁሉም ማለት በክርስቶስ ላመኑ ሁሉ ለወንዶችም ለሴቶችም ይገባቸዋል፤ የሚሉ አሉ ፤ ይህንም የመሰለ ቃል በብሉይ ኪዳን በኦሪት ዘጸአት ፲፱ ፡ ፮ ፡ ላይ ይገኛል ፤ ይሁን እንጂ በዚያ ጊዜም እስራኤላውያን ሁሉ ካህናት አልነበሩም ፤ የብሉይ ኪዳን ካህናት የተለዩ ነበሩ ፤ ክህነት ይገባናል ብለው በድፍረት የተነሡ ቢኖሩም ተቀጥተዋል (፪፡ዜና ፡ ፳፮ ፡ ፲፮ ፤ ዘኁል. ፲፮)፤ የቅዱስ ፡ ጴጥሮስም ቃል የሚያመለክተው መሥዋዕተ ስብሐት ለማቅረብ የሚያስችለውን ሀብት መንፈሳዊ ነው እንጂ በጅምላ ሁሉም ከዲቁና እስከ ጵጵስና ማዕርግ አላቸው ለማለት አይደለም ፤ ጌታችንም በተለይ ለሐዋርያት የሰጠውን ሥልጣን ለተከታዮቹ ሁሉ አልሰጠም ፤ (ሉቃ ፡ ፮ ፡ ፲፪—፲፫ ፤ ማቴ ፤ ፲፰ ፡ ፲፰ )።

## ፭ ምሥጢረ ንስሐ

ንስሐ መጸጸት ከኃጢአት መመለስ ፡ ራስን ማደስና መለወጥ ማለት ነው ፤ ንስሐ ተነሳሒው በአናዛዡ ካህን በኩል ከራሱ ከእግዚአብሔር በእውነተኛ ኀዘን ሥርየተ ኃጢአትን የሚቀበልበት ምሥጢር ነው ።

ከአዳም የተወለደ ሁሉ ከአዳም በተወረሰው የኃጢአት ዘርዕ ምክንያት የኃጢአት ዝንባሌ አለበት ፤ ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ሲያስረዳ እንዲህ ይላል «- - - እኔ ግን ከኃጢአት በታች ልሆን የተሸጥሁ የሥጋ ነኝ ፤ - - - የማልወደውን የማደርግ ከሆንኩ ግን ያን የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም በእኔ የሚኖር ኃጢአት ነው እንጂ» (ሮሜ ፡ ፯፡ ፲፬—፲፰ )፤



ስለዚህ ሰው ከጥምቀት በፊት የሠራው ኃጢአት ሁሉ በጥምቀት ይሰረይለታል ፤ ከጥምቀት በኋላ የሠራው ኃጢአት ግን በንስሐ ይሰረይለት ዘንድ እግዚአብሔር ምሥጢረ ንስሐን ለሰው ልጆች ሰጥቶአል ።

### አመሠራረቱ

ምሥጢረ ንስሐን የመሠረተ ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ ከትንሣኤው በኋላ ሥልጣነ ክህነትን ለሐዋርያት በሰጣቸው ጊዜ ምሥጢረ ንስሐን መሥርቶአል(ዮሐ፡፳፡፳፩—፳፫)፤ ከዚያም አስቀድሞ ኃጢአተኛውን ከኃጢአቱ መፍታትና ማሠር እንደሚችሉ በነገራቸው ጊዜ የምሥጢረ ንስሐን ተስፋ ሰጥቶአቸው ነበር (ማቴ ፡ ፲፮ ፡ ፲፱ ፤ ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፲፰)፤ በመሠረቱ ኃጢአትን የማስተስረይ ኃይል ለጌታችን ብቻ ነው (ሉቃ ፡ ፭ ፡ ፳) ፤ ነገር ግን ይህን ኃይል ራሱ ጌታችን ለሐዋርያት ሰጣቸው ፤ በሐዋርያትም በኩል ለጳጳሳትና ለቀሳውስት ተሰጣቸው (ዮሐ ፡ ፳ ፡ ፳፩—፳፫)።

### አፈጻጸሙ

ምሥጢረ ንስሐን መፈጸም የሚችሉ ጳጳሳትና ቀሳውስት ብቻ ናቸው ፤ እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ተነሳሒውና ካህኑ ብቻቸውን ሆነው ይፈጸማል ፤ ተነሣሒው ማለት ኃጢአተኛው ስለሠራው ኃጢአት ከፍተኛ ጸጸት ፥ ልባዊ ኑዛዜ መናዘዝ ፤ ወደ ሠራው ኃጢአት እንደገና ላይመለስ መወሰን በክርስቶስ ጽኑዕ እምነት በምሕረቱም ፍጹም ተስፋ ማድረግ አለበት ።

እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት ኃጢአትን ለካህን አምኖ መናዘዝ ያስፈልጋል ፤ ካህኑም ኑዛዜውን በምሥጢር መጠበቅ አለበት ፤ ኑዛዜ ራስን በካህኑ ፊት መክሰስና መውቀስ ማለት ነው ፤ ኑዛዜ ኃጢአተኛውን በሠራው ኃጢአት እንዲገሥጽ እንዳይመለስበትና እንዲያፍርበት ያደርገዋል ፤ ስለ ኑዛዜ መጻሕፍት ቅዱሳት በሰፊው ይናገራሉ ፤ (የሐዋ ፡ ፲፱፡ ፲፰ ፤ ያዕ ፡ ፭፡ ፲፮ ፤ ፩፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፱ ) ፤ ንስሐ መግባት የሚገባው ኃጢአትን በተገነዘበ ጊዜና ቅዱስ ቍርባን ከመቀበል በፊት ነው ።

### በምሥጢረ ንስሐ የሚገኝ ጸጋ

ተነሳሒው በመምህረ ንስሐው ፊት ቀርቦ ኃጢአቱን በሚገባ ከተናዘዘ በኃጢአቱ ካለቀሰ ስርየተ ኃጢአትን ያገኛል ፤ ከእግዚአብሔር



www.ethiopianorthodox.org

ጋር ይታረቃል ፤ የነፍስ ሰላምንና ዕረፍትን ያገኛል ፤ በድሎ የነበረው እንዳልበደለ ይሆናል ፤ ፍጹም ተሐድሶና ለውጥን ያገኛል ።

## ካህኑ ለተነሳሒው የሚሰጠው ቅጣት (ቀኖና)

ተነሳሒው የኃጢአቱን ክብደት እንዲያስታውስ ካህኑ፡ —ጾም ለተወሰነ ጊዜ እንዲጾም እንዲጸልይ ምጽዋት እንዲሰጥ ከምሥጢራት እንዲከለከል ያዝዘዋል ፤ ይህም በጌታችንና በሐዋርያት ታዝዞአል ፤ (ማቴ ፡ ፲፮ ፡ ፲፱ ፤ ፩ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፬—፭) ።

ይህ የሚሆንበት ምክንያት ተነሳሒው ኃጢአቱ ምን ያህል አሳዛኝና ከባድ መሆኑን እንዲረዳ ፣ ነፍሱን ለማንጻት እንዲችል ሌሎች ቅጣት መቀበሉንና መመለሱን ተመልክተው እንዲቀበሉት ፤ (፪ ፡ ቆሮ ፡ ፪ ፡ ፮—፰ ፤) እርሱንም አይተው እንዲገሡጹ (፩፡ ጢሞ፡ ፭ ፡ ፳ ፡ ) ነው ።

# ፮. ምሥጢረ ተክሊል

ተክሊል የሚለው ቃል ለሙሽሮች በጋብቻቸው ጊዜ የሚፈጸመውን ሥርዐት ፣ ቃል ኪዳንና የሚቀዳጁትን አክሊል የሚለብሱትንም ልብሰ መርዓ የሚያመለክት ነው ፤ ምሥጢረ ተክሊል ሙሽራውንና ሙሽሪትን አንድ የሚያደርግ መለኮታዊ ጸጋን የሚያሰጥ የጋብቻን አንድነት የሚያጸና ምሥጢር ነው ፤ ጋብቻ ወይም ምሥጢረ ተክሊል ከሌሎች ምሥጢራት ተለይቶ ምሥጢራዊና ተፈጥሮታዊ ነው ፤ ምሥጢራዊ መባሉ ጸጋ እግዚአብሔር ስለሚሰጥበት ነው ፤ ተፈጥሮታዊ መባሉም ማንም በተፈጥሮ ባሕርዩ ስለ ሚፈጽመው ነው ።

## አመሠራረቱ

እግዚአብሔር በጥንተ ፍጥረት የመጀመሪያውን ሰው በፈጠረ ጊዜ «ሰው ብቻውን ይኖር ዘንድ መልካም አይደለም ረዳትን እንፍጠርለት እንጂ» ብሎ ሔዋንን በመፍጠሩ ቅዱስ ጋብቻን መሥርቶአል ፤ (ዘፍ ፡ ፪ ፡ ፲፰—፳፬ ፤) ቀጥሎም «ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉዓት -» በማለት የሁለቱን አንድነት ባረከ ፤ ( ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፳፰ ።)

ነገር ግን ይህ አንድነት በኃጢአት ምክንያት ረክሶ ስለነበር በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እንደገና ታደሰ ፤ ራሱ ጌታችን በቃና ዘገሊላ በተደረገው ሠርግ ተገኝቶ ውሃውን ወደ ወይን በመለወጥ ጋብቻን አከበረ ፤ (ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፩—፲፩) ።



## የጋብቻ ዓላማ

ሀ. የሰው ዘርዕ እንዳይቋረጥ ዘርዕ ለመተካትና ምድርን ለመሙላት ነው ፤ (ዘፍ፡ ፩ ፡ ፳፯—፳፰ ፤) በዚህም ዓላማው ጋብቻ የእግዚአብሔር የሥራው ኅብረት ነው ፤ ጋብቻ ለማኅበረ ሰብእ (ለሀገር) ለመንግሥተ እግዚአብሔር አስፈላጊ ነው ፤ ጋብቻን መቃወም ራስን ኅብረተ ሰብእን እግዚአብሔርንም መቃወም ነው ።

ለ. የባሕርይ ፍትወትን ለማራቅ ነው ፤ (፩፡ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፰—፱ ፤ ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፲፩ ፤)

ሐ. ሰው ብቻውን መኖር ስለማይገባው ፣ እርስ በርስ በመረዳዳት ለመኖር ነው ፤ (ዘፍ ፡ ፪ ፡ ፲፰ ።)

## አፈጻጸሙ

ምሥጢረ ተክሊል በቤተ ክርስቲያን እንጂ በሌላ ቦታ አይፈጸምም ፤ በቄስ ወይም በጳጳስ ይፈጸማል ፤ ተክሊል በድንግልና ኖረው ለሚጋቡ እንጂ ለፈቶች አይደረግም ፤ በክርስትና ሃይማኖት ሥርዐት ፡ ጋብቻ አንድ ወንድ ለአንድ ሴት አንዲት ሴት ለአንዲት ወንድ እንጂ ብዙ ሴቶች ለአንድ ወንድ ብዙ ወንዶችም ለአንዲት ሴት አይፈቀድም ፤ ስለዚህ ከአንዲት ሴት በላይ ወይም ከአንድ ወንድ በላይ ለሚያገቡ ምሥጢረ ተክሊል አይፈጸምም ።

## የተጋቢዎች ግዴታ

የሚጋቡት ሁለቱም የተዋሕዶ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባላት መሆን አለባቸው ፤ ጋብቻን የሚከለክል ሥጋዊና መንፈሳዊ ዝምድና የአካልና የአእምሮ ጉድለት ከመጠን በላይ የሆነ የዕድሜ መበላለጥ መኖር የለበትም ፤ የወላጆች ፈቃድ ብቻ ሳይሆን የተጋቢዎቹም ፈቃድ እንዲሆን ያስፈልጋል ።

## በምሥጢረ ተክሊል የሚገኝ ጸጋ

ምሥጢረ ተክሊል የሙሽራውንና የሙሽራይቱን ባሕርያዊ አንድነት ወደ ንጹሕ መንፈሳዊ አንድነት ይለውጣል ፤ እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ትምህርት ጋብቻ የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያኑ አንድነት ምሳሌ ነው ፤ በመሆኑም የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን አንድነት ለዘለዓለም እን



www.ethiopianorthodox.org

ደሆነ ባልና ሚስት ሳይለያዩ እንዲኖሩ የሚያስችል መንፈሳዊ ኃይልንና አንድነትን በምሥጢረ ተክሊል ያገኛሉ ፤ (ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፴፩ ።)

ጋብቻ ከሁለቱ አንዱ ካልሞተ ወይም አመንዝራ ካልሆነ በቀር አይፈርስም ፤ «እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው ሊለይ አይገባ ውም ። (ሮሜ ፡ ፯ ፡ ፪—፫ ፤ ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፮ ፤)

## ፯ ምሥጢረ ቀንዲል

ምሥጢረ ቀንዲል የታመሙ ምእመናን በቅብዐ ቅዱስና በቀሳው ስት ጸሎት ለነፍና ለሥጋ ፈውስ የእግዚአብሔርን ጸጋ የሚቀበሉበት ምሥጢር ነው ።

ቀንዲል መብራት ማለት ነው ፤ ምሥጢረ ቀንዲል በሚደረግበት ጊዜ ሰባት መብራት ይበራል ፤ ስለዚህ ስያሜው ከሥርዐቱ አፈጻጸም ተወስዶአል ፤ ከዚህም ጋር የጥንት ቤተ ክርስቲያን የምትጠቀምበት መብራት የዘይት ቅብዐት ነውና ቅብዓ ዘይቱ በግብሩ ቀንዲል ተብሎአል ።

### አመሠራረቱ ፤

ከትንሣኤ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን በላ ካቸው ጊዜ ድውይ የመፈወስን ኃይል ሰጥቶአቸዋል ፤ (ማር፡፲፮፡፲፯—፲፰፤) ከዚያም በፊት በጥንተ ስብከት ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ በየከተማው በላካቸው ጊዜ ድውያንን በዘይት እየቀቡ ይፈውሱ ነበር ፤ (ማር፡ ፮፡ ፲፫ ።) ከዚያ በኋላ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የምሥጢሩ መጋቢዎች ፤ እን ደመሆናቸው በትእዛዙ መሠረት ሲሠሩበት ኖረዋል ፤ (፩፡ ቆሮ፡፬፡ ፩፤) ቀጥሎም ቀሳውስት በዘይት እየቀቡና እየጸለዩ ሕሙማንን እንዲፈውሱ ሐዋርያት አዝዘዋል ፤ (ያዕ፡ ፭፡ ፲፬—፲፭ ፤) እስካሁንም ድረስ ከሐዋርያት ሲያያዝ በመጣው ትውፊት መሠረት ቤተ ክርስቲያናችን በምሥጢረ ቀንዲል ትገለገላለች ።

### አፈጻጸሙ ፤

ምሥጢረ ቀንዲል የሚፈጸመው በንጹሕ የወይራ ዘይት ነው ፤ ቅብዐ ዘይቱ በጳጳስ ይባረካል ፤ በቄስም ሊባረክ ይችላል ፤ ምሥጢረ ቀንዲል በጳ ጳስ ወይም በቄስ በቤተ ክርስቲያን ወይም በመኖሪያ ቤትና በሆስፒታል ሊፈጸም ይችላል ፤ በሽተኛው ከመቀባቱ በፊት ኃጢአቱን ይናዘዛል ።



### በምሥጢረ ቀንዲል የሚገኝ ጸጋ ፤

በሽተኛው ቀንዲል ሲቀባ በሥጋዊ ደዌ ደክሞ የነበረው መንፈሳዊ ኃይሉ ይበረታል ፤ ሥጋና መንፈስ አንድ ስለሆኑ የአንዱ ሌላውን ይሰ ማዋል፤ ሥጋ ቢደክም መንፈስም ይደክማል ፤ መንፈስ ሲጠነክር ደግሞ ሥጋም ይጠነክራል ፤ የመንፈስ ኃይል የሥጋን ድካም ያስወግዳል ፤ ከዚህም ጋር በምሥጢረ ቀንዲል በሽተኛው ስርየተ ኃጢአትን ያገ ኛል ፤ ይህም ኑዛዜ ሲጨመርበት ነው ።

አንዳንድ ሊቃውንት «ምሥጢረ ቀንዲል የሚፈጸመው ለሥጋዊ ፈውስ ከሆነ ምሥጢር መባል የለበትም» ይላሉ ምክንያታቸውንም ሲሰጡ ምሥጢር መባል የሚገባው መንፈሳዊውን ጸጋ ብቻ የሚያስ ጠው ነው ይላሉ ፤ ቤተ ክርስቲያናችን ግን ምሥጢረ ቀንዲል ለሥጋም ለነፍስም ፈውስ የሚገኝበት ምሥጢር መሆኑን ታምናለች ።

ምሥጢረ ቀንዲል ለሞት መዘጋጃ እንደሆነ የሚያምኑ አሉ ፤ እን ደዚህ የሚሉ ክፍሎች ምሥጢረ ቀንዲል በሽተኛው ሊሞት ሲያጣጥር ይፈጽሙለታል ፤ እንደነርሱ ሥርዐት ምሥጢረ ቀንዲል የሚፈጸመው አንድ ጊዜ ብቻ ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ግን ምሥጢረ ቀንዲል ለደዌ ሥጋም ለደዌ ነፍስም እንደሚበጅ ታምናለች ፤ ስለዚህም ምእመናን በታመሙ ጊዜ ሁሉ ምሥጢረ ቀንዲልን ትፈጽምላቸዋለች ።

ምሥጢረ ቀንዲል በ፩፡ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፳፰ ላይ ከተጠቀሰው ሀብተ ፈውስ የተለየ ነው ፤ ማንኛውም ጳጳስ ወይም ቄስ ምሥጢረ ቀንዲልን ለመፈ ጸም ሥልጣን አለው ፤ «ሀብተ ፈውስ» የሚባለው ግን ለተለዩ ሰዎች ነው ፤ የተለዩ ከተባለም ለካህን ወይም ካህን ላልሆነ ሊሰጥ ይችላል ።



www.ethiopianorthodox.org

## ፲፫ | ትንሣኤ ሙታን የክርስቶስ ዳግም ምጽአትና

## የመጨረሻው ፍርድ ።

የዚህ ዓለም ፍጻሜ በሚሆንበት ጊዜ በተከታታይ የሚፈጸሙ ነገሮች አሉ ፤ እነርሱም የሙታን ትንሣኤ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት የመጨረሻው ፍርድና የዘለዓለም ሕይወት ናቸው ፤ እነዚህም ነገሮች በቅዱሳት መጻሕፍት በሃይማኖት ቀኖና በትምህርተ አበውም ተረ ጋግጠው ተነግረዋል ።

### ፩/ ትንሣኤ ሙታን

ሞት የሰው ፍጻሜ አይደለም ፤ ከጊዜያዊ ሕይወት ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት መሸጋገሪያ ነው እንጂ ፤ ዛሬ ፈርሶ በስብሶ ዐፈር ሆኖ ያለው የሰው ሥጋ ከነፍስ ጋር ተዋሕዶ ይነሣል ፤ ቀድሞ ሥጋን ከመሬት ወስዶ ነፍስንም እምኀበ አልቦ አምጥቶ አዋሕዶ ሰውን የፈጠረ አምላክ ኋላ ነፍስን ካለችበት ሥጋንም ከመቃብር እንደገና ሰብስቦ ሕይወት ሰጥቶ ማንሣት አይሳነውምና ።

በመጀመሪያ እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን ሕያዊት (የማትሞት) ነፍስን ሲሰጣቸው ሥጋቸውም የማይሞት ነበር ፤ ነገር ግን በሰይጣን ምክር በኃጢአት በወደቁ ጊዜ ሞት ተፈረደባቸው ፤ ይሁን እንጂ ሰው በሕይወት እንዲኖር የነበረው የእግዚአብሔር ዓላማ በሰይጣን አልተደ መሰሰም ፤ ሰው ከሞተ በኋላ ተነሥቶ ለዘለዓለም እንዲኖር እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ ትንሣኤ ዘጉባኤን መደበ ።

ስለዚህ የዛሬው ሕይወት ጊዜያዊ ነው ሞትም ጊዜያዊ ነው በመ ጨረሻ ጊዜ ዘለዓለማዊ ሕይወት ብቻ ይኖራል ።

ሥጋ አሁን ባለው መልኩ አይነሣም ትንሣኤ በተሐድሶ ነውና ጉድለት ያለበት አካል ሁሉ በጉድለቱ አይነሣም በትንሣኤ ጊዜ ረዥ ምና አጭር ቀይና ጥቁር አይኖርም፤ዛሬ ያለው የሥጋ ፍላጎት ሁሉ ያንጊዜ አይኖርም ፤ ማግባት መጋባት አይኖርም ፤ ከትንሣኤ በኋላ ሰዎች ሁሉ እንደ መላእክት ሆነው ይኖራሉ ፤ ( ማቴ ፡ ፳፪ ፡ ፴ ፤) ዛሬ ነፍስ በሥጋ እንዳለች ሁሉ ኋላ ሥጋ በነፍስ ይኖራል ።

ትንሣኤው በተሐድሶ ቢሆንም የሚነሣው ያው ቀድሞ የነበረው አካል ነው ፤ ዛሬ መልካም ሥራ ያልሠራ ሌላ አካል ተነሥቶ ዋጋ አይቀ በልም ፤ እንደዚሁም ዛሬ ክፉ ያልሠራ ሌላ አዲስ አካል ተነሥቶ ቅጣት አይቀበልም ፤ ስለዚህ መልካምም ሆነ ክፉ ሥራ የሠራው አካል ይነሣል ፤

ትንሣኤ ሙታን በብሉይና በሐዲስ ኪዳናት ተረጋግጦ ተነግሮአል ። (ኢሳ፡ ፳፮ ፡ ፫ ፡ ዳን፡ ፲፪ ፡ ፪፡) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ሙታ ንን በራሱ ትንሣኤ አረጋግጦአል ፤ (ሮሜ ፡ ፬ ፡ ፳፭ ፡) በቃሉም ትንሣኤ ሙታንን አጽድቆ ተናግሮአል፤ (ዮሐ፡ ፭፡ ፳፭—፳፱ ፡ ፮ ፡ ፴፱ ፤ ፵—፵፬ ፡ ፲፩ ፡ ፳፬—፳፭ ፤) ሐዋርያትም ትንሣኤ ሙታንን ሰብከዋል ፤ (የሐዋ. ፬. ፩. ፤ ፩. ቆሮ. ፲፭. ፩. ተሰ. ፬. ፲፫. — ፲፯. ፤ ራእ. ፳ ፡ ፲፫ ፤ የሃይማኖታችንም ቀኖና የመጨረሻው ክፍል «ወንሴፎ ትንሣኤ ሙታን የሙታንን ትንሣኤ ተስፋ እናደርጋለን» በማለት የሰው ልጅ ዋና ተስ ፋው ከሞት በኋላ ሕይወት ከመቃብር ባሻገር ትንሣኤ መኖሩን ማመን እንደሆነ ያስረዳል ።

### የትንሣኤ ዓይነት ፤

የሰው ዘር ሁሉ በምንም ዓይነት ሞት ቢሞት ይነሣል ፤ ሙታን ሁሉ ክርስቶስ እንደተነሣ ይነሣሉ ፤ (ሮሜ፡ ፰ ፡ ፳፫ ፤ ፩ ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፲፫—፳ ፤) ጻድቃንም ኃጥኣንም ይነሣሉ ፤ (ማቴ፡ ፳፭፡ ፴፩—፵፤) ሁሉም መለከት በተነፋ ጊዜ ይነሣሉ ፤ (፩ ቆሮ. ፲፭ ፡ ፶፪ ፤ ፩ ተሰ. ፬ ፡ ፲፮፤) ነገር ግን ትን ሣኤው የተለያየ ነው ፤ የጻድቃን ትንሣኤ የክብር ነው ፤ የኃጥአን ትን ሣኤ ግን የሃሳር ነው፤( ዮሐ. ፭. ፳፭—፳፱፤)ጻድቃን ፈጣሪያቸው ክርስቶስን መስለው ይነሣሉ ፤ ኃጥአን ግን አለቃቸው ሰይጣንን መስለው ይነሣሉ ።

### የትንሣኤ ጊዜ

ትንሣኤ ሙታን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ በሚመጣበት ጊዜ ይሆናል ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤና ዳግም ምጽአት የተያያዙ ናቸው ፤ በመ ካከል የሚሆን ሌላ ጣልቃ ነገር አይኖርም ።

ትንሣኤ ሙታን አንድ ጊዜ ነው ፤ ስለዚህም ራሱ ጌታችን በመከር መስሎ አስተምሮአል ፤ መከሩ አንድ ጊዜ እንደሆነ ትንሣኤ ሙታንም አንድ ጊዜ ብቻ ይሆናል ፤ በሕይወት የሚቆዩት ግን ጌታ በሚመጣበት ጊዜ ወዲያውኑ ይለወጣሉ ፤ (፩ ተሰ. ፬ ፡ ፲፯—፲፯፤) ከትንሣኤ ሙታን ቀጥሎ ወዲያው ጌታችን ይመጣና የመጨረሻ ፍርድ ይሰጣል ፤ ከዚያም የዓለም ፍጻሜ ይሆናል ።



www.ethiopianorthodox.org

## ፪/ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ፤

ቀድሞ ሥጋ ለብሶ ሰው ሆኖ በትሕትና መጥቶ የነበረው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዓለም ፍጻሜ ጊዜ ዳግመኛ በክብር ይመጣል ፤ ዳግም ምጽአቱ ከቀዳማዊ ምጽአቱ ይለያል ፤ ቀዳማዊ ምጽአቱ በትሕትና ነበር ፤ ዳግም ምጽአቱ ግን በግርማ ይሆናል ፤ ቀዳማዊ ምጽአቱ «ንስሑ» እያለ ለማስተማር ነበር ፤ ዳግም ምጽአቱ «ሑሩ» ና «ንዑ» ብሎ ለመ ፍረድ ይሆናል ።

የክርስቶስ ቀዳማዊ ምጽአቱ አስቀድሞ በብሉይ ኪዳን ተነግሮ እንደ ነበር ዳግም ምጽአቱም በሐዲስ ኪዳን ተነግሮአል ።

ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ዳግም ምጽአቱ ደጋግሞ ተና ግሮአል . (ማቴ፡ ፳፬ . ፴ ፤ ፳፭ . ፲፬ ፤ ፳፮ . ፷፬ ፤ ዮሐ. ፲፬ . ፫ .) መላእክ ትም «ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲያርግ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል» በማለት ዳግመኛ ተመልሶ መምጣቱን በግልጥ አስረድተዋል ፤ (የሐዋ፡ ፩ . ፲፩) ቅዱስ ጳውሎስና ሌሎች መልእ ክታትን የጻፉ ሐዋርያትም ስለክርስቶስ ዳግም ምጽአት ሰፋ አድርገው ጽፈዋል፤ (፩.ተሰ.፬. ፲፭—፲፯፤ ፪፡ ተሰ.፩፡፯—፰ ፤ ቲቶ ፡ ፪ ፡ ፲፫፤ ፩፡ ቆሮ . ፩ ፡ ፰ ፤ ዕብ ፱ ፡ ፳፰ ፤ ፩፡ ጴጥ . ፩ ፡ ፲፯ ፤ ፩ ዮሐ . ፪ ፡ ፳፰ ፤ ያዕ . ፭ ፡ ፯ ፤ ይሁዳ ፡ ፲፬ )፤ በሃይማኖታችንም ቀኖና «በሕያዋንና በሙታን ይፈርድ ዘንድ ዳግመኛ በክብር ይመጣል» በተባለው መሠረት ምጽአቱ ዘወትር ሲታሰብ ይኖራል ፤ በጸሎተ ቅዳሴም «ሞትህንና ቅድስት ትንሣኤህን ዳግመኛ መምጣትህንም እንናገራለን» እያለች ቅድስት ቤተ ክርስቲያ ናችን ሁልጊዜ ታውጃለች ።

### የዳግም ምጽአቱ ምልክቶች

ጌታችን ዳግመኛ ከመምጣቱ በፊት መምጣቱ የተቃረበ መሆኑን የሚገልጡ ምልክቶች በዓለም እንደሚታዩ ቅዱሳት መጻሕፍት ይናገ ራሉ ፤ ምልክቶች እንደ ሬታውራሪ ሆነው መምጣቱን ያሳውቃሉ ፤ ከምልክቶቹ አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው ።

ሀ. ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል ፤(ማቴ . ፳፬ ፡ ፲፬፤ ማር . ፲፫ ፡ ፲)፤

ለ. እስራኤላውያን ሁሉ ለመዳን ያምናሉ ፤(ሮሜ ፡ ፲፩ ፡ ፳፭ ) ።

ሐ. ሐሳዊ መሢሕ በሐሳውያን ነቢያትና መሢሓን አድሮ በሰ ይጣን ኃይል ታአምራት እያደረገ ይመጣል ፤ ሕዝብን ያስ ታል ፤ ማቴ . ፳፬ ፡ ፭—፲፩ ፤ ፪፡ ተሰ . ፪ ፡ ፫—፬ ፤ ፩ ዮሐ . ፪ ፡ ፲፰—፳፪ ።



መ. ዓመፅ ይበዛል ፍቅር ይቀዘቅዛል፤ (ማቴ . ፳፬፡ ፲፪፤) ከዚያ በፊት ያልሆነ ወደፊትም የማይሆን ታላቅ መከራና ሁከት ይሆናል ፤ (ማቴ . ፳፬ ፡ ፳፩፤) ረኃብ ጦርነት ፍርኃትና ሽብር የመሬትና የሰማያት መናወጥ ይሆናል ፤ (ማቴ . ፳፬ ፡ ፳፱—፴ ፤ ማር. ፲፫ ፡ ፳፬—፳፭ ፤ ሉቃ. ፳፩፡ ፳፭—፳፯) ፤ ፀሐይና ጨረቃ ይጨል ማሉ ከዋክብት ይረግፋሉ በሰማይ ላይ ምልክት ይታያል ፤ (ማቴ፡ ፳፬ ፡ ፳፱—፴)፤ በመጨረሻ ጊዜ በሰማይ ላይ የሚታየው ምልክት መስቀል እንደሚሆን የሐዲስ ኪዳን ሊቃውንት ይተ ረጕማሉ ፤ ከእነዚህ ምልክቶች ሁሉ በኋላ ክርስቶስ በደመና መጥቶ ይታያል ።

### የመምጣቱ ጊዜ

ክርስቶስ ዳግመኛ የሚመጣበት ዓመትና ወር ዕለትና ሰዓት ፈጽሞ አይታወቅም ቅዱሳት መጻሕፍትም ስለዚህ አይነግሩንም ፤ ጊዜው ሲደርስ እንደ ሚሆን ከማመንና ተዘጋጅቶ ከመጠበቅ በቀር የመምጣቱ ዘመንና ወራት ፤ ዕለትና ሰዓት ነገር ምሥጢር ነው ፤ ከአብ በቀር ማንም አያውቀ ውም መላእክት አያውቁትም (ማቴ. ፳፬ ፡ ፴፮ ፤ ማር. ፲፫፡ ፴፪ )፤ የሰው ልጆ ችም ማለት ሐዋርያትም አያውቁትም (የሐዋ ፩ ፡ ፯) ።

ነገር ግን ጊዜው የተቃረበ መሆኑ ተገልጦአል ፤ ይህም ማለት ቢዘ ገይም እንኳ የማይቀር መሆኑን ያስረዳል ፤ (ዕብ.፲ ፡ ፳፭ ፤ ያዕ. ፭፡ ፱ ፤ ፩ ፡ ጴጥ. ፬ ፡ ፭) ።

### የአመጣጡ ሁኔታ ፤

ጌታችን በሚመጣበት ጊዜ ሁሉም እንዲያየው በክበበ ትስብእት ይመጣል ፤(ማቴ. ፳፬፡ ፴ ፤ የሐዋ.፩ ፡ ፲፩ ፤ ቲቶ ፪ ፡ ፲፫ )፤ ሊቃነ መላእክት የመምጣቱን ዐዋጅ በመለከት ያሰማሉ ፤ (፩ ፡ ተሰ ፬ ፡ ፲፯)፤ ሠራዊተ መላእ ክት አጅበውት ይመጣሉ፤ (፪፡ ተሰ. ፩፡ ፯) ፤ የተሰቀለበት መስቀል በሰማይ ላይ ይታያል ፤ (ማቴ.፳፬ ፡ ፴)፤የሰው ልጅ ምልክት የተባለ መስቀል ነውና ።

### የመምጣቱ ዓላማ ፤

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የቀዳማዊ ምጽአቱ ዓላማ ሥጋ ለብሶ ሰው ሆኖ ወንጌልን አስተምሮ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሙቶ ተነሥቶ



www.ethiopianorthodox.org

ሰውን በኃጢአት ምክንያት ከመጣበት የሞት ፍርድ ለማዳን ነበር ፤ ነገር ግን ዳግመኛ የመምጣቱ ዓላማ «በሕያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድ» ይሆናል ፤ ከትንሣኤ ዘጉባኤ በኋላ ክርስቶስ በክብር ተገልጦ ሁሉም እያዩት በገሀድ ይፈርዳል ፤ (ማቴ ፳፭ ፡ ፴፩=፵፮) ።

ዛሬ በሞት ጊዜ ያለው ፍርድ ጊዜያዊ ከመሆኑም በላይ ግላዊ ነው ፤ ፍርድ ከሚቀበለው ግለሰብና ከእግዚአብሔር በቀር በመካከል የሚያይ ሌላ የለም ፤ በመጨረሻው ቀን ግን እያንዳንዱ ሰው በዐደባባይ በሁሉም ፊት ይፈረድበታል ፤ ይህም የሚሆነው አንዱ ሌላውን ምን ያህል እንደበደለ ያውቅ ዘንድ ነው ፤ (ራእ ፡ ፳ ፡ ፲፪) ።

በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ቀድሞ በዚህ ዓለም በሥጋ የጀመረው የአድኅኖት ሥራ የቤተ ክርስቲያንም ክብር በምልዐት ይፈጸማል ፤ ምክንያቱም ዛሬ በሃይማኖተ ወንጌል በምግባረ ወንጌል ጸንተው የኖሩ ጻድቃን በዳግም ምጽአቱ ጊዜ «ንዑ ኅቤየ ቡሩካኑ ለአቡየ ትረሱ መንግሥተ ሰማያት የአባቴ ቡሩካን መንግሥተ ሰማያትን ትወርሱ ዘንድ ወደ እኔ ኑ» ተብለው ወደ ዘለዓለም የደስታ ሕይወት ይሄዳሉ ፤ በዚያም ሁል ጊዜ እግዚአብሔርን እያዩ በክብር ይኖራሉ ፤ ነገር ግን ክብራቸው እንደ ሥራቸው ይለያያል ፤ (፩ ቆሮ ፲፭ ፡ ፵—፵፩) ።

ዛሬ ከሃይማኖተ ወንጌል ከምግባረ ወንጌል ወጥተው የኖሩ ኃጥአን ደግሞ «ሑሩ እምኔየ ርጉማን ውስተ እሳት ዘለዓለም እናንተ የተረገማችሁ ከእኔ ተለይታችሁ ወደ ዘለዓለም እሳት ሂዱ» የሚል ፍርድ ተፈርዶባቸው በማያቋርጥ የቅጣት ሕይወት ይኖራሉ ፤ (ማቴ.፳፭ ፡ ፵፩=፵፮ ፤ ዮሐ. ፲፯፡፴፩ ፤ ፡ሮሜ ፪ ፡ ፲—፲፯) ።

በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ጊዜ ሞት ይጠፋል ፤ ሰይጣንም ለዘለዓለም ይታሠራል ፤ ሕይወት ብቻ ለዘለዓለም ይቀጥላል (፩ ቆሮ. ፲፭ ፡ ፶፭—፶፯ ዕብ.፪ ፡ ፲፬ ፤ ራእ. ፳ ፡ ፲—፲፭ ፡ ፳፪ ፡ ፲፪ ) ።



www.ethiopianorthodox.org

# የካህናት ተልእኮ፤

በሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ



www.ethiopianorthodox.org

# መቅድም ፤

ይህ የካህን ተልእኮ በማለት የቀረበው ጽሑፍ ካህኑ ሊያደርገውና ሊፈጽመው የሚገባው ምንና ምን እንደሆነ ለይቶ የሚያስረዳ ነው ።

ካህን ማለት የበቃ፤የነቃ፤ከሁሉም ነገር የተለየ፤ለእግዚአብሔር አገልግሎት ብቻ የተሠለፈ ማለት ነው ፤ ስለዚህ ካህን ከተሾመበት ማለት ካህን ከሆነበት ዕለት ጀምሮ ከሰው ተራ ወጥቶ በሰማያዊ ነገድነት የተመዘገበ ምድራዊ መልአክ ነው ። ካህን ከምድራዊ ንዝንዝና ጭቅጭቅ የራቀ፣ማዕርጉን የጠበቀ፣በዕውቀት ግን የላቀ ክፉውንና ደጉን የለየ፤ምንን መሥራት ምንን መተው እንዳለበት ዐውቆ የሚኖር ነው ። ካህን የሚሆን ሁሉ በሕይወቱ ፣ በልብሱ ከሌላው ሰው ሁሉ ተለይቶ የሚታወቅ መሆን አለበት ። ካህኑ ራሱን ያወቀ ራሱንም የጠበቀ ስለሆነ ሁሉ ያከብረዋል፣ እንደ እግዚአብሔር መልአክም አድርጎ ይቀበለዋል፤ የሚናገረውን ይሰማል፤ በዚህ መልክ እርሱም ተልእኮውን እንደ ዓላማው ይፈጽማል ። ካህን በዘሩ በወገኑ ግዴታ ኑሮበት የሚሾም አይደለም ፤ እንዲሁም እንደ ግብር ዕዳውን ለመወጣት ብቻ የሚሾሙ አይደለም ፤ የሚቀበለው ሥልጣን ሰው ሠራሽ ሳይሆን እግዚአብሔር የፈቀደው ነው ፤ ስለዚህ እርሱን በትክክል ለማገልገል ፣ ሕዝበ እግዚአብሔር የሆነውንም ምእመን ለማስተማር ቆርጦ የተነሣ መሆን አለበት ። ለእግዚአብሔር አምልኮት ለማቅረብ ቆርጦ ካህኑ ሲነሣ እግዚአብሔርም ሲፈቅድለት ምእመናንም ሲመርጡት የተሾመ እንደሆነ እንደ ዓላማው ይፈጽማል ።

ቅዱሳን ሐዋርያት በዚህ መልክ መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ መረጣቸው ፤ ሀብተ ክህነትንም ፣ ሥልጣነ ክህነትንም ሰጣቸው ፤ የክህነትን ተልእኮ እንዲፈጽሙ ሥልጣኑን ሰጥቶ ወደ ዓለም አሠማራቸው ።

የሐዋርያት ተከታዮች የሆኑ ሁሉ በሐዋርያት መራጭነት ፣ በእግዚአብሔርም ጠሪነት በአንብሮተ እድ ተሾሙ ፣ ካህን ሊቀ ካህናት ሆኑ ፤

የሐዋርያት ተከታዮች የሆኑ ሁሉ በሐዋርያት መራጭነት ፣ በእግዚአብሔርም ጠሪነት በአንብሮተ እድ ተሾሙ ፣ ካህን ሊቀ ካህናት ሆኑ ፤ በተሾሙበትም ቦታ ፣ በተሾሙበትም ዓላማ ሠሩ፣ ስለዚህ ተልእኳቸውን በሚገባ ፈጸሙ ።

አሁንም በጊዜያችን የሚነሡ ካህናት የሐዋርያት ተከታዮች ሆነው የሚሠሩ ፣ በእነርሱ እግር በትክክል የተተኩና የሚተኩ መሆናቸውን አምነው የሚሠሩ መሆን አለባቸው ።



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ይኸችም ትንሽ ጽሑፍ የምታስገነዝበው እንደመረሳት እያለ የሄደው የካህኑ ተልእኮ ምንና ምን መሆን እንደሚገባው ነው ። ምንም ሥጋዊ ሹመትም ቢሆን ለሥራ መሾሙ የታወቀ ቢሆንም የካህኑ ሹመት ግን ዕጥፍና ድርብ የሆነ ኃላፊነት ያለበት ፡ ከባድ ሥራም የሚሠራ መሆኑን ዐውቆ እያንዳንዱ ካህን እንደ ዓላማው ለመፈጸም ይችል ዘንድ መብቱንም ግዳጁንም የምትገልጥ ናት ።

ካህን የሆነ ሁሉ ይኸችን ጽሑፍ በማንበብና በማጥናት ራሱን እን ዲያስተካክል በእውነተኛውም የካህን ጐዳና እንዲራመድ ትመራዋለች ።

ካህን ለመሆን ገና የሚመኝ ፡ በዚህም ዓላማ የሚሠለጥን እንዳለ ደግሞ የኃላፊነቱን ከባድነት ፡ የሥራውን ብዛት አይቶ ይሁንብኝ ብሎ እንዲገባና ተልእኮውን በሚገባ ለመፈጸም ብቁ ሆኖ እንዲገኝ የምታደርግ ጽሑፍ ናት ።

ካህኑ ማዕርጉ ምጡቅ ፡ አእምሮው ረቂቅ ሆኖ በትንሹና በዝቅተኛው ነገር ሁሉ የማይጨቃጨቅ ፡ እውነተኛውን የካህኑን ዓላማ ብቻ የሚ መለከት ሆኖ ይገኝ ዘንድ ቤተ ክርስቲያናችን ይኸን መመሪያ ሰጥታለች።

ለራሱ ተልእኮውን ዓላማውን የሚያውቅ ፡ መንጋውን የሚጠብቅ መሆን አለበት ፤ ሐዋርያው ጳውሎስ ለተከታዮቹ ማስጠንቀቂያ መመሪያ ሲሰጥ የተናገራቸው ቃላት «አሁንም ለራሳችሁ ተጠንቀቁ ለመንጋውም ሁሉ ፡ መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ላይ ጠባቆች አድርጎ የሾማችሁ የእግዚአ ብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁ ዘንድ እርሱ በደሙ የዋጃትን» የሚል ነበር ፡ (የሐዋ ፡ ሥራ ፡ ፳ ፡ ፳፰) ።

ካህናት ነን ብለን በካህን ስም ከቀረብን የሚጠብቀን ኃላፊነት ይኸን የመሰለ ነው ፤ ታዲያ እኛም ተልእኳችንን ዐውቀን ይኸን ለመፈ ጸም ዝግጁ ሆነን እንቅረብ ።

ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ



# ክፍል ፩ እውነተኛ ካህን

## ፩፡ የክህነት ትርጉም

ካህን ማለት ኮኼን ከሚለው ከዕብራይስጡ የተወሰደ ቃል ነው ፡ ትርጉሙም የተለየ ፡ የተቀደሰ ፡ ለእግዚአብሔርም አገልጋይነት ብቁ የሆነ ማለት ነው ፤ በእርግጥም እንደሚያመለክተው አንድ ሰው ካህን ሲሆን ልዩ ጸሎት ደርሶለት ፤ ልዩ ቡራኬም ተሰጥቶ በመንፈስ ተቀብቶ ነው ።

የብሉይ ኪዳን ካህን የብሉይም ሊቀ ካህን ይሾም የነበረው እግ ዚአብሔር በሚወደውና በሚፈቅደው መሥመር የተሠማሩና ለዚሁ አገ ልግሎት ብቁ ናቸው ተብለው ከተመረጡ ነገዶች ከነገደ አሮንና ከነገደ ሌዊ ውስጥ ነበር ።

እነዚህም ካህናት ከተለዩ ነገዶች ወጥተው ቢሰየሙም ገና ለሹመት በቀረቡ ጊዜ የተለየ ጸሎት የተለየም ቅብዓት ተሰጥቷቸው ይሰየሙ ነበር።

በብሉይ ዘመን የካህናት ምርጫና ሹመት በዚህ መልክ ሲፈጸም ይገኝ እንጂ ይኸ ሁሉ ለሐዲስ ኪዳን ካህን አምሳል መርገፍ በመሆን እንደተፈጸመ የታወቀ ነው ።

የሐዲስ ኪዳን ክህነት ግን ጀማሪ የሆነው እውነተኛው ካህን ሊቀ ካህን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ። እርሱም ክህነቱ ዘለዓለማዊ ነው ፤ እንደመ ልከ ጼዴቅም ክህነት ነው።ሹመቱም ከዘር የወረደ ሳይሆን ከባሕርዩ የተ ገኘ ነው ፤ እንደ ትርጉሙ እውነተኛ ካህን ሆኖ የተገኘ ፡ እንደ ሊቀ ካህ ንነቱም ተልእኮውን የፈጸመ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ፤ ምክንያ ቱም ካህን የሚሆን ስለ ሕዝቡ ኃጢአት መሥዋዕት የሚያቀርብ ፡ ጸሎት የሚጸልይ ፡ ሕዝቡን በትክክል ወደ ደኅንነት ጐዳና የሚመራ፤የእግዚአብ ሔር እውነተኛ አገልጋይ ፤ የተለየ የተቀደሰ ነውና ። ጌታችን ኢየሱስም ለዚህ ሁሉ እውነተኛ ምሳሌነቱን የሰጠ እውነተኛ ሊቀ ካህናት ነውና። ከዚያ በኋላ የሚነሣው ካህን ሁሉ እርሱን አብነት አድርጎ እውነተኛ ካህን ሆኖ በመገኘት እንዲሠራ እንጂ በስም ብቻ ወይም የካህን ልብስ በመል በስ ብቻ ካህን ነኝ እንዳይል ፡ ካህንም መስሎ እንዳይቀርብ ካህን የሚ ለው የስም ትርጓሜ ያስረዳል ። የሐዲስ ኪዳን ክህነት ጀማሪ የሆነው ኢየ ሱስ ክርስቶስም ምሳሌነቱን በሥራ ገልጦ አስረድቷልና ።



www.ethiopianorthodox.org

## ፪/ የክህነት አጀማመር ፤

የክህነት አነሣስ ከሰው ልጅ ድኅነት ፥ ከሰው ልጅም ማኅበራዊ ኑሮ ፍላጎት የተነሣ አምላክ የፈቀደው ማዕርግ ነው ።

ካህን የሚለው ስምና የካህን ተልእኮ ገና ሳይታወቅ የቤተሰብእ አስተዳዳሪዎች አባቶች እንደ ካህን ሆነው በካህንም እግር ገብተው ይሠሩ ፥ የካህኑን ቦታ ይዘው ተልእኳቸውን ይፈጽሙ ነበር ።

ከነዚህም አባቶች መካከል ጥቂቶቹ ፓትርያርክ (አርእስተ አበው) እየ ተባሉ የሚጠሩ ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በትክክል የሚፈጽሙ ፤ እርም ጃቸውን በማስተካከል የእግዚአብሔርን ፍለጋ በመከተል የሠሩ ናቸው። እነዚህ ሰዎች ምክር ፥ ተግሣጽ ለቤተ ሰብእ ሲሰጡ ፥ በመልካም ግብረ ገብነት ሲመሩ ፥ ጸሎት ሲጸልዩ ፥ መሥዋዕት ሲሠው የኖሩ ናቸው ።

### ስም በመጥራት ጥቂቶቹን ያነሣሣን እንደሆነ ፡—

፩/ ኖኅ የተባለው አባት ፥ ይኸ አባት ቤተሰቡን ሠርቶ ቀጥቶ ከመ ኖሩ የተነሣ በመላ የሰው ልጅ ሁሉ በጥፋት ውሃ ሲቀጣ ራሱን ቤተሰቡ ንም ለማዳን ችሏል ። ልጆቹ ስሕተት ሠርተው በደልም ፈጽመው እን ዳይፈርድባቸው በማለት እንደ ካህን ሲጸልይላቸው ፥ መሥዋዕትም ሲሠ ዋላቸው እናገኛለን (ዘፍ ፡ ፰ ፡ ፳) ።

፪/ አበ ብዙኃን አብርሃም ፥ እርሱም እንዲሁ የቤተሰብ አባትና አስተዳዳሪ እንደመሆኑ እንደ ካህን ቤተሰቡን ሲመክር ሲያስተምር በመ ልካም ሥነ ሥርዓት ሲመራ ፥ መሥዋዕትም ሲሠዋ ይገኛል (ዘፍ ፳፪፡ ፲፫) ።

፫/ የዘለዓለም ካህን የተባለው መልከ ጼዴቅ ፥ ይኸ ሰው ትውልዱ ነገዱ አይታወቅም እንጂ ካህን በሌለበት ዘመን ካህን ሆኖ ኅብስተ አኮ ቴት ጽዋዓ በረከት አቅርቧል (ዘፍ ፡ ፲፬ ፡ ፲፰) ።

፬/ የሙሴ አማት ዮቶር ፥ ይኸ ሰው የምድያም ካህን እየተባለ ይጠራ ነበር ፤ ቤተሰቡንም ያስተምር ይመክር ነበር ፤ ጸሎት ይጸልይ መሥ ዋትም ይሠዋ ነበር (ዘጸአ ፡ ፳፰ ፡ ፪) ።

፭/ መስፍኑ ሙሴ ፥ የእስራኤል መሪ አስተማሪ የሆነው ሙሴ እስ ራኤልን በመንፈሳዊም በሥጋዊም አመራር እየመራ ሕዝቡን ሕዝበ



እግዚአብሔር አሰኝቷል ፤ እርሱም የአምላክ ባለሟል ተብሏል ፤ እንደ ፓትርያርክ (ሊቀ ካህናት) ሆኖ አሮንንና ልጆቹን ካህናት ይሆኑ ካህናትም ይባሉ ዘንድ ቀብቷል ፥ ሹሟል ።

ከዚህ በኋላ ግን የብሉይ ኪዳን ክህነት ተጀመረና የክህነት ወገን የክህነትም ቤት የአሮን ቤት ሆነ፤ የእርሱ ልጆች የልጅ ልጆቹም ሁሉ ካህ ናት እየሆኑ ካህናትም እየተባሉ የብሉይ ኪዳን የክህነትን ተግባር ሲፈ ጽሙ ኖረዋል ።

የአሮንና የልጆቹ የክህነት አገልግሎት ሁሉ ለሐዲስ ኪዳን ክህነ ታዊ አገልግሎት ምሳሌ ሆኗል ።

## ፫/ የብሉይ ኪዳን ካህን ፤

እግዚአብሔር አምላክ የሁሉ ፈጣሪ የሁሉም አስገኝ እንደመሆኑ ነገሩም ሁሉ ገንዘቡ ነው ፤ ስለዚህ ሕዝቡን እርሱ የሚጠብቅ የሚመለ ከት ሲሆን እንደ እርሱ ሆኖ ከእርሱ በታች የሚጠብቅለት ከሰው ወገን ካህን አድርጎ አስነሣ ። ነቢዩ ሙሴ በእስራኤል ላይ መስፍን ሆኖ ሲነሣ በቤቱ የታመነ መሪ ፥ የታመነም አስተዳዳሪ በመሆን ነው ። ይኸንንም ቅዱስ ጳውሎስ ሲመሰክርለት «ሙሴም በቤቱ ሁሉ የታመነ ሆኗልና እንደሎሌ ለምስክር ኋላ ይነግር ዘንድ ባለው ነገር (ዕብራ ፥ ፫ ፥ ፭) ።

ሙሴ የእስራኤል መሪ ይሆን ዘንድ ከእግዚአብሔር ሲጠራ የፈር ዖን ልጅ ሆኖ በሰው ዘንድ ከብሮ ከመኖር ይልቅ ከሕዝቡ ጋር መከራን ይቀበል ዘንድ ስለወደደ የፈርዖን ልጅ ነህ ቢሉት አይደለሁም ሲል ካደ። ይኸንንም ሐዋርያው ጳውሎስ «ሙሴ ከአደገ በኋላ የፈርኦን የልጅ ልጅ እንዳይባል በእምነት እንቢ አለ ፤ ከግብጽ ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለ ክርስ ቶስ መነቀፍ እጅግ የሚበልጥ እንደሆነ አስቧልና ፤ ለጊዜው በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራን መቀበልን መረጠ ፤ ብድራቱን ትኩር ብሎ ተመልክቷልና» ሲል በሰፊው ገልጦ ጽፎለት እናገኛለን (ዕብራ ፡ ፲፩ ፡ ፳፬—፳፮) ።

ሙሴ በእግዚአብሔር የታመነ መስፍን በመሆኑ ሕዝበ እግዚአብ ሔር የተባለውን እስራኤልን እየመራ ከባርነት ወደ ነፃነት ፥ ከባዕድ አገር ወደ ምድረ ርስት ይዞ ገብቷል ።

ሙሴ እንደ መስፍንም እንደ ካህንም እየሆነ ሕዝቡን ሲመራ ፥ ሕዝቡ ባጠፉም ጊዜ ሲገሥጽ ፥ ሲመክር ቆይቷል ። የሕዝቡን ጩኸት ወደ እግ



www.ethiopianorthodox.org

ዚአብሔር ያሰማ የእግዚአብሔርንም ምሕረት ደግሞ ወደ ሕዝቡ ያስተላ ልፍ ነበር ።

እስራኤል ተሳስተው ጣዖት ቢያመልኩ ለራሱ ነፍስ ሳይሳሳ ሙሴ እሥራኤልን ቀጥቷል፣ አምልኮተ ጣዖትን አጥፍቷል (ዘጸአ ፡ ፴፪፣ ፳፯—፳፰) ።

ሙሴ እንዲህ እያደረገ ክህነትን ከምስፍና ጋር ይዞ ሲቆይ እግዚአ ብሔር አምላክ ክህነትን ለአሮንና ለቤተሰቡ ስለ ሰጠው አሮንን ካህን አድርጎ ሹሞታል ። ከዚያ በኋላ ክህነት ከአሮን ዘር እንዳይወጣ፣ የአሮን ነገድ ወንድ የሆነው ሁሉ ካህን እንዲሆን ካህንም እንዲባል ተደነገገ ።

ስለዚህም እግዚአብሔር አምላክ ሙሴን እንዲህ ሲል አዘዘው «አን ተም አሮንን ወንድምህን ልጆቹንም ከእስራኤል ልጆች መካከል ለይ ተህ ወደ አንተ አቅርብ ፤ ካህናት ይሆኑልኝ ዘንድ፣ አሮንን፣ ናዳብን፣ አቡሁንም፣ አልዓዛርንም፣ ኢታምርንም፣ የአሮንን ልጆች» (ዘጸ፡ ፳፰፡፩)።

አሮንም የሙሴ ታላቅ ወንድም የሆነው የመጀመሪያው የብሉይ ኪዳን ካህን ሆነ ፣ ከእርሱም ባለሟልነት የተነሣ ልጆቹ የልጅ ልጆቹ ሁሉ በእርሱ እግር እየገቡ ካህናት እንዲሆኑ ካህናትም እንዲባሉ ሆነ ። ሥራቸውም መሥዋዕት መሠዋት እግዚአብሔርን ማምለክ ፤ የሕዝቡን ኃጢአት ማስተስረይ ፤ የኪዳኑን ጽላት መሸከም ሌላም ይኸን የመሰለ ነበር ። እነዚህ የብሉይ ኪዳን ካህናት የእግዚአብሔር ኃይል መገለጫ የሥልጣኑ መታወቂያ በመሆን ለምጽ የሚያነጹ፣ ደዌ የሚፈውሱ፣ ርኩ ሱን ሁሉ የሚቀድሱ ነበሩ ። ካህናት በጦር ሜዳም የኪዳኑን ታቦት በመ ሸከም ሳይፈሩ ከሠልፉ የሚውሉ ነበሩ ፤ እነርሱም ታቦተ ኪዳኑን ተሸ ክመው በጦር ሜዳ በዋሉ ጊዜ እስራኤል በአቸናፊነት ከብረው ይመለሱ ጠላት ግን አፍሮና ድል ሆኖ ይገባ ነበር ። እንዲሁም የዮርዳኖስን ወንዝ እስራኤል በተሻገሩ ጊዜ ካህናት ጽላተ ኪዳንን ተሸክመው ከወንዙ መካ ከል ገብተው በመቆማቸው ወራጁ ውሀ ቆመላቸው ፤ ስለዚህ ሕዝቡ በደ ረቁ ተሻገረ ። የኢያሪኮንም ከተማ ለመያዝ ሙከራ በአደረጉ ጊዜ ጽላተ ኪዳንን የተሸከሙ ካህናት የኢያሪኮን ቅጽር ፯ ጊዜ በመዞራቸው ቅጽሩ ፈረሰ ፤ እስራኤልም ገብተው ወጓቸው ድልም አደረጓቸው (ኢያሱ ፡ ፮ ፡ ፩—፳፯) ።

ካህናት ከዘመን ወደ ዘመን የተሸጋገሩትን ያህል በቊጥር እየበዙ በማዕርግም እያደጉ በመሄዳቸው ሊቀ ካህናት ወይም ሊቃነ ካህናት እስ መባል ደርሰው ነበር ።

በነዚህ ካህናት አንጻር ደግሞ ሊዋውያን የሚባሉ ነበሩ ፤ እነርሱም የሌዊ ልጆች ናቸው፤ ስለዚህ በሌዊ ሊዋውያን ተብለዋል።እነዚህም ነገዶች እስራኤል ጣዖት በአመለኩ ጊዜ አሮን ሕዝቡን በመፍራት ሳይከላከል በመቅረቱ እግዚአብሔር አምላክ ተቆጥቶ ለእርሱና ለልጆቹ ተቃ ራኒዎች የሆኑ ነገዶች እነዚህን ሊዋውያንን አስነሣበት። ጣዖት ያመለከውን ሕዝብ ሙሴ በቀጣበት ጊዜ ሌዊና ልጆቹ ተባብረውት ነበር ፤ ስለዚህ ይህ ክብ ርና ስም ተሰጣቸው (ዘጸ ፣ ፴፪ ፡ ፳፯—፳፰) ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሌዊ ልጆች እንደ አሮን ልጆች ካህናት ሆነው ካህናትም መስለው መታየት ጀመሩ ፤ ዋና ሥራቸው ግን ደብተራ ኦሪ ቱን ማገልገል ፣ ንዋየ ደብተራውን መሸከም ነው ። ይኸንም የሚያመለ ክት እግዚአብሔር አምላክ ያሰማውን ድምፅ እንዲህ ሲል እናገኛ ለን «እግዚአብሔር ሙሴን ተናገረው እንዲህ ሲል የሌዊን ነገድ አት ቊጠረው ቊጥራቸውንም ከእስራኤል ልጆች ጋር አታድርግ ። ነገር ግን በምስክሩ ድንኳን ላይ ሌዋውያንን አቁማቸው ፤ በዕቃውም ላይ ሁሉ በእርስዋም በሚሆነው ነገር ሁሉ ላይ እርሳቸው ድንኳኒቱን ይሸከሙ ፤ ዕቃውንም ሁሉ፤እርሳቸውም ያገለግሏት ፤ በድንኳኒቱም ዙሪያ ይሥፈሩ» (ዘኊል ፣ ፩ ፣ ፵፯—፶ ) ።

ይኸ የብሉይ ኪዳን ሥርዓት እስከ ክርስቶስ ዘመን ሠራ ፤ ለሐዲስ ኪዳንም አምሳል መርገፍ ሆነ ፤ ምንም መጀመሪያውን የፈቀደው የደነገ ገው እግዚአብሔር አምላክ ቢሆንም ሕጉን በሕግ በአደሰው ጊዜ ለሐዲስ ኪዳን ካህን ጀማሪ ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ ።

እውነተኛው ሊቀ ካህናት እርሱ ሆነ ፤እርሱም መሥዋዕት የሚሠዋ፣ መሥዋዕትም ሆኖ የሚቀርብ በትክክልም የሕዝቡን ኃጢአት የሚያስተ ሰርይ ሆኖ ቀረበ ።

## ፪/ የሐዲስ ኪዳን ካህን ፣

እግዚአብሔር አምላክ ለሕዝቡ መሪዎች አስተማሪዎች ይሆኑ ዘንድ ካህናት እንዲሾሙ ቢያደርግም ካህናቱ ተግባራቸውን ከመርሳታ ቸው የተነሣ ሕዝቡ ጠባቂ እንደሌለው መንጋ ባዘነ ፣ ቃባ እንደያዘውም በግ ተቅበዘበዘ ። ሕዝቡን ራሱ በፈቀደ ጊዜ እግዚአብሔር ወልድ ልዑል ባሕርዩን ዝቅ አደረገ፤ማለት ከሰማየ ሰማያት ወረደ ከድንግል ማር ያም ተወለደ ።



www.ethiopianorthodox.org

ጌታችን ኢየሱስ የ፴ ዓመት ዕድሜ ሲሆነው ሰው የሆነበትን ዓላማ ለመፈጸም ማስተማር ጀመረ ፤ በዚህም ጊዜ ደከመኝ ልረፍ ፥ በዛብኝና ሰለቸኝ ስለዚህ ልተወው ሳይል ማስተማሩን ፥ ሕዝብንም ማገልገሉን ሳያቋርጥ የካህንነቱን የሊቀ ካህንነቱን ተልእኮ ፈጸመ ።

የሰው ልጅ በሠራው ኃጢአት ተፈርዶበት ከተሰጠው ቅጣት ለማዳን እግዚአብሔር ወልድ በሰው እግር ገብቶ ለመሞት ፈቀደ፤ ሰው ራሱን ለማዳን ከማይችልበት ደረጃ ደርሶ ነበርና ። ሰው የፈለገውን ያህል ደም ቢያፈስ ፤ ስብ ቢያጤስ ፤ መሥዋዕትም ቢሠዋ ከቶ ሊድንአልቻለም ነበርና ፤ ስለዚህም ሕዝቡን ለማዳን በብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህናት አንጻር እርሱ እውነተኛው ሊቀ ካህናት ሆኖ ቀረበ ። ሊቀ ካህናት የሚባለውንም ስም ገንዘብ አድርጎ ራሱን ሠዋ ።

ሊቀ ካህንነቱም እንደ አሮን ልጆች እንዲሁም እንደሌዊ ልጆች ከዘር ሲወርድ ሲወራረድም የመጣለት አይደለም ፤ እርሱም እንደ ብሉይ ሊቀ ካህናት መሥዋዕት ያቀረበ አይደለም ፤ ለማዳን ችሎታ ያለው ሊቀ ካህናት እንደመሆኑ ለማዳን የሚችለውን ራሱን መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ እንጂ (ዕብራ ፡ ፬ ፡ ፲፬—፲፰) ።

ክርስቶስ ዘለዓለማዊ ሊቀ ካህናት ሆነ ፤ ስለዚህም ነቢዩ ዳዊት አስቀድሞ «አንተ ካህኑ ለዓለም በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ» ሲል ተናግሮለታል (መዝ. ፩፻፱ ፡ ፬ ፡ ዕብራ ፡ ፯ ፡ ፳) ። ሊቀ ካህናችን ኢየሱስ የመጣበት የካህንነቱን ተልእኮ በዚህ መልክ ፈጸመ ፤ የሐዲስ ኪዳንም የመጀመሪያው ሊቀ ካህናት ሆነ ፤ የእውነተኛው ካህን ምሳሌ በመሆን አስተማረ ፤ በቃል ያልተማረውንም በሥራ ተርጕሞ አሳየ ። ክርስቶስ እውነተኛና ዘለዓለማዊ ሊቀ ካህናት እንደመሆኑ የእርሱ ተከታዮች የሚሆኑትን እርሱን መስለው የሚሠሩትን ሐዋርያትን መረጠና በእግሩ ተካቸው ፤ ለመረጣቸው ሐዋርያትም ፍጹም ክህነታዊ ሥልጣንን ሰጣቸው ፤ በሁሉም ላይ አሠለጠናቸው (ማቴ ፡ ፲ ፡ ፩) ።

ቅዱሳን ሐዋርያትም መምህራቸው ክርስቶስ «ሒዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ፤ ስታጠምቋቸውም በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም» ሲል ያዘዛቸውን በመከተል በዓለም ተበትነው የዛሬው ካህን የእነሱ ተተኪ ሁኖ ሊሠራውና ሊፈጽመው የሚገባውን ተልእኮ በትክክል ፈጸመ ። (ማቴ ፡ ፳፰ ፡ ፲፱) ።



እነዚህ ሐዋርያት የተሰቀለውን ክርስቶስን ማዕከል በማድረግ በማ ፤ ስተማር ፤ ጸሎት በመጸለይ ፤ መሥዋዕት በማቅረብ ፤ በሽተኞችን በመፈወስ በጠቅላላም ክህነታዊ አገልግሎትን በመፈጸም ሠሩ ።

ሕይወቱ ተበላሽቶ የነበረውን ሕዝብ ከብሌት ወደ ተሐድሶ ለወጡት ፤ ማኅበራዊ ኑሮው መራራ የነበረውን አጣፈጡት፤በጠቅላላም ሁሉን ከሞት ወደ ሕይወት መለሱት ።

ለሐዲስ ኪዳን ካህን ሁሉ መሥራች ኢየሱስ ክርስቶስ እንደመሆኑ የእርሱን ፈለግ ተከትለው ተልእኳቸውን በመፈጸም ለክህነታዊ አገልግሎት ፍጹም ሠራተኞችና ምሳሌ ሆነው ቅዱሳን ሐዋርያት ሠሩ ።

ከሐዋርያት ጀምሮ ለክህነት ማዕርግ ብቁ የሆኑት እየተመረጡ ተሹመው አገልግሎታቸውን የፈጸሙ ብዙዎች ናቸው ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ክህነት ቅዱስ አገልግሎት በመሆኑ ከእግዚአብሔር ጥሪ የደረሰው፤ ቤተ ክርስቲያንም የመረጠችው፤ ለዓላማውም ብቁ ሆኖ የተገኘው ሰው ካህን እየሆነ ፥ በአንብሮተ እድም እየተሾመ ፤ ተልእኮውን እየፈጸመ ሳያቋርጥ እስከ ጊዜያችን ደርሷል ።

---

### ፩/ ለክህነት አገልግሎት መጠራት ፤

ማንኛውም ሰው ለአንድ ሥራ ጥሪ ወይም ስጦታ አለው ፥ ይህም ስጦታ የተፈጥሮ (የባሕርይ) ሊሆን ይችላል ፤ ወይም በትምህርትና በልማድም ይገኛል ፤ ይህም ነገር እርግጠኛ መሆኑን የሚያስረዳ አንድ ሰው አንድ ነገርን ይወዳል ሌላውን ግን ይጠላል ፤ አንደኛውን አዘውትሮ ይሠራል፤ ስለርሱም ይናገራል ፤ ሌላውን ግን ሊያየው ቀርቶ ሊሰማው አይወድም ። ይህ የመውደድና የመጥላት ስሜት ኃይል «ጥሪ ወይም ስጦታ» ይባላል ። የተፈጥሮ ስጦታ ወይም ጥሪ የተባለው የማይናወጥ ልባዊ ስሜት ሆኖ እናገኘዋለን ። የተፈጥሮ ስጦታ ወይም ጥሪ በትምህርት ምክንያት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለና እያደገ እየተስፋፋም የሚሄድ ነው ፤ ስለዚህ አንድን ሕፃን ከልጅነቱ ጀምሮ በዚህ ስጦታ ሊመሩትና ሊያሳድጉት ይገባል ፤ በዚህ ዓለም ልዩ ልዩ አይነት የሆኑ ዕውቀቶችና ጥበባት ይገኛሉ ፤ የሰውም ስጦታው እንዲሁ የተለያየ በመሆኑ አንዱ የሚወደውንና የሚያዘወትረውን ሌላው አይወደውም ፤ ስለ ርሱም ፍላጎት ከቶ የለውም። ይህንም ይዘው የቀደሙ አቴናውያን ሕፃናት በመረጡት እንዲያድጉ በማለት ከሕፃንነታቸው ጀምሮ የሚሠሩትንና የሚናገሩትን ጠንቅቀው ይከታተሏቸው በዚያውም ያሳድጓቸው ነበር ይባላል ። ካህ



www.ethiopianorthodox.org

ንም የሚሆን ሰው እንዲሁ የተፈጥሮ ስጦታና ጥሪ ሊኖረው ይገባል ፤ ምክንያቱም የሕዝቡ መሪ ፤ የትሩፋት አበጋዝ ፤ የነፍሳቸውም ጠባቂ ፤ የመልካምም ሥራ ሁሉ አብነት ስለ ሆነ አንድ ጊዜ ከጀመረ ወደ ኋላ ሊመለስ ከቶ የማይችል ነውና ስለዚህ «ኢየሱስም አለ ማንም የለም ማረሻ በእጅ ይዞ ወደ ኋላው የሚመለከት ለእግዚአብሔር መንግሥት ይሆን ዘንድ» ሲል ይነግረናል (ሉቃ ፡ ፱ ፡ ፷፪) ።

ካህኑ ይህን ለማለፍ ለሥራውም መልካም ውጤትን ለማግኘት የሚችለው ቀድሞውን ጥሪ ሲኖረው ከእግዚአብሔርም ሲታዘዝ ነውና ።

ይህ ጥሪ ሰማያዊ የሆነ ሰማያዊም አገልግሎት ያለው ፤ በሚገባም ቢፈጽሙት ሰማያዊ ዋጋን የሚሰጥ ስለ ሆነ ብዙዎች አክብረው ይቀበሉታል፤ እንደ ጥሪያቸውም ለመፈጸም ተጋድሎን ያደርጋሉ ። ይኸ ጥሪ ወይም ስጦታ የተባለው ሀብት ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ወይም የሚጠራ ማለት ነው ። በብሉይ ኪዳን አርእስተ አበው የተባሉት እነ ሙሴ በመላም ነቢያት ከእግዚአብሔር ዘንድ እየተጠሩ ሀብተ ትንቢት እየተሰጣቸው ተልእኳቸውን ፈጽመዋል ። በሐዲስ ኪዳንም በክርስቶስ የተጠሩ በመላ ሐዋርያት እንደ ጳውሎስ ፤ ሰብዓ አርድእት ይህንም የመሰሉ ብዙዎች ናቸው ። ይህ ዐይነት ጥሪ ግን በሁለት ይከፈላል ይኸውም አንደኛው ውስጣዊ፤ሁለተኛው አፍአዊ ጥሪ ይባላል ።

ሀ/ ውስጣዊ ጥሪ የተባለው በተፈጥሮ የሚሰጥና የሚጠራ የሰው አሳቡ የሚያዘነብልበት በዚያውም ጸንቶ የሚኖርበት ከትምህርትም ጋራ የተከታተለው እንደሆነ መልካም ውጤትን የሚሰጥ ጥሪ ወይም ስጦታ ነው ።

ይህ ጥሪ ወይም ስጦታ ለማንኛውም ሥራ ለማንኛውም ጥበብ የሚሰጥ ነው፤ በተለይ ግን ሊጠነቀቁለት የሚገባ ለክህነት ማዕርግ ነው ፤ ምክንያቱም ከእግዚአብሔር ስጦታ ወይም ጥሪ ያለው ራሱም ወዶና ለምዶ የገባው ካህን ምንም ጊዜ ልዩ ልዩ ጸዋትወ መከራ ቢደርስበት አይሰቀቅም አይመረርም ፤ እንዲያውም ደስ እያለው በመከራ ላይ መከራ ቢጨመርበት ጸጋ እንዲበዛለት አምኖ ይቀበለዋል ፤ (፪፡ ቆሮ፡ ፲፪ ፡ ፱—፲ ፡ የሐ ሥራ ፭ ፡ ፵፯—፵፪) ።

ጥሪ ሳይኖረው ራሱም ሳይወደው የገባ እንደ ሆነ ግን በየጊዜው ሲመረር ፤ ሲበሳጭ ፤ ለራሱ ቀርቶ ለሌሎችም የመሰናክል ድንጋይ ይሆናል ፤ ስለዚህ ካህን የሚሆን ሰው ሰውነቱን ይመርምር ፤ ጥሪውን ያክብር ፤



የኃላፊነቱን ከባድነት የሥራውን ብዛት አጥንቶ ይግባ። ጥሪ ወይም ስጦታ እንዲኖረው የፈለገ እንደሆነ ደግሞ አስቀድሞ ልባዊ ጸሎት ያድርግ፤ለማንኛውም ሥራ ተስማሚ እንዲሆን እግዚብሔርም እንዲፈቅድለት «ወይኩን ፈቃድከ» እያለ ይጸልይ፤ጸሎት የበር ሁሉ መክፈቻ የማትሰበር ቁልፍ ናትና ፤ ስለዚህ ያለማቋረጥ ይጸልይ ፤

ክርስቶስ እንኳን ሐዋርያትን ለዚህ ሥራ ሲመርጥ አስቀድሞ ወደ ተራራ ወጥቶ ጸሎት ጸልዮ ነው « ሆነም በዚያች ወራት ወደ ተራራ ወጣ ጸሎት ይጸልይ ዘንድ በእግዚአብሔር ጸሎትም ተግቶ ነበር ሌሊቱን ሁሉ ቀንም በሆነ ጊዜ ደቀመዛሙርቱን ጠራ ከእርሳቸውም ዐሥራ ሁለት መረጠ ሐዋርያት ያላቸውን» (ሉቃ ፡ ፮ ፡ ፲፪—፲፫)

ይህም የሚያስረዳን ለሿሚም ለተሿሚም አስቀድሞ ጸሎት ማድረግና ጥሪውን ወይም ስጦታውን ማግኘት እንዳለበት ነው ፤ ከዚህም በቀር ካህኑ ከዚያን ቀን ጀምሮ ሥራው ጸሎት እንደሆነ እንዲረዳው ነው (፩፡ ጢሞ፡ ፪ ፡ ፩—፫) ።

ለ/ አፍአዊ ጥሪ ፡— አፍአዊ ጥሪ ማለት እንዲሁ ከውጭ የሚሰማ ድምፅ ነው ፤ ይህ እንደ ገና በሁለት ክፍል ይከፈላል ፤ ቀጥተኛ አፍአዊ ጥሪና በጐን የሚሆን አፍአዊ ጥሪ ናቸው ።

ቀጥተኛ ጥሪ ማለት በቀጥታ ከእግዚአብሔር የሚጠሩት ጥሪ የሚሰሙትም ድምፅ ማለት ነው ። እግዚአብሔር ሕዝቡን ያለ ጠባቂ ከቶ ትቶት አያውቅም ስለዚህም የርሱ እንደራሴዎች ሆነው በታማኝነት የሚጠብቁለትን ሲጠራና ሲመርጥ ድምፅም ሲያሰማ ይኖራል ።

ለምሳሌ ፡— በብሉይ ኪዳን ፡ ሙሴን ፡ ኤልያስን ፡ እንዲሁም በመላ ነቢያትን ሕጉን የሚያስተምሩለትን ትንቢት የሚናገሩለትን ሕዝቡን የሚያስተዳድሩለትን ጠርቷል (ኦሪት ዘፀአ ፡ ፫ ፡ ፬—፳፪) ።

በሐዲስ ኪዳንም በመላ ሐዋርያትን ጠርቷል (ማቴ ፡ ፲ ፡ ፩—፭) ። ሰብዓ አርድዕትንም ሌሎችንም አገልጋዮች ራሱ ጠራቸው (የሐ ፡ ሥራ ፱ ፡ ፬—፳፮)።«እርሳቸው ም በእግዚአብሔር ሲያገለግሉ ሲጾሙም ፡ መንፈስ ቅዱስ አለ በርናባስንና ሳውልን ለዩልኝ ለጸራኋቸው ሥራ በዚያን ጊዜም ጾሙ ፤ ጸልዩም ፤ እጃቸውንም በጫኑባቸው ጊዜ ሰደድዋቸው»

(የሐ ፡ ሥራ ፡ ፲፫ ፡ ፪—፫) ። የሐዋርያትን ጥሪ ራሱ ሲያጸድቀው «እናንተ አልመረጣችሁኝም እኔ እላንተን መረጥኋችሁ እንጂ እስነሣ



www.ethiopianorthodox.org

ኋችሁም ትሄዱ ዘንድ ፍሬም ታፈሩ ዘንድ ፍሬያችሁም ይኖር ዘንድ» ሲል ጌታ አስረድቷል ፤ (ዮሐ ፡ ፲፮ ፡ የሐ ፡ ሥራ ፡ ፩ ፡ ፳፬—፳፮) ።

እንደዚህ እያደረገ የቤተ ክርስቲያን ኃላፊ፤ ጠባቂ፤ አበነፍስ የሚሆኑትን ሁሉ እግዚአብሔር ሲጠራቸው እናገኛለን ፡ ይህም ቀጥተኛ ጥሪ ይባላል ። ቀጥተኛ ያልሆነ አፍአዊ ጥሪ ማለት ደግሞ ከራሱ ከእግዚአብሔር በቀጥታ ከላይ እንደዘረዘርነው ሳይሆን በጐን በሕልም በሰው ወይም በቤተ ክርስቲያን አማካይነት የሚጠሩት ጥሪ ነው ። በቤተ ክርስቲያን አማካይነት የሚጠሩት ጥሪ ለምሳሌ ፡ በርናባስንና ማትያስን በምግባር በሃይማኖት ፍጹም ሆነው ቢያገኟቸው ሐዋርያት መረጥዋቸው «ሁለትም አቆሙ፤በፊታቸው ዮሴፍን በርናባስ ተብሎ የሚጠራውን ዮስጦስ ተብሎ የሚጠራውንም ማትያስን በጸለዩም ጊዜ አሉ ፤ አንተ ጌታ ሆይ የሁሉን ልብ የምታውቅ ከእነዚህ ከሁለቱ አንዱን ግለጥ የመረጥከውን የዚህችን ማገልገል የመልእክቲቱን ሥፍራ ይወስድ ዘንድ ይሁዳ የተዋትን ወደ ሥፍራው ይሄድ ዘንድ ዕጣውም በማትያስ ላይ ወደቀ ከዐሥራ አንዱ ሐዋርያት ጋራም ተቈጠረ (የሐ ፡ ሥራ ፡ ፩ ፡ ፳፫—፳፮) ፤

ይህንም የመሰለ በቤተ ክርስቲያን የሚደረግ ጥሪ እስጢፋኖስንና ሌሎችን ስድስቱን ዲያቆናት እናገኛለን (የሐ ፡ ሥራ ፡ ፮ ፡ ፭) ።

ቀጥተኛ ከእግዚአብሔር ያልሆነ አፍአዊ ጥሪ ይህ ነው፤ እንደዚህ ያለ ጥሪ ወይም ምርጫ ለካህናት የኖራቸው እንደሆነ የሥራቸው እርምጃ ከዕለት ወደ ዕለት እየጎላ ይሄዳል ፤ ተልእኳቸውንም በሚገባ ይፈጽማሉ ።

## ፮/ ክህነት ቅዱስ ማዕርግ እንደሆነ ፤

ከቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት ፩ኛው ከፍተኛውም ፡ ማለት ሌላውን ምሥጢር ሁሉ የሚቀድስና የሚያነጻ ምሥጢረ ክህነት ነው ። ምሥጢረ ክህነትን ተቀብለው በሚገባ ተልእኳቸውን የሚፈጽሙ ካህናት ሁሉ የቅዱሱ የእግዚአብሔር እንደራሴዎች ስለሆኑ ቅዱሳን ይባላሉ ።

የሐዲስ ኪዳን ክህነት መሥራች ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነ እርሱ ቅዱስ እንደመሆኑ መዓርጉም ቅዱስ ነው ።

ካህናት የተመረጡ ወገኖች ፡ የተቀደሱ ዘሮች እንደሆኑ ቅዱስ ጴጥሮስ «እናንተ ግን የመንግሥትና የክህነት ወገን ናችሁ ፤ የተቀደሳችሁም ዘር ለርስት የተለየ ሕዝብ - - - » ሲል አስረድቷል (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፱) ።



ካህናት ከፍተኛ ማዕርግ ቅዱስ ሥልጣን ስላላቸው የማሠርና የመፍታት ሥልጣን አላቸው ፤ ይኸንኑም ክርስቶስ ሲመሰክርላቸው« ይኸንንም ብሎ እፍ አለባቸው ፤ አላቸውም መንፈስ ቅዱስን ተቀብሎ ኃጢአቱን የተዋችሁለት ቀረችለት ፤ የያዛችሁበትም ተያዘችበት » ሲል በሰፊው አስረድቷል (ዮሐ ፡ ፳ ፡ ፳፪—፳፫) ።

ለቅዱሳን ሐዋርያት ቅድስናቸውን አረጋግጦ እርሱም ቀድሶ አባቱም እንዲቀድሳቸው «ቀድሶሙ በጽድቅከ» ሲል ጸልዮላቸዋል ፤ ስለዚህ ካህን በምድር ያለ መልአክ ነው ፤ ሕይወቱን ለእግዚአብሔር ምስጋና የሰጠ ሁል ጊዜ እንደ መላእክት ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ እያለ የእግዚአብሔርን ስም እየቀደሰ ይኖራልና ።

ቅዱስ ጳውሎስ በየጊዜው የሚነሡትን ካህናት ቅዱሳን ሲላቸውና ቅዱሳንም መሆን እንዲገባቸው ሲናገር «ስለዚህም ቅዱሳን ወንድሞቼ ሆይ ከሰማይ በመጣችው መጠራት ባልንጀሮቼ ይኸን የሃይማኖታችንን ሐዋርያ የካህናትንም አለቃ ተመልከቱ ኢየሱስ ክርስቶስን » ሲል ገልጦ ጽፎ እናገኛዋለን (ዕብራ ፡ ፫ ፡ ፩) ።

ክህነት ቅዱስ ማዕርግ ከፍተኛም ሥልጣን ሲሆን ማንም በዘር ሊወርሰው በገንዘብ ሊገዛው አይችልም ፤ እግዚአብሔር አምላክ ለጠራውና ለዚህ ትበቃለህ ላለው ብቻ ነው እንጂ (የሐ ፡ ሥራ ፡ ፰ ፡ ፲፰—፳፬) ። ማዕርገ ክህነት ለመላእክት እንኳን ያልተሰጠ ለሰው ልጅ የተሰጠ ማዕርግ ነው ፤ ዘኢተገብረ ለመላእክት ተገብረ ለካህናት ሲል ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተናግሯልና ።

ቅዱስ ጳውሎስ በቅዱሳን መላእክት ላይ እንኳን ካህኑ ሥልጣን እንዳለው ሊፈርድም እንደሚችል ሲናገር «ወይስ አታውቁምን እኛ በመላእክት እንድንፈርድ ፡ እንዴት ይገባን ፡ በዚህ ዓለም ነገር መፍረድ» ሲል አስረድቷል (፩ ፡ ቆሮ፡ ፮ ፡ ፫) ።

ክህነት ቅዱስ ማዕርግ በመሆኑ ካህኑ በምድር የወሰነውን እግዚአብሔር በሰማይ ያጸድቀዋል ፤ ካህኑ ከእግዚአብሔር የተጣላውን ሰው ጸልዮ መሥዋዕትም ሠውቶ ሰውየውን ወደ ንስሓ አስገብቶ ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቀዋል ።

የክህነት ማዕርግ እንዲህ ያለ ቅዱስና ክቡር ሲሆን ለዚህ ማዕርግ ተቀባይ የሚሆነው ሰውም በጣም የበቃ ለማዕርጉ የተስማማ መሆን አለበት ።



www.ethiopianorthodox.org

## ፲/ የካህኑ መለያ ምልክት ፤

ምንም ለሐዲስ ኪዳን ካህን ጀማሪው ኢየሱስ ክርስቶስ ቢሆን እርሱም እውነተኛውን ክርስቲያናዊ ሕይወት የኖረና ምሳሌነቱን የሰጠ ቢሆን ፣ ተከታዮቹ ሐዋርያትም በዚያው መንፈስ ቢመሩም የኋላ አባቶች ነገሩን በማጠንከር በምርጫው ጊዜም የበለጠ ጥንቃቄ እንዲደረግበት በኋላም በልብሱ ፣ በቆቡ ፣ በመስቀሉ ፣ በሌላም ይኸን በመሳሰሉ መለያ ዎች ካህኑ እንዲታወቅ፤ከሌላውም ሰው እንዲለይ ወስነዋል ። ይሁን እንጂ ልብስ ሰውየውን ካህን ስለማያደርገው ውስጣውያን መለዮች እንዲኖሩትና በነዚያ መጠበቅ እውነተኛው ካህን ተለይቶ እንዲታወቅ ተደርጓል ። ለእውነተኛው ካህን መለያ መታወቂያም ከሚሆኑት ብዙዎች ውስጥ የሚከተሉትን ፺ቱን እንደ ዋና አድርገን እናቀርባለን ።

፩ኛ/ ፍጹም ሃይማኖት ፡— ካህኑ የሥራው ሁሉ መጀመሪያ መፈጸሚያም ሃይማኖት ነው ፤ ማለት በእግዚአብሔር ፈጣሪነት ሁሉ እንደተፈጠረ፥ ሁሉንም እግዚአብሔር እንደሚቆጣጠረው ፣ ሁሉንም እግዚአብሔር እንደሚያውቀው ማመን ለካህኑ ጌዴታው ነው። የሁሉም ፈጣሪ የሁሉም አስገኝ እግዚአብሔር ነው ፤ የሆነውና የሚሆነው ሁሉ እርሱ ሳያውቀው እርሱም ሳይፈቅደው ከቶ አይደረግምና ። ይኸም ዓይነት እምነት የካህኑ ብቻ ሳይሆን የሰው ሁሉ ዋናውና ዘላቂው እምነት ነው ፤ የሁሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር እንደሆነ ካህኑ በፍጹም ልቦናው ከአመነ፤ ሁሉንም የሚቆጣጠር እርሱ ብቻ መሆኑን ከዐወቀ፤ በተግባሩ የበረታ ፣ የማይፈራ ፣ የማያፍር ፣ ከእውነትም ፈቀቅ የማይል ይሆናል ፤ ምክንያቱም ክፉ ቢሠሩ ፍዳ ፣ በጎ ቢሠሩ ዋጋ የሚከፍል እርሱ ብቻ መሆኑን አምኖ ይሠራልና ። ካህኑ የእርሱ ብቻ አገልጋይ ይሆናል ፤ ከእርሱም ብቻ ዋጋ ለማግኘት ይጠብቃል ፤ ያለዚያ ጊዜያዊውን ክብር ከጊዜያዊ ሰው ይጠብቃል ፤ ሰውን የሚያመልከው ፤ ሰውን የሚፈራው ሁሉ ኃላፊውን ክብር ለጊዜው ያገኝ ይሆናል ፤ ያውም ሁል ጊዜ አይሆንም ፤ ቀጥሎም ሿሚውም ተሿሚውም ሰዎች እንደመሆናቸው አብረው ያልፋሉ ።

ክብሩም ሹመቱም አብሮ ያልፋል ፤ ስለዚህ ነዋሪው ቀዋሚው ካህኑ ኃላፊ ሆኖ ይቀራል ማለት ነው ። ነገር ግን በእግዚአብሔር አምኖ እርሱን ምስክር አድርጎ የሚሠራ እንኳን ካህኑ ማንም አማኒ ቢሆን ክብር አለው ፤ ለሥራውም መልካም ውጤት አለው ።

በእግዚአብሔር አምኖ የሚጀመር ሁሉ መልካም ፍጻሜ አለው ፤ ሁሉን ለማድረግ ችሎታ ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነውና ፤ ገበሬው



በእግዚአብሔር አምኖ ዘሩን ከጎተራ አውጥቶ ይዘራል ፣ ነጋዴው በእግዚአብሔር አምኖ ወረቱን ሁሉ ከመዝገቡ አውጥቶ ይነግዳል ፤ ሁሉም በእግዚአብሔር ስም ስለሚያደርጉት እንደ ዓላማቸው እንደ ጀመሩትም ይፈጽሙታል ፤ መልካም ውጤትንም ያገኛሉ ።

ካህኑ ግን በበለጠ ለራሱም የሥራ ውጤትን ያገኘ ዘንድ ፣ ለሌላውም ያስተምር ዘንድ የጐላ የጸና ሃይማኖት እንዲኖረው ያስፈልጋል ፤ ስለዚህ የጸና ሃይማኖት የካህኑ የተለየ መታወቂያ ምልክቱ ይሆናል ።

፪ኛ/ ፍጹም ፍቅር በክርስቶስ ፡— ክርስቶስ በሰው ልጅ ላይ ያለውን ፍቅር ከከፍተኛ ዙፋኑ በመውረድ ፣ ከድንግል ማርያም በመወለድ ፣ ፍጹም ሰው ሆኖ በመታየት ገልጦታል ፤ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ወጣ ወረደ ፣ ሰው የሆነውን ሁሉ ሆነ ከኃጢአት በቀር ።

እንዲሁም ፍጹም ፍቅሩን ሕይወቱን በሞት በመለወጥ ገለጠው ፤ የሰውን ልጅ ለማዳን እርሱ ሞተ ፤ የእርሱን ሕይወት ለኛ ሰጠ ፤ የኛን ሞትም እርሱ ሙቶ እኛን አዳነን ።

የክርስቶስ ፍቅር በዚህ ዓይነት ሲገለጥ የክርስቶስ ተከታይ የሆነው ካህን ፤

፩/ በክርስቶስ ዘንድ ያለው ፍቅር ፍጹም መሆን አለበት ፤ ማለት በመከራ በችግር የማይለወጥ መሆን አለበት«ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው ፣ ሞት ቢሆን ፣ ሕይወትም ቢሆን ፣ መላእክትም ቢሆኑ ፣ ያለው ቢሆን የሚመጣውም ቢሆን ፣ ኃያላትም ቢሆኑ ፣ ከፍታም ቢሆን ፣ ዝቅታም ቢሆን ፤ ያለው ቢሆን ልዩ ፍጥረትም ቢሆን ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቻለሁ» (ሮሜ፡ ፰ ፡ ፴፱) ።

እንዲሁም ካህኑ በምእመናኑ የተወደደና ምእመናኑን የሚወድ ስለነርሱም ሕይወት የሚያስብ ፣ የሚናገር ፣ የሚሠራ መሆን አለበት ። እንዲያውም ከዚህ አልፎ መሥዋዕት ሆኖ የሚቀርብ መሆን አለበት ፤ ካህኑ የምእመኑ እውነተኛ ጠባቂ ተከባካቢ እንደመሆኑ በምእመናኑ ላይ በሚደርስባቸው ችግር ሁሉ ተካፋይ መሆን እንዲያውም በእነርሱ እግር ገብቶ ታዳጊነቱን ማሳየት አለበት ።

እውነተኛ ጠባቂ ራሱን ለመንጋው አሳልፎ ይሰጣል ፤ ምንደኛው ግን በጎቹም የእርሱ ያልሆኑ አውሬ ሲመጣ ባየ ጊዜ ጥሎ ይሸሻል ሲል ክርስቶስ በወንጌል ቃሉ አስረድቷል ፤ (ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፲፩—፲፫) ።



www.ethiopianorthodox.org

በመጀመሪያ አንድ ሰው ካህን የሚሆነው ክርስቶስ የሞተለትን መንጋ ለመጠበቅ ፥ ከሞትም ለማዳን ቆርጦ ሲገባ ነው ፤ እንዲህ ካልሆነማ ለምን ካህን ይሆናል !

ለራሱ ብቻ ክብርን ሲሻ ካህን የሚሆን ሰው ዓላማ ቢስ ነው ለማለት ይቻላል ።

ክርስቶስ በደሙ የዋጃትን ቤተ ክርስቲያን እንዲጠብቅ መንፈስ ቅዱስ ካህናትን የሁሉ መሪዎች አድርጎ አስነሣቸው፤ሾማቸው ፤ ስለዚህ ዛሬም ካህን የሚሆነው ሁሉ ይህን ዓላማ ተከትሎ የሚሠራ መሆን አለበት (የሐ ፡ ሥራ ፡ ፳ ፡ ፳፰) ።

ፍጹም ፍቅር የክርስቶስ ተከታይ ለመሆን የሐዋርያነትም አገልግሎት መታወቂያ ምልክት ነው ፤ እንግዲህ ይህ ምልክት የሌለው ሰው ካህን መሆን ቀርቶ ክርስቲያንነቱም ያጠራጥራል ማለት ነው ።

ካህን የሚሆን ፍጹም ፍቅር እንዲኖረው ማስፈለጉን ይኸም እውነተኛ መታወቂያ መሆኑን ክርስቶስ ሲያመለክት «አዲስ ትእዛዝ ሰጣችሁ እርስ በርሳችሁ ትፋቀሩ ዘንድ እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ ደቀ መዛሙርቴ እንደሆናችሁ ሁሉም ያውቃችኋል ሲል ተናግሯል (ዮሐ ፡ ፲፫ ፡ ፴፬) ።

ፍቅር የሌለው ሰው ካህን መሆን ቀርቶ ክርስቲያንነቱ እንኳን ያጠራጥራል ፤ የክርስቶስ ተከታይ የሚሆነው በምንድን ነው ? በስም ወይም በልብስ ? እውነተኛው ካህን ክርስቶስን በግብር ይከተለዋል፤ ይመስለዋል፤ እውነተኛ ካህን መሆኑም በዚህ ይታወቃል ።

ክርስቶስ ቅዱስ ጴጥሮስን ሲሾመውና እንደገናም የሐዋርያነት ማዕርጉን ሲሰጠው የፍቅር ምልክት አይቶ ነው ፤ ማለት ሦስት ጊዜ ትወደኛለህ ? እያለ አዎን ሲለው በጎቼን፤ጠቦቶቼንም ፤ ግልገሎቼንም ጠብቅ እያለ ከፍቅሩ የተነሣ ጠባቂ እንዳደረገው እናውቃለን (ዮሐ ፡ ፳፩ ፡ ፲፭—፲፯) ።

ሌሎችንም ሐዋርያት እርሱ እንደወደዳቸው እስከ መጨረሻው እንዳፈቀራቸው ራሱ ጌታችን ገልጦ ተናግሮ እናገኘዋለን ፤ ስለዚህም ሐዋርያትን ጠባቂዎች አስተማሪዎች አደረጋቸው (ዮሐ ፡ ፲፫ ፡ ፩) ።

ሥራው ሁሉ የሚፈጸመው በፍቅር ነው ፤ ባልንጀራችንን ከወደድነው ሀብቱን ሕይወቱን አናጠፋም ፤ ስሙንም አናጠፋም ፤ አደራውን እንጠ



ብቃለን፤እንደዚህም ሁሉ ክርስቶስን ከወደድነው አካሉ የሚሆነው የምእመን ሕይወት ሲጠፋ ዝም አንልም ፤ የክርስቶስ ስም እንደጠፋ ያስቆጥራልና ። ክርስቶስን ከወደድን መንጋው ሲበተን ዝም አንልም ፤ እንዲሁም እርስ በርሳችንም ስንፋቀር ቤተ ክርስቲያናችን አትወድቅም ። ካህኑ ተልእኮውን ሊፈጽም የሚችለው እንከን የሌለበት ፍቅር በሰውም በእግዚአብሔርም ላይ ያለው እንደሆነ ነው ።

፫/ <u>ፈሪሃ እግዚአብሔር</u> ፡— ፈሪሃ እግዚአብሔር ለካህኑ ቀርቶ ለማንኛውም አማኒ አስፈላጊ ነው ፤ ማለት አምላክን እርሱ ፈርቶ አክብሮ ለሌላው የሚያስተምር የሚያሳምን ነውና ። ፈሪሃ እግዚአብሔር ስንልም እግዚአብሔር ይገድለኛል ያጠፋኛል በሚል ፍርሃት የሚፈራ ማለት አይደለም ፤ እግዚአብሔር አባታችን ስለሆነ ከበጎ አድራጊነቱ ፤ ከጸጋ ሰጭነቱ የተነሣ እናከብረዋለን ፤ ከውለታውም የተነሣ እንፈራዋለን ፤ እንዴት እርሱ ሲወደን እኛ እንጠላዋለን !

ጨካኝና ፈራጅ መሆኑን ዐውቀው የሚፈሩት ጠላትን ብቻ ነው ፤ ጠላት ምሕረትና ርኅራኄ የለውምና ። እንግዲህ እግዚአብሔርን በዚህ መልክ የምንፈራው ከሆነ ጠላቶቹ ነን ማለት ነው ፤ ግን እንዲህ አይደለም ሊሆንም አይገባም ። ከቸርነቱ ከምሕረቱና ከይቅር ባይነቱ የተነሣ አባታችን ብለን አባታችንም አድርገን እንቀበለዋለን እናከብረዋለን ፤ ሕጉን እንጠብቃለን ትእዛዙን እናከብራለን ።

ሁል ጊዜ የሚከብድ የወዳጅ ጥል ነው ፤ ስለዚህ የአባታችን የእግዚአብሔር ሕግ ማፍረስ ፤ እርሱንም ቸል ማለት ያሳዝናል ያስፈራል፤ ይኸን ካህኑ በሚገባ ያወቀ የጠበቀ መሆን አለበት ።

ፈሪሃ እግዚአብሔርን ገንዘብ ካደረገ ማንም ቢሆን አይበድልም ፤ ከሕጉ አይናወጥም ፤ በዋዛ በፈዛዛ ጊዜውን አያሳልፍም ፤ ግንኙነቱንም ከእግዚአብሔር ጋር አያቋርጥም ። በተለይ ካህኑ ፈሪሃ እግዚአብሔርን ገንዘብ ያደረገ እንደሆነ ሥራው ሁሉ ይከናወንለታል ፤ እንደ ዓላማው ተልእኮውን ለመፈጸም ይችላል ።

፬/ <u>መንፈሳዊ ቅንዓት</u> ፡— ካህኑ ለእግዚአብሔር አምልኮና ለሕጉ ለሥርዓቱም የሚቀና የሚቆረቆር መሆን አለበት ፤ በዚህም መለዮ ካህኑ መታወቅ መገመት አለበት ። ቅ/ሐዋርያት የክርስቶስ ውለታ ፤ የክርስቶስም ሥራ እየታሰባቸው መንፈሳዊ ቅንዓት እንደ እሳት እያቃጠላቸው በዓለም ተበትነው ያለይሉኝታ እየመሰከሩና እየሰበኩ ሕይወታቸውን አሳ



www.ethiopianorthodox.org

ለፉ ፤ ራሱ ክርስቶስ «ቅንዓተ ቤትክ በልዓኒ» ያለውን ቃል ተከትሎ ቤተ መቅደሱ በተሠራበትና በሚገባው አገልግሎት ሳያውል ባገኘው ጊዜ ሊታገስ አልቻለም ፤ ስለዚህ በውስጡ የሚሸጡትን የሚሸፍጡትንም ሁሉ ከቤተ መቅደስ አስወጣ ፤ ለአባቱ ቤት ለአባቱም ሕገጋት ቀናተኛ መሆኑን በሥራም በቃልም ገለጠ ።

አሁንም አንድ ካህን መንፈሳዊ ቅንዓት ከአለው ኩቶ አያመነታም ፤ ቸልም አይልም ሕገ እግዚአብሔርን ራሱ ጠብቆ ለሌሎች እንዲጠብቁ ያስደርጋል ። ምን ቸገረኝ በማለትና የምን ግዴ የሚሠራው መንፈሳዊ ቅንዓት የሌለው ካህን እንደሆነ ይታወቃል ፤ እንደዚህም ያለው ሁሉ የዕለት ጥቅሙንም ብቻ ይመለከታል ።

በዕለት ጥቅም የሚደለሉ እንስሳት ብቻ ናቸው ፤ ምክንያቱም እነርሱ የማሰብ የማመዛዘን ችሎታ የላቸውምና ፤ የዕለቱን በልተውና ጠጥተውም የማደር ፈቃድ ብቻ አላቸውና ።

ሰው ግን በተለይም ካህኑ ሁሉን አርቆ የሚመለከት መሆን አለበት፤ እንዲያውም የዚህን ዓለም ብቻ ሳይሆን የወዲያኛውን ዓለም ተስፋ የሚያደርግ ስለሆነ የሚያስበው ፣ የሚናገረው ፣ የሚሠራው በዚህም ዓለም በወዲያኛውም ዓለም ለሚሆነው ነውና ።

፫/ ንጽሕና ፡ ቅድስና ፡—የእግዚአብሔር አገልጋይ የሆነ ካህን ከሁሉ በበለጠ ንጽሕናን ቅድስናን ገንዘብ ያደረገ መሆን አለበት፤ምክንያቱም፡—

፩ኛ/ ካህኑ እግዚአብሔርን የሚያገለግል ስለሆነ ከእርሱ ለመቅረብ የሚችል ተልእኮውንም የሚፈጽም ንጹሕ ቅዱስ የሆነ ነውና ።

፪ኛ/ ሕዝቡን የሚያነጻ የሚቀድስ ነውና ፣ አስቀድሞ እርሱ ንጹሕ ቅዱስ መሆን አለበትና ።

ካህኑ ከተልእኮው አንደኛው በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አማካይነት ሕዝቡን ማንጻት መቀደስ ነው ፤ ታዲያ ሌላውን የሚያነጻውና የሚቀድሰው ካህን እርሱ ካልነጻ እንዴት ሌላውን ሊያነጻ ይችላል? እንዲያውም የበለጠ እንዳያሳድፍ ያሰጋል ። ሌላውን በደል ሁሉ ካህን ይቅር ሲል ይቅርታም ሲያደርግ የክህነት ማዕርግ ግን ከአደፈ ከተጓደፈ በኋላ ይቅርታ የሌለው በመሆኑ አስቀድሞ በንጽሕና ለመያዝ ትልቅ ጥንቃቄ ያስፈልጋል ።



ቅዱስ እግዚአብሔር በቅድስናው ለዘለዓለም የሚኖር ነው ፤ ስለ ዚህ የሰው ልጅ ሁሉ ቅዱስ ይሆን ዘንድ «ኩኑ ቅዱሳነ እስመ አነሂ ቅዱስ «ሲል በብሉይ ኪዳን አዟል (ዘሌዋ ፡ ፲፩ ፡ ፵፬) ። ቅዱስ ጴጥሮስም ክርስቲያኑ ሕዝብ ሁሉ በንጽሕና መኖርምንጽሕናን ገንዘብ ማድረግ ተገቢ መሆኑን በመግለጥ ይኸንኑ ትምህርት በመድገም ተናግሯል (፩ ፡ ጴጥ.፩. ፲፮) ።

ቅድስና የካህኑ የተለየና ከሁሉም የበለጠ መታወቂያ መመዘኛም መገመቻም ነው ። ሥልጣነ ክህነት የተዋሐደው ፣ የማሠር የመፍታት ኃይል እንዳለው የሚታወቅበት ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት የሚያደርግበት ፣ የሚታይበት ፣ ንጽሕናው ቅድስናው እንደሆነ መድኃኒታችን ኢየሱስ «ብፁዓን ንጹሓን እስመ እሙንቱ ይሬእይዎ ለእግዚአብሔር» ሲል አስረድቷል (ማቴ ፡ ፭ ፡ ፲) ።

ይኸንንም መሠረት አድርጎ አባ ሕርያቆስ «እስመ በአንጽሖ መንንፈስ ርእይዎ ነቢያት ለእግዚአሙ» ሲል ተናግሯል ፤ (ቅዳሴ ማርያም) ።

ካህኑ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርበው ሌላውንም ምእመን ሊያቀርበው የሚችል ንጽሕና ቅድስና ያለው እንደሆነ ነው ፤ ክህነታዊ ተልእኮውን ሁሉ የሚያከናውነው ንጽሕናን ቅድስናን ገንዘብ ያደረገ እንደሆነ ነው ፤ ያለዚያ ክንፉን እንደተሰበረ መብረርም እንደሚሳነው አሞራ ተግባሩን ሁሉ ለማከናወንና ግዳጁን ለመፈጸም የማይችል ሆኖ ይኖራል ።

፬/ ፍጹም ዕውቀት ፡— ምንም ከሰው ወገን ሙሉና ፍጹም ዐዋቂ ባይኖር ካህኑ ከማንኛውም ሰው የተለየና የተሻለ ዕውቀት ሊኖረው በግድ ያስፈልጋል ፤ ምክንያቱም ሁሉንም የሚመክር ፣ ሁሉንም የሚያስተምር ነውና ።

እንዲያውም የካህን ዕውቀት እጥፍና ድርብ መሆን አለበት ፤ ማለት ማንኛውም ሰው የሚያውቀውን ሁሉ ሰው እንደመሆኑ ከሰው ጋርም እንደመኖሩ ማወቅ ግድ አለበት ፤ ያለዚያ ከማኅበሩ ይለያል ፤ ከሰው ተራ ይወጣል ፤ ከዚህ በተለይ ግን ፤

ሀ/ የተለየ ዕውቀት ፡ —ለካህኑ የተለየ ዕውቀት ያስፈልገዋል ፤ ይኸውም ቴዎሎጂ የተባለው ጥናት ነው ። ለካህኑ ተገቢ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ ሳያውቅ ፣ በእነርሱም ሳይጸና ካህን መሆን የለበትም ። ዓላማውን ሳያውቅ ለምንም እንደ ተሠለፈ ምንም ማድረግ እንዳለበት ሥራውም ምን ዓይነት እንደሆነ ሳያውቅ የተሰለፈ ከሆነ በምንም መልክ ተል



www.ethiopianorthodox.org

እኮውን ሊፈጽም አይችልም ። እንግዲህ ለራሱ የማያውቅ ለሰው ምን ሊያደርግ ይችላል ተብሎ እምነት ይጣልበታል ! እንዴትስ በኃላፊነት ቦታ ይቀመጣል ! ስለዚህ ካህኑ የተለየ ዕውቀት የተለየም ትምህርት በግድ ያስፈልገዋል ።

ካህንም የሚባለው ካህንም የሚያሰኘው የካህኑን ሞያ በመያዙ በካህኑ ቦታ በመገኘቱ ነው እንጂ በምእመንነት እያለ ካሀን ሊሆን ወይም ሊባል አይችልም ፤ እንዲህስ ከሆነ እንዴት አድርጎ ሌላውን ሊመራ ይችላል !

እንግዲያውስ «ዕውሩን ዕውር ቢመራ ገደል ይገባል ሁሉም በየተራ» እንደተባለው ሁሉም ከድኅነት ውጭ ይሆናሉ ።

ስለዚህ ካህን የሆነ ሁሉ የተወሰኑትን የትምህርት ዓይነቶች ሁሉ ጠንቅቆና አጠቃሎ መማርና ማወቅ አለበት ።

ለ/ <u>ጠቅላላ ዕውቀት፤</u> — ዘመኑ የሳይንስ ዘመን እንደመሆኑ ካህኑ ተጠያቂ እንጂ ጠያቂ ሆኖ እንዳይገኝ ዘመኑ ያፈራውንም ዕውቀት ሁሉ በመጠኑም ቢሆን ያወቀ መሆን አለበት ።

ሰው በዕውቀት ኃያላኑን አራዊትንና እንስሳትን ይገዛል ፤ ይኸም የተፈጥሮ ዕውቀቱ ነው? በበለጠ በትምህርት ዕውቀት የተራቀቀ ከሆነ ሰውን ይገዛል፤ሰውን እጅ ያደርጋል ፤ ያለዚያ እርሱም ይማረካል ፤ ለሌላ አድማቂ የሌላም ተላላኪ ይሆናል ፤ ስለዚህ ካህኑ ዕድሜውን ሙሉ ሲማር መኖር አለበት ።

እነዚህ ነገሮች በካህኑ ጉልተው ሊታዩ መታወቂያውም ፥ መለያውም ሊሆኑ ይገባል ።

እነዚህ መታወቂያዎች ካሉት እርሱም ሳይፈራ ሳያፍር ተግባሩን ሊያከናውን ይችላል ፤ ምእመናኑም በሁኔታው አምነው ቃሉን ይሰማሉ ፤ ትእዛዙን ይከተላሉ ፤ እውነተኛ አባት አድርገው ይይዙታል እግዚአብሔርም የሥራው ሁሉ ረዳት ይሆነዋል ፤ ስለዚህ እንደ ዓላማው ተግባሩን በመፈጸሙ ተደስቶ ይኖራል ።

የካህኑ ሀብት የካህኑም የደስታ ሕይወት የሚሆነው የገባበትን ግዴታ መወጣትና የሥራውም ሁሉ መቃናት ነውና ። እንግዲህ ካህኑ ምን መሆን እንዳለበት ካህን የሚባለው የትኛው እንደሆነ መለያው ምን እንደሆነ ተረዳን ።



# ክፍል ፪ ሥርዓተ አምልኮ

የምእመናን ጠባቂ (አበ ነፍስ) የሚሆነው ካህኑ የመጀመሪያ ተግባሩ በጸሎት ጽሙድ መሆን ፤ ለቅዱስ አምላክ ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብ ፥ ለምእመናን ሕይወት ሰላምና ጤንነት ምልጃ ፤ ስእለትና፤አስተብቍዖት ማድረግ ነው ። ይኸንንም ተግባር ጊዜና ሰዓት ጠብቆ ማቅረብ መፈጸም ዋና የካህኑ ተልእኮ ነው ።

ቅዱስ ጳውሎስ ተወዳጅ ደቀ መዝሙሩን ጢሞቴዎስን ለኤፌሶን ሀገረ ስብከት ጠባቂ (አበ ነፍስ)አድርጎ ሲልከው ከሁሉ በፊት ጸሎት ፥ ስእለትና አስተብቍዖት፥ ምልጃም እንዲያደርግ ከፍተኛ ማስጠንቀቂያን ሰጥቶ ነው ። እርሱንም እንዲሁ ሲል ይገልጠዋል ፤ «እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰል በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር ልመናና ጸሎት ፥ ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ» እንዲደረግ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ - - - (፩ ጢሞ ፥ ፪ ፥ ፩—፬) ።

አምልኮተ እግዚአብሔር ስንልም ብዙ መልክ ያለውና በብዙ መልክ የሚፈጸም ስለሆነ ካህኑ ግዴታው መሆኑን ዐውቆ ተግቶ ነቅቶም መፈጸም አለበት ፤ አምልኮተ እግዚአብሔር በመጠኑም ቢሆን በጸሎት ፤ በምጽዋት ፥ በስግደት ፥ በጾም ፥ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንንም በመፈጸምና ይኸን በመሳሰለው ሁሉ ይፈጸማል ። እንግዲህ እነዚህ እያንዳንዳቸው እንዴት እንደሚፈጽሙ በሚከተለው መልክ እንዘረዝራለን ።

ሀ/ <u>ጸሎት፡—</u> ጸሎት ራሱ በ፫ ይከፈላል ፤

፩/ <u>ምስጋና፡—</u> ምስጋናም ማለት አምላክ አማልክቱን ፥ ንጉሠ ነገሥቱን እግዚአብሔርን በማንኛውም ጊዜ ፤ በማንኛውም ምክንያት ያለ ማቋረጥ ማመስገን ነው ። ሰው የተፈጠረው ለምስጋና ስለሆነ ሰው ሁሉ ትንሹም ትልቁም እንደ የችሎታው ለአምላክ ምስጋና ማቅረብ ፥ ተገዥነቱንም መግለጥ ግድ አለበት ፤ ለዚህም አብነት የሚሆነው ካህኑ ስለሆነ ፥

፩ኛ/በአስተማሪነቱ ፥ ፪ኛ/ በግሉ ለራሱ ጸሎት ማድረግ አለበት ፤ መጀመሪያውም ተልእኮው ይኸው ነው ።

ማንኛውም ሰው ቢያዝንም ቢደሰትም፤ መንገድ ቢሄድም፤ ቢቀመጥም፤ አምላኩ ምስጋና ማቅረብ አለበት ፤ በተለይም የሕዝብ ጠባቂ የሆነው ካህኑ እንደመላእክት ለእግዚአብሔር ምስጋና ሁል ጊዜ ማቅረብ አለበት ።



www.ethiopianorthodox.org

ካህኑ ከሕዝቡ የሚለይበት ፣ የሚታወቅበትም ጸሎተኛነቱ ፣ በጸሎት ከእ
ግዚአብሔር ጋር መገናኘቱ ነው ፤ ምክንያቱም ተልእኮው ለዓለማዊ ግብር
ሳይሆን ለመንፈሳዊ ተግባር ነውና ። ጸሎትም ሲያደርግ በመጀመሪያ ለእግ
ዚአብሔር ምስጋና በማቅረብ ፡ ውለታውን በመናገር መጀመር አለበት ።

ጌታችን ኢየሱስ ጸሎት በአስተማረ ጊዜ በመጀመሪያ ምስጋና
ማቅረብ እንደሚገባ እንዲህ ሲል አስተምሯል «አባታችን ሆይ በሰ
ማያት የምትኖር ፣ ስምህ ይቀደስ ፣ መንግሥትህ ትምጣ ፣ ፈቃ ድህ በሰ
ማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን» (ማቴ ፡ ፮ ፡ ፱—፲ ።

እንግዲህ እኛም የእርሱን ፍለጋ የተከተልን በየጊዜው ንጹሕ ምስ
ጋና ለአምላካችን ማቅረብ አለብን ። የሕዝቡ ጠባቂ የሆነው ካህኑ ይቅርና
ማንኛውም ሰው በደስታም ላይ የሆነ፤ማለት በጫጉላ ያለ ሙሽራም ቢሆን፤
በኃዘንም ላይ ያለ ሰው ቢሆን ፣ በኀዘን በችግርም ያለ ቢሆን፤ለምሳሌ በግ
ዞትም በእሥራትም ላይ ያለ ቢሆን፤ሰው የተፈጠረው ለምስጋና መሆኑን
ዐውቆ አምላኩን ያመሰግን ዘንድ ግዴታ አለበት ። ንባብና
አእምሮ ያለው ሰው ቀርቶ ሌላው ግዑዝ ፍጥረት የሆነው ሁሉ ለእግዚአ
አብሔር ምስጋና እንዲያቀርብ ቅ-መጽሐፍ ይናገራል (መዝ ፡ ፲፱ ፡ ፩)።

፪/ልመና፡--ሁለተኛው የጸሎት ክፍል ምልጃ ፣ ልመና ነው ። ይኸም
መጀመሪያ ስለራስ ፣ ቀጥሎ ስለ ሕዝቡ (ስለሚጠብቃቸው) በአጠቃላይም
ስለ ዓለም ሰላም ሁሉ መለመን አለበት ፤ ግዴታ ተግባሩም ነው ። የእግዚ
አብሔር ወኪል የሆነው ካህኑ ከምልጃ ከልመና ፣ ከጸሎት ወደኋላ ማለት
ከቶ የለበትም ፤ ከእርሱ ጸሎትና ምልጃ የተነሣ አምላክ ለሕዝ ቡ ይቅርታ
ውን ለማድረግ ፈቃደኛ ነውና ። «ለምኑ ይሰጣችኋል ፤ እሹ ታገኛላችሁ
ውን ለማድረግ ፈቃደኛ ነውና ። «ለምኑ ይሰጣችኋል ፤ እሹ ታገኛላችሁ
ደጅ ምቱ ይከፈትላችኋል» ሲል የተናገረ አምላክ እውነተኛ ስለሆነ ከእ
ርሱ ስለማይቀር የለመነውን እናገኝ ዘንድ ልመናችንን በሰፊው ማቅረብ
አለብን (ማቴ ፡ ፯ ፡ ፯) ።

እኛ ከቸልተኝነታችን የተነሣ ጸሎት ባለማድረጋችን ከአልቀረብን
በቀር ከአምላክ ዘንድ አንድም የሚቀርብን ነገር የለም ፣ ስለዚህ ሁሉን
የሚያውቅና እኛ የምናውቅበትን አእምሮ ፤ የምንሰማበትን ጆሮ የፈጠረ
አምላክ ልመናችንን ሰምቶ ሁሉንም ዐውቆ ፤ የጠየቅነውን ሁሉ ይፈጽም
ልናል ።

ልመና ማቅረብ እንደሚገባን ከጸሎታችን ውስጥ ፪ኛው ክፍል
ልመና መሆን እንደሚገባ ክርስቶስ አስተምሯል ፤ እርሱም እንዲህ ይላል
«የዕለት እንጀራችንን ስጠን ለዛሬ ፣ በደላችንንም ይቅር እንድትለን



እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል ወደፈተናም አታግባን ከክፉ አድ
ነን እንጂ» ጌታ የልመናውን መልክ በዚህ ለይቶ አመልክቶ እናገኘዋለን
(ማቴ ፡ ፮ ፡ ፲፱—፲፩ )።

በዚህ መልክ ለተለያዩ ሰዎች ፤ ስለተለያዩ ችግሮች መለመን ይቻላል ።
በተለይ ግን ሁል ጊዜ ስለ ሰው ልጅ ደኅንነት ፣ ስለዓለም ሰላም መለመን
የካህኑ ተልእኮ ነው ። ይኸም ለሰው ልጅ ሁሉ ተገቢ ሲሆን ካህኑ በበ
ለጠ ስለ ራሱም ፣ ስለቤተሰቡም ፣ ስለምእመናኑም ፣ ስለ ሀገሩና በጠቅላ
ላው ስለ ኅብረተሰቡ ሁሉ ምልጃ ፤ ስእለትና አስተብቁዖት ማድረግ
ግዴታው ይሆናል ።

እንግዲህ ካህኑ በዚህ መልክ በጸሎት ጽሙድ እየሆነ ሌላውም እን
ዲህ እንዲሆን ማስተማርና መምከር ግዴታው ነው ። እርሱም ራሱ ንጹሕ
የሚሆነው ፣ የሌላውንም በደል የሚያነጻው በስእለትና በአስተበቊዖት
በምልጃም በጠቅላላም በጸሎት ተልእኮውን የፈጸመ እንደሆነ ነው ።

ጸሎት የካህኑ የተለየ ቀዳሚ ተግባሩ ነው ፤ በዚህም ምክንያት ሁል
ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ያልተቋረጠ ግንኙነት ይኖረዋል ፤ ጸሎት የሰውና
የእግዚአብሔር ግንኙነት መግለጫ ወይም ውይይት ነው ። ሰው እግዚአ
ብሔርን በጸሎት ይጠራዋል ፤ ችግሩን ገልጦ ይነግረዋል ፤ ዋይታውን
ያካፍለዋል ፤ እግዚአብሔር ደግሞ ጩኸቱን ይሰማዋል ፤ ጸሎቱን ይቀበ
ለዋል ፤ ስለዚህ ፣ ይረዳዋል ፣ ግዳጁንም ይፈጽምለታል ።

፫/ ምስጋና (መደምደሚያ) ፡ —እንደገና እግዚአብሔርን ስለ ውለ
ታውና ስለበጎ አድራጎቱ ያመሰግናል ፤ ምክንያቱም የለመኑትን የማይነሳ
የነገሩትን የማይረሳ ፣ ዝቅተኛም ነው ብሎ ማንንም ሰው ቸል የማይል አም
ላክ እውነተኛ አባት ነውና ።

እግዚአብሔር ኃያልና ገናና ሲሆን ግንኙነቱን ከደካማው ከሰው
ጋር ያደረገው ስለ ቸርነቱ ነው ፤ ግን የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን ኃይል
በመግለጥ ፣ ገዥነቱንና አስተዳዳሪነቱን በመመስከር ምስጋና ያቀርብለ
ታል፤ይኸንንም ጌታ ራሱ ሲያስተምር «መንግሥት ያንተናትና፤ኃይልም፣
ምስጋናም ለዘለዓለሙ አሜን»ሲል ገልጦ አስተምሯል(ማቴ፡ ፮ ፡ ፲፫) ።

በዚህ መልክ የተዘጋጀ ወይም ይኸን የመሰለ ጥንታዊም አዲስም
የጸሎት ሥነ ሥርዓት ይዞ (ተከትሎ) ካህን ሁልጊዜ መጸለይ አለበት፤ሕዝ
ቡንም ማስተማር አለበት ። ሕዝቡን ለማንጻት ፣ ለማጽናት ከክፉ ነገርም
ሁሉ ለመጠበቅ ካህኑ በምንም መልክ የማያቋርጥ ጸሎት መጸለይ አለበት።



www.ethiopianorthodox.org

ማንም ሰው ሳይታክትና ሳይሰለች ሳያቋርጥም መጸለይ እንዳለበት ጌታ ሲያስተምር በመበለቲቱና በጨካኙ ፈራጅ መስሎ ተናግሯል(ሉቃ ፲፰ ፩—፲፡) እንግዲህ ከላይ በተገለጸው የጸሎት ሥነ ሥርዓት ዓይነት በተለ ያዩ ሰዓቶች ማንኛውም ሰው መጸለይ እንዳለበት ተናግረናል ፤ በተለይ ግን ካህኑ ሕይወቱ በጠቅላላው ከጸሎት ጋር የተያያዘ ስለሆነ ሁል ጊዜ በጸሎት ጽሙድ መሆን አለበት ።

ከአምልኮት ሥርዓት ውስጥ የሚገቡ በእርሱም አማካይነት ጸሎትና ስእለት አስተብቍዖትም የሚፈጸምባቸው ፤ ጸጋ ፣ በረከት ፣ ልጅነት ፣ የሚሰጥባቸው ፣ ድኅነተ ሥጋና ድኅነተ ነፍስ የሚገኝባቸው ፯ቱ የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት ተብለው የሚጠሩት ናቸው ።

ካህኑ እነዚህን በየጊዜው ሲፈጽም የጠባቂነቱ ቀንበር ኃፊነቱም ይወገድለታል ። እነዚህም ምሥጢራት ሲፈጸሙ የተለየ ጸሎት፤ ምስጋና ፤ ምልጃም ይደረጋል ፤ በዚህን ጊዜ ካህኑ ለጸሎት ጽሙድ መሆኑን ይገልጣል።

በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንም አፈጻጸም በዕድሜ ፤ በጾታ ፤ በማዕርግ የተለያዩትን ወገኖች ሁሉ ካህኑ ያገኛቸዋል ። በተለያየም መልክ እያንዳንዱ የሰው ልጅ እነዚህን ምሥጢራት ይፈልጋቸዋል ፤ እንግዲህ ካህኑም እነዚህን ለመፈጸም ተገቢ ሆኖ መቅረብ አለበት ፣ ምእመናኑም ይኸን ለመቀበል ተገቢ ሆነው መቅረብ አለባቸው የጋራ ችግራቸውም በዚህን ጊዜ ተወገደላቸው ።

## ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ፣

በአምልኮት ሥርዓት ውስጥ ከፍተኛውን ቦታ ይዘው የሚገኙት ፤ ካህኑም ተልእኮውን በትክክል የሚፈጽምባቸው ፣ ኃላፊነቱን የሚወጣባቸው ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን እየተባሉ የሚጠሩ ናቸው ።

ሕዝቡን ለማንጻት በእምነቱና በትምህርቱ ፣ በሥነ ሥርዓቱም ለማጽናት ፤ አምልኮተ እግዚአብሔርንም በሚገባ ለመፈጸም እነዚህ ምሥጢራት በየጊዜው መፈጸም አለባቸው ።

እንዲሁም እያንዳንዱ አማኒ እምነቱን የሚገልጥባቸው ፣ ከኃጢአት የሚነጻባቸው ፤ በእምነቱ ጸንቶ ለመኖር የሚያስችሉት እነዚህ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ናቸው ።

እነዚህም ምሥጢራት ለሰው ሁሉ የሚታደሉ ናቸው ብንልም ምሥጢር እንደመሆናቸው መጠበቅ በጥንቃቄም መያዝ አለባቸው ፤ ላልመሰሉና ላላመኑ አይሰጡምና ፤ በእምነት እንኳን መስለው በሥነ ምግባራቸው የተለዩ ከሆነ የማይሰጡ ናቸው ።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አክብራ የምትቀበላቸው ፯ቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሚከተሉት ናቸው ።

፩/ ምሥጢረ ጥምቀት
፪/ » ሜሮን
፫/ » ቍርባን
፬/ » ንስሐ
፭/ » ክህነት
፮/ » ተክሊል
፯/ » ቀንዲል ናቸው ።

እነዚህም ፯ቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሰው ልጅ ሃይማኖታዊና ሥነ ምግባራዊ ሕይወቱ የሚደገፍባቸው ናቸው ። እንዲሁም የሰው ልጅነቱ የሚታደስባቸው ፤ ፍጹም መንፈሳዊ ለውጥ የሚያገኝባቸው ማእከሎች እነዚህ ምሥጢራት ናቸው ።

እነዚህ ምሥጢራት በቤተ ክርስቲያን መዝገብነት የሚጠበቁ ሲሆኑ ቤተ ክርስቲያንም በኃጢአት የወደቁትን ታነሣበታለች ፤ የታሠሩበትን ትፈታበታለች ፤ የደከሙትን ታጸናበታለች ፤ በጠቅላላውም ለሰው ልጅ መንፈሳዊ ኃይልን የምትሰጥባቸው የምታስተላልፍባቸውም ናቸው።

ከነዚህም ምሥጢራት አንዱ ከሌላው ሊለይ አይችልም ፤ ፍጹም ድኅነትን ለማግኘት ሁሉንም መፈጸም በግድ ያስፈልጋል ፤ አንዱ ከሌላው ተለይቶ ከተጓደለ ሙሉ መንፈሳዊ ሕይወት ሊገኝ አይችልም፤ ቤተ ክርስቲያንም እያንዳንዳቸውን ምሥጢራት በተለያዩ ጊዜያቶች ለተለያዩ ሰዎች ትፈጽመው እንጂ ፯ቱ ሁሉ መጠበቅ ፣ መፈጸምም በግድ አለባቸው ። ከ፯ቱ ምሥጢራት ውስጥ ፬ቱ በግድ ለሰው ልጅ ሁሉ ያስፈልጋሉ ፤ ማለት ልጅ ነው ትልቅ ነው ፤ ወንድ ነው ሴት ናት ፣ ካህን ነው ፣ የጨዋ ልጅ ነው ሳይባል ለሁሉም በግድ ያስፈልጋሉ ፣ እነርሱም ጥምቀት፣ ሜሮን፣ ቍርባን ፣ ንስሐ ናቸው ።

ማንኛውም ሰው ከሥላሴ ለመወለድ ፣ በዘርም ከወረደው ኃጢአት ለመንጻት ፣ ከብልየትም ለመታደስ በግድ ጥምቀት ያስፈልጋል ።

ከጥምቀትም ቀጥሎ ልጅነቱን ለማጽደቅ ፣ መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል ማኅተመ መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ ሜሮን ይቀባል ። ማንም ቢሆን ጥምቀትን ተጠምቆ ሜሮን ወዲያው መቀባት አለበት ።



www.ethiopianorthodox.org

ጥምቀት መወለድ ፣ ሜሮን ደግሞ መንፈስ ቅዱስን መቀበል ልጅነትን ማረጋገጥ ነው ። የተወለደው ሰው ምግብ ያስፈልገዋል ፤ ስለዚህ ወዲያው ሥጋውንና ደሙን ይቀበላል ፣ ማለት መንፈሳዊ ምግብን ይበላል ፤ መንፈሳዊ መጠጥንም ይጠጣል ። እንዲሁም የተወለደው ሰው በየጊዜው መታጠብ መንጻት ስላለበት ንስሓ ይገባል ፤ ከበደሉም ይነጻል ፤ ስለዚህ በየጊዜው ንስሓ መግባት አለበት ።

እነዚህ ፬ቱ ምሥጢራት በዚህ መልክ በአንድ ጊዜ ይፈጸማሉ ፤ ፩ኛው ከሌላው ተለይቶ ሊቀር አይችልም ።

ሌሎቹ ፫ቱ ምጢራት ግን ክህነት ፣ ተክሊል ፣ ቀንዲል የተባሉት ለተወሰኑ ራሳቸውንም ለዚህ ላበቁ እግዚአብሔርም ለወደደላቸው ሰዎች ብቻ እንጂ ለሁሉ አይሰጡም ። ሁሉ ካህን ሊሆን አይችልምና ፣ ከፍ ያለ መመዘኛ ሊኖር ይችላል፤ ያንን ማለፍ በግድ ያስፈልጋልና ። ከዚህም በቀር በጾታ የሴት ወገን ካህን አይሆንምና። እንዲሁም ሁሉም ሊያገባ አይችልም ጃንደረባ ሆነው የሚወለዱ አሉና ፣ ሰው ጃንደረባ ያደረጋቸውም አሉና ፣ ራሳቸውንም ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ፣ ስለ ወንጌል ትምህርትም ሲሉ ጃንደረባ ያደረጉ ይገኛሉና (ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፲፪ ።)

ከነዚህም ምክንያቶች በቀር ቤተሰብን የማስተዳደር ችሎታ ፣ ሥራን የመሥራት ፈቃድና የመውጣትም የመውረድም ኃይልን ይጠይቃልና ። ሚስት አግብቶ ቤተሰብን መሥርቶ እንዲሁ መተው ተገቢ አይደለምና ፣ የሚያገቡ ሁሉ ይኸን መቻል አለመቻላቸውን ማመዛዘን በግድ ስላለባቸው ሁሉም ሊያገባ አይችልም ።

ሰው ሁሉ ሊታመም ስለማይችል ጸሎተ ቀንዲልም ለሁሉ አይፈጸምም ፣ በመንፈስ ወይም በሥጋ ደዌ አድሮባቸው ፤ በሽታ ጸንቶባቸው ጸሎተ ቀንዲል እንዲፈጸምላቸው ከጠየቁ በቀር ለሰው ሁሉ እንዲሁ አይፈጸምምና ።

ከነዚህ ከ፯ቱ ምሥጢራት ውስጥ በየጊዜው እየተደጋገሙ የሚፈጸሙ አንድ ጊዜም ብቻ የሚፈጸም አለ ፤ አንድ ጊዜ ብቻ የሚፈጸሙ ግን በምንም መልክ የማይደገሙ ናቸው ።

እነርሱም ፡—ጥምቀት ፣ ሜሮን ፣ ክህነት ናቸው ። ጥምቀት አንዲት ናት፣ «ነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለስርየተ ኃጢአት» ሲሉ ፫፻፲፰ ሊቃውንት ወስነዋል ።

ቅዱስ ጳውሎስም «አንድ ጌታ አንዲት ሃይማኖት ፣ አንዲት ጥምቀት» እያለ የጥምቀት አንድነቷን ገልጾ ጽፎአል (ኤፌሶ ፡ ፬ ፡ ፭) ።



አንድ ጊዜ ከተጠመቁ በኋላ ጥምቀት በምንም መልክ አይደገምም ፤ ፍጹም በደል በድሎ እንኳን ቢገኝ ንስሓ ይገባል እንጂ እንደገና አይጠመቅም። ያመነ የተጠመቀ ሁኖ ሳለ ከሃይማኖት ውጭ ሆኖ ቆይቶ ቢመለስም እንኳን ንስሓ ይሰጠዋል እንጂ እንደገና አይጠመቅም ።

ሜሮንም ከጥምቀት ጋር የሚሄድ የልጅነቱ ማጽደቂያ ፤ የመንፈስ ቅዱስ መሰጠት ማረጋገጫ በመሆኑ ወዲያው ከጥምቀት ጋር እንደተሰጠ እርሱው በቂ ነው አይደገምም ።

ክህነትም በዲቁና ፣ በቅስና ፣ በጵጵስና አንድ ጊዜ ከተሾመ በኋላ በዚያው ሥልጣን ላይ አይደገምም ፤ ከዲቁና ወደ ቅስና ፣ ከቅስናም ወደ ጵጵስና ይራመዳል እንጂ በምንም መልክ ቢሆን በዚያው ማዕርግ ላይ አይደገምም ። በአንድ ማዕርግ ላይ ተደግሞ ከተገኘ ሰጭውም ተቀባዩም እንደሚቀጡ የቤተ ክርስቲያን ሕግ ያስረዳል ።

ተክሊል (ጋብቻ) ደግሞ ከሚደጋግሙትም ከማይደጋገሙትም ምሥጢራት ገብቶ ይቈጠራል ።

ከማይደገሙት ምሥጢራት ገብቶ የሚቈጠርበት አንድ ጊዜ ከተጋቡ በኋላ በምንም መልክ መፋታት ፈጽሞ ክልክል ነውና።በነውር ከተፋቱ በኋላ ደግሞ ማግባት በቤተ ክርስቲያን ዘንድ የተከለከለ ነውና ፣ ቤተ ክርስቲያናችንም የምትቀበለው የአንድ ጊዜን ጋብቻ ነውና ።

ከሚደገሙ ምሥጢራት ጋብቻ መግባቱ ከሁለቱ ጾታዎች መካከል ፩ኛው በሞት የተለየ እንደሆነ በሕይወት ያለው የማግባት ፈቃድን ያገኛል፤ እንዲሁም ከባልና ከሚስቱ ፩ኛው የጋብቻውን እምነት ያጎደለ ፣ በደል የበደለ እንደሆነ ፤ የሥነ ምግባር ጉድለት ስላደረገ እርሱ እንደሞተ ተቈጥሮ ላልበደለው ወገን የማግባት ፈቃድ ይሰጣልና ።

እየተመላለሱ ሁልጊዜ ሲደገሙ የሚኖሩ ምሥጢራት ደግሞ ፪ ናቸው ፤

እነርሱም ፩ኛ ቍርባን ነው ፤ እሱም በየዕለቱ ወይም በየሳምንቱ ፣ ወይም በየወሩ መቍረብ ተገቢ ነውና ። እንዲያውም በዓመት ፫ ጊዜ ያህል እንኳን የማይቆርብ ክርስቲያን ነው ሊባል የማይገባው ነው ፤ ስለዚህ ማንኛውም ክርስቲያን ሁል ጊዜ ሲቈርብ መኖር አለበት ።

፪ኛ/ ንስሓ ፤ በየዕለቱ ንስሐ መግባት ለክርስቲያን ሁሉ በጣም አስፈላጊ ነው ፤ የሰው ልጅ ሕይወት አንድ ቀን እንኳን ቢሆን ሳይበድል የሚውል የለምና ፣ እንዲያውም ከተቻለ በጥዋትም በማታም መናዘዝና ንስሓም መግባት ለክርስቲያን ሁሉ በጣም አስፈላጊ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

ለሌላው ምሥጢር ሁሉ ተገቢ ሆኖ ለመቅረብ እንዲችል አንድ ክርስቲያን ሁል ጊዜ ንስሐ መግባት በግድ አለበት። በደሉን ተሸክሞ፤ከምሥጢራት ሁሉ ርቆ የሚኖረው ሰው ሁሉ ክርስቲያን ሊባል ከቶ አይቻልም፤ ስለዚህ ንስሐ እየተደጋገመ ሊፈጸም ይችላል ።

፫ኛ/ ቀንዲል ፤ ቀንዲል የተባለው ምሥጢር ለኃጢአት ስርየትን የሚሰጥ ፡ ለበሽታም ፈውስን የሚያድል በመሆኑ በየጊዜው እየተደጋገመ ይፈጸማል ።

ምሥጢራት ሁሉ ይህንን የመሰለ መልክ ስላላቸው ክርስቲያኑ ሁሉ በየመልካቸው እንደአስፈላጊነታቸው በየጊዜው ሊፈጽማቸው ይገባል ።

## ምዕራፍ ፭/ ምሥጢረ ጥምቀት ፡

ሀ/ የቃሉ ትርጉም ፡ ጥምቀት ማለት መነከር ፡ መዘፈቅ ፡ መጥለቅ ፡ ማለት ነው ፤ በተጠመቅን ጊዜ በማጥመቂያው ቦታ በተባረከው ውኃ ፫ ጊዜ ጥልም ፡ ብቅ እያልን እንጠመቃለንና። ካህኑ ውኃውን በገንዳ አድርጎ የጥምቀቱን ጸሎት ይጸልያል ፤ ይባርከዋል ፤ ያከብረዋል ፤ በዚህ ጊዜ ውኃው ከጌታ ጎን በዕለተ ዐርብ የፈሰሰውን ውኃ ይሆናል ። ከዚህ በኋላ አጠምቀከ በስመ አብ ፡ አጠምቀከ በስመ ወልድ ፡ አጠምቀከ በስመ መንፈስ ቅዱስ ይኩን ስምከ - - -» እያለ ፫ጊዜ እየነከረ ያወጣዋል፤ ይኸ ጥምቀት ይባላል ፤ በውኃው መነከሩ ወደ መቃብር መግባቱን ፡ ከውኃው መውጣቱ ደግሞ የትንሣኤውን ምልክት ይሰጠናል ። ይኸን እየመላለሰ ፫ ጊዜ ማድረጉ በሥላሴ የማመኑ ምሳሌ ፡ ቃሉ ሳይለወጥ ፩ መሆኑ የአንድነት ምሳሌ ነው ።

ጥምቀት የመቃብር ምሳሌ መሆኑን ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ሲል ያስተምረናል« ወይስ አታውቁምን እኛ በኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቅን በሞት እንደተጠመቅን ፡ እንዲህ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን በሞት፣ ክርስቶስ ከሙታን እንደተነሣ በአብ ክብር እንዲሁም እኛ ደግሞ በአዲስ ሕይወት እንሄድ ዘንድ ከእርሱ ጋር የተተከልን ከሆነ በሞቱ ምሳሌ እንዲሁም ደግሞ እንሆናለን በትንሣኤው (ሮሜ ፮ ፡ ፫—፭) ።

መቃብር በመላ ሰውነትን የሚውጥ የሚያለብስም እንደመሆኑ ጥምቀት? ሲጠመቁ በመላ አካልን የሚውጥ አካልንም በመላ የሚያለብስ ውኃ መሆን አለበት ። በባሕረ ኃጢአት ሰጥሞ የነበረው አካል በተባረከው ውኃ ፫ ጊዜ ሰጥሞ ገብቶ ታጥቦ ሲወጣ ይነጻልና ።



እንዲሁም ጥምቀት ፪ኛ ልደት ስለሆነ ገንዳው ማኅፀነ ዮርዳኖስ መሆን ስላለበት ጥምቀቱ ጥልቅነት ባለው ገንዳ መሆን አለበት፤በተባረከው ውኃ በሥላሴ ስም ብቅ ጥልቅ እያሉ መጠመቅ ከሥላሴ ልጅነትን ያስገኛል፤ ከኃጢአትም ያነጻል፤ ልጅነትን ያድሳል። ጌታ ሲያስተምር ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለድን ወደ መንግሥተ ሰማያት እንደማንገባ ገልጾ ይናገራል ፤ እርሱንም እንዲህ ሲል እናገኘዋለን ፤ «ኢየሱስ መለሰ እውነት እውነት እልሃለሁ ማንም ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ይገባ ዘንድ አይችልም» (ዮሐ ፫ ፡ ፫—፭) ።

ለ/ የጥምቀት አመሠራረት ፡ ጥምቀት ለሰው ልጅ ሁሉ አስፈላጊ ከመሆኑ የተነሣ ራሱ ጌታችን ኢየሱስ መሥርቶታል ፤ እርሱም አስቀድሞ ራሱ በእደ ዮሐንስ በማየ ዮርዳኖስ ተጠምቋል (ማቴ፡፫ ፡ ፯—፲ ፡ ማር ፡፩—፲፩ ፡ ሉቃ ፡ ፫ ፡ ፳፩—፳፪ ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፴፪—፴፫)። በኋላ ደግሞ ሁሉ ይጠመቅ ዘንድ ሲያጠይቅ ደቀመዛሙርቱን «ሒዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ ስታጠምቋቸውም በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስም ስም» ሲል አዟቸው እናገኛለን (ማቴ ፳፰ ፡ ፲፱) ።

እውነተኛውን ጥምቀት ሀብተ ወልድና ስመ ክርስትና የሚያሰጠውን እንዲህ አድርጎ ጌታ መሠረተው ። ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለዳችሁ ወደ መንግሥተ ሰማያት ልትገቡ አትችሉም የሚለው አምላካዊ ቃል የሰው ልጅ የሆነው ሁሉ በግድ መጠመቅ እንዳለበት የሚያመለክት ነው።

ክርስቲያን ለመሆን ክርስቲያንም ለመባል ምሥጢራትንም ሁሉ ለመሳተፍ በጠቅላላውም ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመግባት የመጀመሪያው በር ጥምቀት ነው ፤ ስለዚህ ሰው ሁሉ በዚህ በር ማለፍ ግድ አለበት ። ያለጥምቀት ፍጹም ድኅነት እንደሌለ ጌታ ዐውቆ ጥምቀትን መሥርቶታል ። የተጠመቀ ብቻ እንደሚድን ፡ የተጠመቀም ብቻ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሚሆን ጌታ ሲናገር «ያመነ የተጠመቀ ይድናል ፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል» ብሏል (ማር ፲፮ ፡ ፲፮) ።

ሐ/ ለጥምቀት የሚያስፈልጉ አንቀጾች፡— ምሥጢረ ጥምቀትን በትክክል ለመፈጸም ብዙ ነገሮች ያስፈልጋሉ ፤ ይሁን እንጂ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ያለነርሱም ጥምቀት ሊፈጸም የማይችል ፫ ነገሮች አሉ እነርሱም ፡

፩/ እምነት፡— ተጠማቂው ሰው አስቀድሞ የእግዚአብሔርን ሀልዎት መግቦት ማወቅ ማመንም አለበት ። እንዲሁም በባሕርይ በህል



www.ethiopianorthodox.org

ውና አንድ አምላክ ብሎ የሚያምነውን በአካል፤በስም፤በግብር ፫ ብሎ በሥ ላሴ ማመን በግድ ያስፈልገዋል። እንዲያውም የሥላሴ እምነት የተለየ የክር ስቲያኖች እምነት ነው ፤ ስለዚህ ከጥምቀት ጀምረን የሥላሴን ስም እንጠ ራለን ፤ በሥላሴ እናምናለን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እንጠ መቃለን ።

እንዲሁም የወልድን አዳኝነት ፣ የአብ ቃል መሆኑንም ፤ ከአብ አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ መወለዱን፤ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ መሆኑን ማመን ያስፈልጋል ። እንዲሁም «ልጄ የምወደው ይኸ ነው እርሱን ስሙት» ብሎ እግዚአብሔር አብ በተናገረው መሠረት ያስተማረ ውን ፣ የሠራውን ሁሉ ማመን ፣ መቀበል ፣ እርሱንም መከተል በግድ ያስፈልጋል ። ይኸን ሁሉ ለማወቅ ለማመን ትምህርት ስለሚያስፈልግ አዲስ ተጠማቂው አስቀድሞ ይህን ሁሉ ለማወቅ መማር አለበት ፣ እንዲ ሁም ይኸን ሁሉ ዐውቆ አምኖ መጠመቅ አለበት ።

ሳያምን መጠመቅ ግን እንደ መነከር እንጂ ከሥላሴ ለመወለድ አያ በቃም ። በዕድሜ ከፍ ያሉ ይህን ሁሉ አጠናቀው ማወቅ ቀጥሎም ማመን ከዚያም በኋላ መጠመቅ ያስፈልጋል ። በዕድሜ ሕፃናት የሆኑት በወላጆ ቻቸውና በክርስትና አባቶቻቸው እናቶቻቸውም አማካይነት የምናጠምቃ ቸው እነርሱ ዋስ ወይም ተያዥ እየሆኑ ነው ።

እኛው እናስተምራቸዋለን ፣ እኛው ወደ ክርስቲያናዊ ሕይወት እን መራቸዋለን በማለት ተያዥ ሁነው ስለሚገቡ ነው ። ፪ኛ ዕድሜአቸው ለትምህርት ሲደርስ ወደ ት/ቤት ፤ ወደ ቤተ ክርስቲያን እናመጣቸዋለን ፤ ለካህን ፣ ለሰንበት ት/ቤት እንሰጣለን ሲሉ ነው ። ይኸ ካልሆነ ግን አጥማ ቂውም አስጠማቂውም ተጠማቂውም ይፈረድባቸዋል (ማቴ ፳፫ ፣ ፲፭)።

፪ኛ በሥላሴ ስም መጠመቅ ፣ ጥምቀት አስፈላጊ ነው ስንል እንዲሁ ዝም ብሎ ማጥመቅም መጠመቅም አይደለም ፤ በሥላሴ ስም ማጥመቅ እንጂ። ራሱ ጌታ በኔ ስም አጥምቁ ሳይል በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ ብሎ በሥላሴ ስም ማጥመቅን ከፍተኛ አንቀጽ አድርጎ ነግሮናል (ማቴ ፳፰ ፣ ፲፱) ።

በዚህም መሠረት አጥማቂው ካህን ጸሎቱን በሚገባ ከፈጸመ በኋላ «አጠምቀከ በስመ አብ ፣ አጠምቀከ በስመ ወልድ ፣ አጠምቀከ በስመ መንፈስ ቅዱስ» እያለ የሥላሴን ስም እየጠራ ፫ ጊዜ ከውሀው ብቅ ጥልቅ ያደርገዋል ፤ ይኸም አንቀጽ ሊቀር ሊለወጥም የማይችል የማይገባውም ነው ።



፫/ ጥምቀት በውኃ መሆን፡— ማንኛውም ተጠማቂ ሁሉ ሀብት አለኝ ብሎ በማር በወተት በሌላም ቅባት ነክ ነገሮች ሊጠመቅአይችልም፤ ደግሞም አይገባውም፤ በውኃ ብቻ መጠመቅ ግድ ነውና ። ጌታ ራሱ በውኃ ተጠምቋል ፣ እንዲሁም በውኃ ብቻ ማጥመቅ እንደሚገባን ከውኃና ከመ ንፈስ ያልተወለደ መንግሥተ ሰማያትን ሊወርስ አይችልም ሲል ተናግ ሯል (ዮሐ ፣ ፫ ፣ ፫) ።

ሐዋርያትም ሁሉ በውኃ አጥምቀዋል ፤ የኢትዮጵያ ጃንደረባም በውኃ ተጠምቋል (የሐ ፣ ሥራ ፣ ፰ ፣ ፴፰) ።

፬/ በካህን ብቻ መጠመቅ ፣ ማንም ሰው በራሱ ሊጠመቅ አይ ችልም ፣ ያልሆነ ሰውም ሊያጠምቅ አይችልም በደንበኛው ካህን እንጂ ፤

መ/ ለጥምቀት የተወሰነ ዕድሜ፡— ማንኛውም ሰው ያለ ዕድሜ ገደብ መጠመቅ ያስፈልጋል ፤ ምክንያቱም ጌታ የተናገረው አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ አጥምቁ የሚል ነው እንጂ የዕድሜ ፣ የጾታ ፣ የጐሳ ገደብ ከቶ አላደረገም ።

የቤተ ክርስቲያን ሕግ ፍትሐ ነገሥቱም «ጥምቀትም የተሠራ ነው ለወንዶችም ለሴቶችም ፣ ለትንንሾችም ለትልልቆችም» ሲል ማንኛ ውም ሰው ሁሉ ሕፃናትም ሽማግሌም መጠመቅ ግድ እንዳለባቸው ያመ ለክታል (ፍት ፣ ነገ አንቀጽ ፫) ።

ሐዋርያትም በየደረሱበት ሁሉን ያጠምቁ ነበር እንጅ በዕድሜ በጾታ በሌላም መልክ እንደ ነበር የሚገልጥልን የለም ፣ ለምሳሌ ቅ/ጴጥሮስ ቆር ኔሌዎስንና ቤተሰቡን እንዳጠመቀ እናገኛለን (የሐ ፣ ሥራ ፣ ፲ ፣ ፳፫) ። ቤተሰብ ሲል ዕለት ከተወለደ ሕፃን ጀምሮ እስከ ፻ ከዚያም በላይ ዕድሜ ያላቸው ሰዎች ሊገኙ ይችላሉ ፤ እንግዲህ ጴጥሮስ ሁሉንም አጠመቀ እንጂ በምክንያት የተወው የለም ።

ያልተጠመቀ አይድንም የሚለው አምላካዊ ቃል ሁሉም በጥምቀት ጥላ ሥር ማደር እንዳለበት ያመለክታል ። እንግዲያውስ ሕፃኑን ፣ ሽማግ ሌውን ፣ ወንዱን ሴቱን ሁሉንም ማጥመቅ እንጂ በዕድሜ ገደብ በሌላም ምክንያት ለይቶ መተው ተገቢ አይደለም ። ወንድ በ፵ ቀን ሴት በ፹ ቀን መጠመቅ እንዳለባቸው ቤተ ክርስቲያን ትናገራለች ፤ ወዲያው ግን የታ መመና ሞት የሚያሰጋው ከሆነ ይኸ ሳይጠበቅ ማጥመቅ ተገቢ እንደሆነ ትናገራለች ። ይኸን ስንመለከት ደግሞ እንደተመቸ በማንኛውም ዕለት ማጥመቅ እንዳለብን እንጅ ገደቡን እያመለክትም ።



www.ethiopianorthodox.org

ሠ/ የጥምቀት ዋጋ ፡— ጥምቀት በሚታይ አገልግሎት የማይታይ ጸጋን ያሰጠናል፤ማለት ውኃ በገንዳ ሆኖ ካህኑ ልብሰ ተክህኖውን ለብሶ ሲጸልይ በኋላም ሲያጠምቅ ይታያል ፤ይኸም የሚታይ አገልግሎት ይባላል ።

በጥምቀት አማካይነት ልጅነት ሲሰጥ ፣ ኃጢአቱ በቁራኝነት የመጣው ሲወገድ ፣ መንፈስ ቅዱስ ሲሰጥ አይታይም ፣ ይኸም የማይታይ ጸጋ ይባላል ።

ዋናው የጥምቀት ዋጋው የሥላሴ ልጅ ፤ የመንግሥተ ሰማያት ባለቤት መሆን ፣ በጥምቀት ታጥቦ ከኃጢአት ንጹሕ መሆን ነው ።

## ምዕራፍ ፪ ምሥጢረ ሜሮን ፣

ሀ/ የቃሉ ትርጉም ፡— ሜሮን ማለት ቅባት ማለት ነው ፤ ይኸም ሜሮኖ እቀባለሁ ከሚለው ግሪክኛ ቃል የወጣ ነው ። ይኸም ቅባት እንደማንኛውም ቅባትነት እንዳላቸው ቅባት አይደለም፤የተባረከ የከበረ ፣ ከጥንት ከሐዋርያት ሲያያዝ የወረደ ቅባት ነው እንጂ ፣

ለ/ አመሠራረቱ፡— ይኸ ምሥጢር በቅ/ሐዋርያት ጊዜ የተመሠረተ ነው ፤ ይኸውም አጥምቀው ሲፈጽሙ እጃቸውን ጭነው ሲጸልዩላቸው መንፈስ ቅዱስ ይወርድላቸው ነበር ፤ ግን በዚያን ጊዜ ቅብዓቱ እንደ ነበር የሚያጠይቀው ሐዋርያው ዮሐንስ «እላንተ መቀባት አላችሁ ከቅዱሱ ፣ ሁሉንም አውቃችኋል» ሲል ተናግሯል (ዮሐ ፣ ፪ ፣ ፳)። እንደገናም በዚሁ ምዕራፍ ላይ «ከእርሱ የወሰዳችሁት መቀባት በእናንተ ትጸናባችኋለች ፤ ማንም ያስተምራችሁ ዘንድ አትሹም እንደዚሁ መቀባት ያስተምራችኋል እንጂ ስለ ሁሉ ፣ እርሱም እውነተኛ ነው» (ዮሐ ፣ ፪ ፣ ፳፯)።

ቅዱስ ጳውሎስም እንዲሁ «እግዚአብሔር የሚያጽናናን ከእናንተ ጋር በክርስቶስ ሃይማኖት የቀባንም እርሱ ነው ፤ እርሱም ደግሞ አተመነ የመንፈሱንም መያዣ በልባችን ሰጠን ሲል ተናግሯል ( ፪፡ቆሮ ፣ ፳፩— ፳፪) ።

እኛም ሜሮንን ለአዲስ ተጠማቂዎች ስንቀባ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፣ብለን የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ እንደተቀበሉ ለማረጋገጥ ማኅተም አድርገን ነው ። ይኸንንም እንደገና ቅ/ጳውሎስ መስክሮ እንዲህ ሲል ጽፎ እናገኘዋለን «የእግዚአብሔርንም አዱስ መንፈስ ለመድኃኒት ቀን የታተማችሁበትን አታሳዝኑ» (ኤፌ ፣ ፬ ፣ ፴) ።



እንግዲህ የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆናችን ምልክት ማኅተመ መንፈስ ቅዱስን እንታተማለን ፣ ቅብዐ መንፈስ ቅዱስን እንቀበላለን ፤ በዚህ በሚታየው አገልግሎት የማይታየውን ጸጋ እናገኛለን ።

ሐ/ የሜሮን ጥቅም፡— ሀብተ መንፈስ ቅዱስን ለማግኘት ፣ ከእግዚአብሔር ለመወለድ ማረጋገጫው ማኅተመ መንፈስ ቅዱስን እናገኛለን ።

## ምዕራፍ ፫ ምሥጢረ ቍርባን

፩/ ብሂል

ምሥጢረ ቍርባን ማለት ጌታችን ኢየሱስ የመሠረተው ፣ ያስተማረውና በመጨረሻም ማዕድ አቅርቦ እንኩ ብሉ ይኸ ሥጋዬ ነው ፤ እንኩ ጠጡ ይኸ ደሜ ነው ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠው ፤ በሥራም የገለጠው ፣ እስከዛሬም ያለ አድልዎ ለሁሉ የሚሰጠው የክርስቶስን ሥጋና ደም የመቀበል ምሥጢር ነው ።

ካህኑ ኅብስቱን በጻሕል ወይኑን በጽዋዕ አድርጎ የሚያቀርበው ፣ በጸሎትና በእግዚአብሔር ቃል ተለውጦ ኅብስቱ ሥጋ መለኮት ፣ ወይኑ ተለውጦ ደመ መለኮት የሚሆነው ፣ ሕዝብ ለድኅነትና ለዘለዓለም ሕይወት የሚቀበለው ምሥጢረ ቍርባን ይባላል ።

ምሥጢረ ቍርባን ስንበላውና ስንጠጣው በኅብስትና በወይን መልክ ነው ፣ ግን በካህኑ ጸሎትና ቡራኬ ተለውጦ የክርስቶስ አካል ይሆናል ፤ ማለት ደሙ ፍጹም የክርስቶስ ደም በዕለተ ዓርብ የፈሰሰውን ፣ ሥጋውም በዕለተ ዓርብ የተቆረሰውን ይሆናል ፤ የዚህም ለውጥ እንዴት እንደሆነ ስለማይታወቅ ምሥጢር ተብሏል ።

እንግዲህ ክርስቶስ ሊቀ ካህናት ሁኖ ለአባቱ ያቀረበው ፤ ያሳረገው መሥዋዕት ስለሆነ የክርስቶስ ተከታይ የሆነ ሁሉ ከዚህ ሥጋ መብላት ፣ ከዚህም ደም መጠጣት ግዴታ ነው ፣ ያለዚያ ተዋሕዶት የሚኖር ሕይወት የለውም ፤ ክርስቶስ ሲያስተምር አስቀድሞ «እኔ ነኝ የሕይወት እንጀራ ፣ ከሰማይ የወረደ ፣ ማንም ከዚህ እንጀራ የሚበላ ፣ ለዘለዓለም ይኖራል እኔም የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው » ሲል አስተምሮ ነበር(ዮሐ፡ ፮ ፣ ፶፩—፶፮) ። ከዚህም በማያያዝ «እውነት እውነት እላችኋለሁ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ እላንተ ሕይወት የላችሁም ፤ ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ ለርእሱ የዘልዓለም ሕይወት



www.ethiopianorthodox.org

አለው ፡ እኔም በኋለኛው ቀን አስነሣዋለሁ ሲል ገልጦ ተናግሯል (ዮሐ. ፮ ፡ ፶፬) ። በዚህ መልክ ክርስቶስ ሲያስተምረው የቆየውን በመጨረሻ ጊዜ በተግባር ገለጠው ። ማለት የመጨረሻ እራት አድርጎ ሥጋውንና ደሙን «ንሡ ብሉ ይኸ ሥጋዬ ነው ፤ ጽዋውንም አንሥቶ አመስግኖ እንዲህ ሲል ለደቀመዛሙርቱ ሰጣቸው ፤ ከዚህ ጠጡ ይኸ ደሜ ነው ፤ ለአዲስ ኪዳን ለብዙ ሰዎች የሚሰጥ ኃጢአትን ለማስተስረያ» ሲል (ማቴ ፡ ፳፮ ፡ ፳፮—፳፰) ።

## ፪/ መቍረብ የሚገባው ማነው ?

በክርስቶስ ያመነ ክርስቶስንም የተከተለ ሁሉ የዕድሜ ፤ የጾታ ገደብ ሳይኖርበት በክርስቶስ ቃል መሠረት ሁሉም ከሥጋው መብላት ከደሙ መጠጣት ይገባዋል ። ምእመኑ ሁሉ ከክርስቶስ ጋር አንድነት ይኖረው ዘንድ ፡ እንዲሁም ሁሉም አንዱ ከሌላው ጋር አንድነት ይኖረው ዘንድ መቍረብ አለበት ። ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ከክርስቶስ ጋር የሚዋሐደው ሥጋውን በመብላት ደሙንም በመጠጣት ስለሆነ በግድ መቍረብ አለበት ።

## ፫/ ሁል ጊዜ መቍረብ እንደሚገባ

ምሥጢረ ቍርባን ከሚደጋገሙ ምሥጢራት ውስጥ ነው ፤ ስለዚህ ማንም ክርስቲያን በየዕለቱ ፡ በየሳምንቱ ፡ በየወሩ ፡ መቀበል አለበት ፤ ቢያንስ እንኳን በዓመት ፫ ጊዜ መቍረብ አለበት ።

ካህኑ በሚያቈርብበት ጊዜ «ሥጋሁ ለአማኑኤል አምላክነ ዘበአማን ዘነሥአ እም እግዝእተ ኵልነ» እያለ ፍጹም የክርስቶስ ሥጋና ደም መሆኑን እየመሰከረ ነው ። የሚቀበለውም ምእመን «አሜን» ልክ ነው አምናለሁ ብሎ ይቀበላል (ፍትሐ ፡ ነገ ፡ አንቀጽ ፲፫ ፡ ቍጥር ፭፻፳) ።

ማንኛውም ምእመን ሲቈርብ ከሥጋው መብላት ከደሙም መጠጣት ግድ አለበት እንጅ አንዱን ተቀብሎ ፪ኛውን መተው ተገቢአይደለም፤ ምክንያቱም ክርስቶስ ሲያስተምር ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው ብሎ ከ፪ቱም መቀበል እንደሚገባ አስተምሯልና (ዮሐ ፡ ፮ ፡ ፶፮) ።

በቍርባን ጊዜ ለሥርዓቱ መልክ እንዲኖረው፡ ዝብርቅርቅም እንዳይል መጀመሪያ ጳጳሳት ፤ ቀጥሎም ካህናት ፤ ቀጥሎም ዲያቆናት ፡ ቀጥሎም ሕዝባውያን እንዲቈርቡ ሕግ ነው ። እንዲሁም ከሴቶችም በፊት ወንዶች እንዲቀበሉ ሕግ ያዛል (ፍትሐ ፡ ነገ፡ አንቀጽ ፲፫ ቍጥር ፭፻፲፱። ይኸም የሥነ ሥርዓት አጠባበቅ እንጂ ልዩነትን የሚያመለክት አይደለም።

## ፬/ እንዴት መቍረብ እንደሚገባ

ቅዱስ ቍርባንን የሚቀበሉ ሁሉ መጾም አለባቸው ፤ ይኸም ማለት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የውሎ ቅዳሴ ስላለ ጾሞ መዋል ስላለበት ነው ፤ የጧት ቅዳሴም ከሆነ በዋዜማው በጊዜ መብላት እንዳለበት ያመለክታል (ፍት፡ ነገ ፡ አንቀጽ ፲፫ ፡ ፭፻፲፪—፭፻፲፫) ። እንዲሁም አስቀድሞ ንስሐ ገብቶ ኃጢአቱን ተናዝዞ ንጹሕ ሁኖ መቍረብ አለበት ።

ለቍርባን የሚሆነውን ኅብስትና ወይን ሌላውንም መብዓ ያመጡትን ሁሉ ካህኑ ስማቸውን በየጊዜው በጸሎት ማንሣት ተገቢ ነው (ፍትሐ ነገ ፡ አንቀጽ ፲፫ ቍጥር ፭፻፺) ።

ለመሥዋዕት የሚሆነው ኅብስት በየዕለቱ መዘጋጀት አለበት ፤ በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት በአደረ መሥዋዕት አይቀደስምና ።

ዛሬም የተሠራው ኅብስት በምንም መልክ ማደር የለበትም (ፍትሐ ነገ - አንቀጽ ፲፫ ቍጥር ፭፻፷) ።

ለቤተ ክርስቲያን የሚሆነውን መብዓ ፡ በተለይም ለቅዳሴ አገልግሎት የሚውለውን ስጦታ ምእመናን ከሆኑና በእምነታቸው በሥነ ምግባራቸው ከታወቁት ሰዎች ብቻ መቀበል ተገቢ ነው ፤ ከሌሎች ወገኖች ከሆነ እግዚአብሔር አይቀበለውምና (ፍትሐ ነገ፡ አንቀጽ ፲፫ ፡ ቍጥር ፭፻፭—፭፻፫ ) ። ለምሥጢረ ቍርባን አገልግሎት የሚውለው ኅብስት ከንጹሕ ስንዴ ብቻ የተሠራና ንጹሕ ወይን መሆን አለበት ፤ ለመሥዋዕት አገልግሎት ሌላ ቅብዓት የሆነ ወይም ሌላ ነገር ፡ ሥጋ ልዩ ልዩ ፍሬም ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲገባ አይፈቀድም ፤ ፈጽሞም ክልክል ነው (ፍትሐ ነገ ፡ አንቀጽ ፲፫ ቍጥር ፬፻፺፯ ቍጥር ፬፻፺፰) ።

## ምዕራፍ ፬/ ምሥጢረ ንስሐ ፡

### ፩/ ብሂል ፤

ንስሐ ማለት መጸጸት መመለስ ማለት ነው ፤ ይኸውም ነስሐ ካለው ከግእዝ የወጣ ቃል ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

አንድ ሰው ወዶና ፈቅዶ በሠራው ፣ ሳያውቅም በስሕተት ቢሆን ፣ ወይም ከልማድ የተነሣ የኃጢአት ዘርፍ ከሆኑት ነገሮች ሲሠራ ከቆየ በኋላ በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን ታርሞ ከቀድሞ ስሕተቱ ቢመለስ የቀድሞ ሥራውን ሁሉ ስሕተት መሆኑን ዐውቆ እንደገና አልመለስበትም ፣ አላደርገውም ፤ አላበጀሁም ብሎ ሲመለስ ንስሓ ይባላል ።

## ፪/ የምሥጢረ ንስሐ አመሠራረት ፣

ይኸንም ምሥጢረ ንስሐ ጌታ የመሠረተው ፣ ያስተማረውም ነው፤ በዚህም ምሥጢር የሰው ልጅ በሠራው ኃጢአት ያስወሰደውን ልጅነት ያስመልሳል ፣ የረከሰውን ሰውነቱን ያነጻል ያረጀውን መንፈሱን ያድሳል።

ንስሐ የበደለውን እንዳልበደለ ፣ ኃጢአተኛውን እንደ ጻድቅ ፣ ዘማዊውን እንደ ድንግል ያደርጋል ። ከሰው ልጅ የሚፈለገውም መመለሱ ፣ መታረሙ ነው እንጂ የእግዚአብሔር ምሕረት ዘላለማዊ ስለሆነ ማንኛውም በዓይ ቢመለስ ፣ ቢጸጸትም ፈጥኖ ይቅርታን ያገኛል ።

## ፫/ ማን ንስሓ መግባት እንደሚገባው ፣

ምሥጢረ ንስሐ ለካህንም ፣ ለሕዝባዊም ሁሉ አስፈላጊ ነው ፤ ምክንያቱም ሁሉም ሰው እንደመሆኑ የማይበደል የለምና ። እንዲሁም ሕፃናት አስበው ለመናገር ከቻሉበት ጊዜ ጀምሮ ክፉና ደግ መሥራት ይችላሉ ተብሎ ስለሚገመት በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ከ፲፪ ዓመት ዕድሜያቸው ጀምሮ ንስሐ መግባት ፍትሐት መፈታት ያስፈልጋቸዋል ። ከዚያ በታች ያለው ሕይወታቸው ግን ከመሠረቱ እንደ ንጹሕ ሠሌዳ ስለሆነ ንጹሐን ናቸው፤ ቢያጠፉም ዐውቀው ይሁንብን ብለው የሚሠሩት ስላልሆነ እንደበደል አይያዝባቸውም ።

ንስሐ ለሰው ልጅ ሁሉ አስፈላጊ መሆኑን ከተናገርን በኋላ የኑዛዜን አስፈላጊነት እንናገራለን ።

## ፬/ ኑዛዜ ፣

እንግዲህ ማንም ንስሐ ከገባ መናዘዝ በግድ አለበት ። መናዘዝም ማለት ዐውቆና ወዶ ሳያፍር የሠራውን በደል ሁሉ ሳያፍር መናገር መለፍለፍ ፣ የጥፋቱን ዝርዝር ሁኔታ መነሻ ምክንያት ከተግባሩ ጋር ለካህኑ መናገር ማለት ነው ።

ኑዛዜ ራስን መክሰስ ፣ መውቀስ ማለት ነው ፣ አንድ ክርስቲያን ክርስቶስ ከካሰለት በደሙም ከዋጀው በኋላ የርሱን ውለታ ዘንግቶ ንጹሑን



አካሉን በኃጢአት ማቆሸሽ ስለሆነ ራሱንም ክርስቶስንም መበደሉን ማ
ወቅ አለበት ፤ ስለዚህ ራሱ ተከሳሽ ሆኖ ካህኑን ታዛቢ ዳኛ አድርጎ በእ
ግዚአብሔር ፊት መቆም ማለት ነው ።

በእርግጥም ተነሳሒውና እናዛገቡ ካህን በግልጥ ሲታይ የይቅርታ
አምላክ እግዚአብሔርም ፫ኛ ሁኖ እንደሚገኝ ይቅርም እንደሚለው አምኖ
መናዘዝ ነው ፤ በዚህም መሠረት ኑዛዜ በካህን ፊት መፈጸም አለበት ።
ጌታ ራሱ ሲናገር «እናንተ ኃጢአቱን የያዛችሁበትን እኔም እይዝበታ
ለሁ ፤ እናንተ ይቅር ያላችሁትን ደግሞ እኔም ይቅር እለዋለሁ» እያለ በሐ
ዋርያት አማካኝነት ለካህናት አስተላልፏል ።

ለምሥጢረ ንስሐ የሚታይ አገልግሎት የማይታይ ጸጋ አለው ፣ ይኸም ተነሳሒውራሱን በእግዚአብሔር ፊት አዋርዶ ሲያለቅስ፣ሲጸጸት፣ በደሉን ሲናገር ፣ ሲያውቅ በድፍረት ፣ ሳያውቅ በስሕተት መሥራቱን በካህኑ ፊት ሲናዘዝ ይታያል፤ ካህኑም የተነሳሒውን ኑዛዜ በጽሙና ከሰማ በኋላ ከእግዚአብሔር ይቅርታን ሲጠይቅለት ፣ ሲጸልይለት ይታያል ፤ ይኸ የሚታይ አገልግሎት ይባላል ።

ይኸም የሚታይ አገልግሎት ከነምሳሌው ፣ ከነምልክቱ መጠበቅ፣ መፈጸምም ያለበት ነው ፤ ምክንያቱም የቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓት እውነተኛውም ትምህርት ነውና ።

ሰውየውም ከልብ መመለስ ፣ መጸጸትና መናዘዝ የተነሣ ፣ ከካህኑም ጸሎትና ምልጃ የተነሣ እግዚአብሔር እንደ ቃል ኪዳኑ በደሉን ይቅር ይለዋል ፤ ኃጢአቱን ያስተሠርይለታል ። ይኸ ሁሉ ሲሆን፤ ጸጋውና በረከቱም ሲሰጠው አይታይም ፤ ስለዚህ ይኸ የማይታይ ጸጋ ይባላል ፤ ይኸ ደግሞ መታመን ያለበት ነገር ነው ፤ ማለት ማንም በደለኛ ራሱ ከተመለሰ እግዚአብሔር ለመመለስ ከበደሉም ለማንጻት ዝግጁ መሆኑን ማመን አለብን ።

## ፭/ የኃጢአት ዓይነቶች ፣

የኃጢአት ዓይነቱ ፣ ስልቱ ብዙ ሲሆን ተጠቃሎ በ፫ ይከፈላል ፤ ይኸውም የሐልዮ ለብቻው አንድ ሲባል የነቢብ ፣ የርእይ ፣ የተናግሮ አንድ ወገን ሆኖ ፪ ይባላል ፤ ገቢርም ፫ኛ ይሆናል ። የኃጢአት መሠረቱ ሐልዮ ነው፤ምክንያቱም ማንኛውም ኃጢአት ሳይታሰብ የሚሠራ የለምና። አንዳንድ በድንገተኛ አጋጣሚ ሳይታሰብ የሚፈጸም ቢኖር ብዙ ጊዜ



www.ethiopianorthodox.org

አይጠየቅበትም ፤ በንዝህላልነቱ ባለመጠንቀቁ ግን ይቀጣል ፤ ስለዚህ የኃጢአት ሥር የሆነውን ሐሳቡን የሰው ልጅ ሁሉ ማራቅ አለበት ፥ ገና ሲታሰብ የእግዚአብሔርን ስም በመጥራት ሰይጣንን በማውገዝ ወዲያው ራሱን ማረም አለበት ።

አንድ በደል የሆነን ነገር በየጊዜው ማሰብ ለመሥራት ፈቃደኛነቱን ይገልጣል ፤ ሱስም ይሆንበታል ፤ ይኸም እንደተፈጸመ ያስቈጥራል ፤ ማለት ለመፈጸም ያስቸገረው የጊዜ የቦታ ፥ የሁናቴ ጉዳይ ነውና ። እንዲያውም ብዙ ካወጣና ካወረደ በኋላ ለመሥራት ፈቅዶ ባለቤት ነቅቶበት ፥ ውሻ ጮሆበት ፥ አጥር ቅጥር በርትቶበት ፥ በጠቅላላም ከዐቅሙ በላይ የሆነ ነገር ገጥሞት ቢመለስ እንደፈጸመው ፥ ፍጹም በደልንም እንደ ሠራ ይቈጠራል ።

እንዲሁም መንገድ ሲሄድ ፥ ወይም ባለበትም ቦታ ሆኖ ክፉ ነገርን ያያል ፤ ይሰማል ፤ ወይም ይናገራል ፤ ይኸ በደል እንደሆነ ተገንዝቦ የእግዚአብሔርን ስም ጠርቶ ሰይጣንን አውግዞ የተወው፤ያልመላለሰው እንደ ሆነ እንደበደል አይቈጠርበትም ፥ ግን አሁንም ስለዚያ ነገር ለመመልከት ፥ ለመስማት ፥ ለመናገር የጓጓ እንደሆነ ያም ነገር እንዲፈጸም የተነሣሣ እንደሆነ አሁንም ይኸን ሁሉ በሥራ ላይ እንዳዋለው ፥ በደልንም እንደፈጸመ፤ኃጢአትንም እንደሠራ ይቈጠርበታል ። ገቢርም ሆኖ ሳይታሰብ የተፈጸመ ሁሉ እንደበደል የማይሆንበት ምክንያት አለ፤ ይኸንም ከፍ ብለን ገልጠነዋል ፤ ግን እንደሁናቴው የሚያገኘው ቀኖና ይኖራል ።

## ፮ ቀኖና

ካህኑ የተነሳሒውን ንስሐውን ተመልክቶ ፤ ኑዛዜውን ሰምቶ ፤ ከእግዚብሔር ምሕረት ለምኖ፤ይቅርታ አሰጥቶ ብቻ አይተውም ፤ ግን እንደ ኃጢአቱ ከባድነትና ቀላልነት ፥ እንደ ተነሳሒው ደካምነትና ብርታት ቀኖና ይሰጠዋል ። ምንም ኃጢአት ሁል ጊዜ ኃጢአት ቢሆን ከባድና ቀላል አለው ፤ እንዲሁም ከተነሳሕያን ውስጥ ለኃጢአት ብርቱ ለንስሐ ደካማ የሆኑ ይገኛሉ ። ይኸም በመጽሐፈ ቀኖና የተወሰነ ቢሆንም የካህኑን ፈሊጥና ዕውቀት ይጠይቃል ፤ ኃጢአቱ በንስሐውና በኑዛዜው በካህኑም ጸሎት እንደ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ተሰርዮለታል ፤ ቀኖናው ከዚህ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም ፤



፩/ ተነሳሒው ስሕተትን በሚያመጣው ወጥመድ ደግሞ እንዳይያዝ ለማስጠንቀቂያ ለሌሎችም መለበሚያ እንዲሆን ቤተ ክርስቲያን የወሰነችው ቅጣት ነው ።

፪/ አዝኖ ደስታ ፥ ጹሞ ፋሲካ ሲሆን ለራሱም ይቀለዋል ፤ ይደሰትበታልና ፥ ምሥጢሩን ማቃለል እንዳይሆን ይኸ ዓይነት ቀኖና ይሰጠዋል ።

ቀኖናውም ቅዱስ መጽሐፍን በተወሰኑት ዕለታት በማንበብ እንዲያሳልፍ ፥ ከሰው ጋር ሳይገናኝ በጸሎት ጽሙድ ሆኖ እንዲቆይ ፥ የተወሰኑ ቅዱሳት መካናትን ለመሳለም እንዲወጣና እንዲወርድ በማድረግ፤ጾም ጸሎት በመያዝ የተወሰኑ ዕለታት ሳምንታት ፥ አውራኅ በመስጠት ፥ ምጽዋት እንዲሰጥ ፥ በጉልበቱ በዕውቀቱ ሌሎች ችግረኞችን እንዲረዳ በማድረግ ፥ ይኸን በመሳሰሉ በሌሎች ተግባሮች ይፈጸማል ።

ኑዛዜው በሥውር ካህኑና ተነሳሒው ከእግዚአብሔር ጋር የሚያደርጉት ውይይት ሲሆን ፤ አንዳንድ ጊዜም በዐደባባይ የሚሆን አለ ፤ ሰው ያወቀው ፀሐይ የሞቀው ግልጥ የሆነ አድራጎት እንደሆነ ቀኖናውም ግልጥ መሆን አለበት ፤ ምክንያቱም ፥

ሀ/ ሌላው እንደታዛቢ ሆኖ እንዳይገምት ማለት እንዲሁ የወጣ እንዲሁም የገባ መስሎ እንዳይታይ ፥

ለ/ የሰው ፊት እሳት ስለሆነ ከባድን ኃጢአት በሕዝብ ፊት ሲናዘዝ መልሶ እንዳይደግመው ቁርጠኛ መሆኑን ሲናገር በበለጠ ራሱን የሚክስ፤ራሱን የሚያጋልጥ ሆኖ በመገኘቱ ፍጹም ይቅርታን እንዲያገኝ ።

ሐ/ ሌላው ሕዝብ እንዲቀጣ፤ማለት አሳፋሪ አስፈሪም ነገር መሆኑን ዐውቆ ሁሉም እንዲጠነቀቅ ፥ ይኸንንም የመሰለውን አድራጎት ወደ መፈጸም እንዳያዘነብል መቀጣጫ ለማድረግ ነው ።

## ፯/ የንስሐ መስጫ ቦታ

ኑዛዜ መፈጸም ያለበት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በምሥጢር ቦታ፥ በእውነት በቅንነት ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ ነው። ለይቅርታ ምክንያት መሣሪያም ሆኖ የቀረበውም ካህን እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የሆነ ፥ ከልቡ ለተነሳሒው የሚጸልይ ከእግዚአብሔር ጋር ለማስታረቅ ችሎታ ያለው ንጽሕናን ቅድስናን ገንዘብ ያደረገ መሆን አለበት ። ለእግዚአብሔር ምሕረት መተላለፊያ እውነተኛም መሣሪያ ሆኖ መገኘት አለበት።



www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፰ ምሥጢረ ክህነት

### ፩/ ብሂል ፡

ምሥጢረ ክህነት የማሠርና የመፍታት ሥልጣን ያለው ከመሆኑም በላይ ሌላውንም የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት ለመቀደስ፤ለማክበር፤ለመፈጸም ችሎታ ያለው እርሱ ብቻ ነው ። ክርስቶስ የሠራው የመሠረተውም ምሥጢር ከመሆኑም በላይ ከርሱም ጀምሮ እስከ ዛሬ ያለማቋረጥ ሲተላለፍ የሚገኝ ነው ፤ ይህንም ሥልጣን ክርስቶስ ለተከታዮቹ ለሐዋርያት ሰጥቷል ፣ ሐዋርያትም ለተከታዮቻቸው በአንብሮተ እድ እያስተላለፉእስከኛ ድረስ ደርሷል ፡ ከኛም እስከ ምጽአት እንዲሁ ያለማቋረጥ እንደሚሰጥ የተረጋገጠ ነው ። ይህንም ምሥጢር ክርስቶስ እንደ መሠረተው በቅዱሳት መጻሕፍት የተመሰከረ ነው (ማቴ ፲ ፡ ፪ ፡ ፲፰—፲፱ ፣ ዮሐ ፡ ፳ ፳፪—፴፫) ።

### ፪/ የምሥጢረ ክህነት ጥቅም

ምሥጢረ ክህነት ሀብትን ያሰጣል፤የማሠርን የመፍታትን ሥልጣን ያስገኛል ፤ እንዲህም ስንል ፤

፩ኛ/ አገልግሎቱ፡ ፍጹም መሆን አለበት፣ውስጣዊ ሥራውም ከልብ እንዲሠራ ጸሎቱም ከልብ እንዲጸለይ ያስፈልጋል ።

፪ኛ/ ምሥጢሩን የሚፈጽመው ሰው ሁል ጊዜ ደንበኛ ካህን መሆንና በእውነት ቤተ ክርስቲያን የመረጠችው በሚገባም በአንብሮተ እድ የተሾመ ካህን መሆን አለበት ።

፫ኛ/ ምሥጢሩ የሚፈጸምለትም ሰው ከልቡ የተዘጋጀ ልቡን ከሕዝባዊነት ተራ ያወጣና የለወጠ፤ወደ መንፈሳዊ ዓለም ያዞረ፤የእግዚአብሔርን ጸጋ ከልቡ የፈለገ መሆን አለበት ። እነዚህ የተዘረዘሩት ነገሮች በሚገባ የተፈጸሙ እንደሆነ ከታሰበው ዓላማ በትክክል ይደረሳል ፤ የተፈለገውም ዋጋ ይገኛል ። ይኸ አገልግሎት በማንኛውም ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ በጥብቅ ሊታሰብበትና በዚህም መልክ ሊደረግ የሚገባው ነው ፤ በተለየ ምሥጢረ ክህነት የበለጠ ጥንቃቄ የበለጠም አፈጻጸም ሊኖረው ይገባል ፤ ምክንያቱም ሌላውን ምሥጢር የሚቀድስ ወደሌላው ስቦ የሚያደርስ በምሥጢረ ክህነት የከበረ ካህን ነውና ።

### ፫/ ምሥጢረ ክህነት ክርስቶስ የመሠረተው ነው ፤

የክህነትን ጸጋ ክርስቶስ በመጀመሪያ ለቅዱሳን ሐዋርያት አደላቸው «ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውም መንፈስ ቅዱስን ተቀብሎ ኀጢአቱን



የተዋችሁለት ቀረችለት የያዛችሁበትም ሰው ተያዘችበት » (ዮሐ ፳ ፡ ፳፪—፳፫ ፤ ማቴ ፲ ፡ ፩—፵፪፤ማር፤ ፮፡ ፯—፲፫፤ሉቃ ፱፡ ፩—፮)።«እርሱም ሰጠ እኩሊቶች ነቢያት ሌሎችም ሰባኪዎች ሌሎችም ጠባቂዎች - - -» (ኤፌ፡ ፬ ፡ ፲፩)።እያለ ቅዱስ ጳውሎስም ይመሰክራል።«አሁንም ለራሳቸው ተጠንቀቁ ለመንጋውም ሁሉ መንፈስ ቅዱስ በርሱ ላይ ጠባቆች አድርጎ የሾማችሁ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁ ዘንድ እርሱ በደሙ የዋጃትን» (የሐዋ ሥራ ፳ ፡ ፳፰) ሲል ቅዱስ ጳውሎስ ያስረዳል ።

ክርስቶስ ይኸን የከበረ ሥልጣን ለሐዋርያት የሰጣቸው በነርሱ ብቻ እንዲወሰን አይደለም ፤ ለነርሱ ብቻ ቢሆን «እኔ እነሆ ከላንተ ጋራ ነኝ በዘመኑ ሁሉ እስከ ፍጻሜም ዘመን ሁሉ» (ማቴ ፳፰ ፡ ፳) ብሎ ባልመሰከረም ነበር ፤ ምክንያቱም ሐዋርያት ሁሉ በአንደኛው መቶ ዓመት ውስጥ የሞቱ ሲሆን ፣ እስከ ዓለም ፍጻሜ ከናንተ ጋራ ነኝ ባላለም ነበር ። ነገር ግን ሐዋርያት ለተከታዮቻቸው እንዲያወርሱ፤በአንብሮተ እድ እንዲሾሙ ይህ ማዕርገ ክህነትና ሌላውም ሀብት ሳይቋረጥ እስከ ዓለም ፍጻሜ የሚሰጥ መሆኑን የሚያረጋግጥ ቃል ነው።ስለዚህ ሐዋርያት ወዲያውኑ በአንብሮተ እድ ሰባቱን ዲያቆናት ሾሙ (የሐዋ ሥራ ፮ ፡ ፫ ፡ ፱)።ቀጥለውም ሁሉም በየሔዱበት ሀገረ ስብከት ዲያቆን ፣ቄስ ኢጲስ ቆጶስ ሾሙ(የሐዋ ሥራ ፲፬፡፳፫) ለምሳሌ ቅዱስ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ለኤፌሶን ኤጴስ ቆጶስ አድርጎ እንደሾመው (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፬) እናገኛለን ። የኤጲስ ቆጶስነቱም ምልክት እርሱ እንዲሾም ሥልጣን ሰጥቶ ነበር ፤ «በተሰጣችሁ ጸጋ በትንቢት በቀሳውስትም ላይ እጅን በመጫን ቸል አትበሉ» (፩፡ጢሞ፡፬ ፡ ፲፬)። እንዲህ አድርጎ የሚመክረው ጢሞቴዎስን መጀመሪያ እርሱ በአንብሮተ እድ ከሾመው በኋላ ነው ፤ « ስለዚህ አሳስብሃለሁ የእግዚአብሔርን የጸጋውን ሕይወት ለማደስ ያደረችብህ ፣ በተሰጠኸው እጅን በላይህ በጫንኩብህ ጊዜ» (፪፡ ጢሞ ፩፡ ፮) ። እንዲሁም የቀርጤስ ኤጲስ ቆጶስ አድርጎ ቲቶን ሹሟል « ስለዚህ በቀርጤስ ተውኩህ የጎደለውን ሁሉ ትሞላ ዘንድ ቀሳውስትንም ትሾም ዘንድ ፣ በየሀገሩ እንዳዘዝኩህ» (ቲቶ ፩ ፡ ፭) ። ይህን የመሰለ ቅ/ሐዋርያት በየሔዱበት አገር ሰው እየመረጡ በአንብሮተ እድ እየሾሙ እስካሁን ይተላለፋል ፣ እስከ ምጽአትም ይህ ጸጋ ሳይጓደል ወይም ሳይቋረጥ ይሰጣል ።



www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፲ ምሥጢረ ተክሊል ፤

### ፩/ ብሂል

ጋብቻ በሕገ ቤተ ክርስቲያን አስተያየት እንደ ምሥጢር ሲታይ የቤተሰብእ ፣ የሕዝብ ፣ የመንግሥት መሠረት ስለሆነ ፣ ትልቅ ዋጋ አለው ፤ ስለዚህ ከዚህ ቀጥለን ሰፋ አድርገን ጋብቻ የሚፈጸምባቸውን አኳኋኖች እንመረምራለን ።

ይሁን እንጅ የጋብቻ ደንብ ለማኅበራዊ ኑሮ ያለውን ጥቅምና አስፈላጊነት ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ተረድተው በብዙ አስተያየት ሊደገፉት ይገባል ።

በቤተ ክርስቲያን ሕግ ውስጥ የጋብቻ ሕግ የሚለው ከቤተሰብ ሕግ ውስጥ ልዩ ክፍልን ይዞ ይገኛል ።

ተክሊል ማለት ወንድና ሴት ተስማምተው በሚያደርጉት ጋብቻ ካህን የሚሠራው የሚፈጽመውም፤ጸጋንና በረከትን የሚያሰጥ መንፈሳዊ አገልግሎት ነው ። ይህም ምሥጢር በሥጋዊ ጠባይ አስፈላጊነት ብቻ የተመሠረተ ሳይሆን ፣ መንፈሳዊ ዓላማ ያለው ፤ ለዘር መብዛትን ፤ ለኑሮ ሕይወትን እንዲያስገኝ ቅዱስ እግዚአብሔር ፈቃዱ ኹኖ ያዘዘው የሠራውም ምሥጢር ነው ፤ ማለት በመጀመሪያው በጥንተ ፍጥረት ሴትና ወንድ በጋብቻ ሥርዓት አንድ ኹነው መኖር እንዲገባቸው አዳምና ሔዋንን በመፍጠሩ ይታወቃል (ዘፍ፡ ፪-፳፩) ። እንዲሁም ከሦቱ አካላት አንዱ የአብ ቃል ወልድ ወደዚህ ዓለም መጥቶ የመጀመሪያ ታምራቱን የገለጠበት አንድ ወንድ በአንዲት ሴት ኹነው በሚጋቡት በቅዱሱ ጋብቻ ነው (ዮሐ ፪ ፣ ፩—፲) ። እንዲሁም ክርስቶስ ሲያስተምር ፈሪሳውያን ሊፈታተኑት ጋብቻን እያቃለሉ ሲጠይቁት ጋብቻ ቅዱስ ሥራ እግዚአብሔር የባረከው፤እግዚአሔር የፈቀደው እንደ ሆነና እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ማንም ለመለየት እንደማይችል በሰፊው አስረድቷል ። ሰው ማግባት እንደሚገባው ፣ ጋብቻም ክቡር እንደሆነ ሐዋርያት ለጠየቁት ጥያቄ « - - - - ይህ ነገር ለሰዎች ኹሉ አይቻላቸውም ለተሰጣቸው በቀር ጃንደረባ ሁነው ከናቶቻቸው የተወለዱ ሰዎች አሉና ፣ ሌሎችም ሰዎች ሰልበው ጃንደረባ ያደረጓቸው አሉና ፣ ስለ መንግሥተ ሰማያት ሰውነታቸውን ጃንደረባ ያደረጉ ሰዎች አሉ ፣ ማስተዋል የሚችል ግን ያስተውል» (ማቴ ፲፱ ፣ ፲፪) ሲል የሰጠው መልስ ያስረዳል ፣ ማለት በንጽሕና ፣ በድንግልና ሊኖሩ እግዚአብሔር ከፈቀደላቸው ሰዎች በቀር ሰዎች ኹሉ በጋብቻ እንዲኖሩ ይህ ቃል ያስረዳል ።



### ፪/ የምሥጢረ ተክሊል የሚታይ አገልግሎት የማይታይ ጸጋ

ምሥጢረ ተክሊልም እንደሌሎች ምሥጢራት የሚታይ አገልግሎት የማይታይ ጸጋ አለው፤ ሙሽራውና ሙሽራይቱ ነጭ ልብስ ለብሰው፤ አክሊል ተቀዳጅተው፤ወደውም ለመጋባታቸው ቃል ኪዳን ሲገቡ፤ካህኑም ስለ አንድነታቸው ሲጸልይባቸው ፣ ሲባርካቸውም ቅዱስ ዘይትንም ሲቀባቸው ይታያል ። እንዲሁም የተፈጥሮ ጋብቻ ሲቀደስ፤ኹለት የነበሩ በመንፈስ ቅዱስ አንድ ሲሆኑ ፤ በኹለቱም ላይ ፍጹም ፍቅር ሲያድርባቸው ፤ መለያየት ሲጠፋላቸው አይታይምና ።

ማንኛውንም ምሥጢር ካህናት እንደሚፈጽሙት ይህም ምሥጢር እንዲሁ በካህናት ሊፈጸም ይገባዋል ። ካህኑ በበለጠ ሊያስብበት ሊጠነቀቅበት የሚገባ በምሥጢረ ተክሊል ነው ፤ ምክንያቱም ለሌላው ምሥጢር ኹሉ ሕዝብ ተሳታፊ የሚሆን ጋብቻ የከበረ እንደሆነ ነው ፤ ጋብቻ ሲረክስ፤ዘር ሲቀነስ ቤተ ክርስቲያንም አብራ ትረክሳለች ፤ አባሎቿም፣ይቀነሳሉ ፤ ለመንግሥት ጸጥታው ሊረጋገጥ ሰላም ጤንነት ሊገኝ አይችልም ። ሰው ሕግን የተላለፈውን ያህል ችግር መከራ ፈተና ያገኘዋል፤ስለዚህ አስቀድሞ ሁሉ በሕግ እንዲያገባ ፣ በጋብቻውም ጊዜ ልዩ ጸሎት እንዲደረግለት መለያየታቸው እንዲጠፋ መድከም የካህኑ ዋና ተግባር ነው ።

### ፫/ ጋብቻ የማይፋታ ምሥጢር መሆን

የመጀመሪያው ሰው አዳም ሔዋንን ብቻ አግብቶ በደስታ ጊዜ በገነት፤ በመከራ ጊዜ በምድረ ፋይድ አብረው ይኖሩ ነበር ። በምቾት ምክንያት ሚስት መፍታት የሚገባ ቢሆን አዳም በገነት ሳለ ሔዋንን በፈታትና ባበረራት ነበር፣ወይም በመከራ ጊዜ መፍታት የሚገባ ቢሆን ምድረ ፋይድ በገቡ ጊዜ ባበረራት ነበር ። ወይም ብዙ ሴት ማግባት የሚገባ ቢሆን ሥላሴ ለአዳም ብዙ ሴት መፍጠር በቻሉ ነበር። ብዙ ወንድ ማግባት የሚገባም ቢሆን ኖሮ ለሔዋን ሥላሴ ብዙ ወንድ በፈጠሩላት ነበር ፤ ነገር ግን አንድ ወንድ በአንዲት ሴት ፣ አንዲት ሴትም በአንድ ወንድ መኖር በደስታም በመከራም አብረው መኖር እንደሚገባቸው ሲያጠይቅ ለሔዋን አዳምን ብቻ ፤ ለአዳምም ሔዋንን ብቻ ፈጠሩ (ዘፍ ፣ ፪ ፣ ፳—፳፯) ። በኋላም ክርስቶስ በዚህ ዓለም ሲያስተምር ይህኑ አጽንቶ «አላነበባችሁምን እግዚአብሔር አስቀድሞ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠረ ፤ ዓለም ፤ ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ምሽቱንም ይከተላል ፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ ፤ ሁለትም አይደሉም ፣ እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው አይለየውም» (ማቴ ፣ ፲፱ ፣ ፮—፱) ሲል በሰፊው አስረድቷል ።



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር በጥንተ ፍጥረት አንድ ያደረገውን ጋብቻ በበደል ምክንያት ብዙ ማግባት ብዙ መፍታት መጣ ፤ ይህም በሰው ላይ እግዚአብሔር ካመጣው ቅጣት አንደኛው ነበር ። በኋላ ግን አምላክ ሰው ኹኖ ሥጋን ለብሶ ፣ የተረገመውን ማኅፀን ቀድሶ፤ ያረጀውን አካል አድሶ፤ የአዳምን ልጅነት መልሶ ጋብቻ እንዲሁ የጸና እንዲሆን አውጆአል ። ሐዋርያትም ይህን ተከትለው ጋብቻ ቅዱስ ምሥጢር ሲሆን መፋታት የማይቻል የማይገባም መሆኑን አጽንተው አስተምረዋል ። ባልና ሚስት ሊለያዩ የሚችሉበት ዋናው ምክንያት ሞት ብቻ ነው፤ይህንም የመሰለ የሥነ ምግባር ሞት ነው፤ ማለት ፩ኛው ወገን ዝሙት በሠራና እምነት ባጐደለ ጊዜ ነው ።

ዘርን ለማብዛትና ጸጋን ለመስጠት የሁለቱን አንድነት ለማጽናት እምነትን ፍቅርን ለማሳደር የተክሊል ጸሎት አስፈለገ ። መጀመሪያ እግዚአብሔር ሰውን ወንድና ሴት አድርጎ ሲፈጥራቸው አንድ ሁነው ተረዳድተው ፣ ተደስተው እንዲኖሩ የሁሉም ገዥ ፣ የሁሉም አዛዥ ሁነው እንዲኖሩ ዘራቸው፤በዝቶ ምድርን መልተዋት እንዲኖሩ ነውና «እግዚአብሔር ሰውን ፈጠረ በመልኩ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው ፤ እግዚአብሔርም ባረካቸው እግዚአብሔርም አላቸው ፤ ብዙ ተባዙም ምድርን ሙሏት ግዟትም ፤ - - - » (ዘፍ ፩ ፡ ፳፯—፳፰ ) በቤተ ክርስቲያን በሚደረገው ጋብቻም የሚጸለየው ጸሎት ይህን የመሰለ ነው ።

## ፬/ የተክሊሉ ጥቅም ፤

ሁለትነት ጠፍቶ አንድነት እንዲመሠረት ፤ የባልና የሚስቱ ፍቅራቸው ፍጹም እንዲሆን ፣ የባልና የሚስትነታቸው እምነት እንዲከበር ነው ።

# ምዕራፍ ፯ - ምሥጢረ ቀንዲል

## ፩/ ብሂል ፤

ቀንዲል ወይም ቅብዐ ቅዱስ የተባለው ምሥጢር ከንጹሕ ወይራ ዘይት የተሠራ ፤ የሥጋንም የነፍስንም በሽታ የሚያርቅ ፤ የማዳን ኀይል ያለው፤ክርስቶስ የመሠረተው ፣ ሐዋርያትም ያስተማሩት ምሥጢር ነው ።

## ፪/ መቼ እንደተመሠረተ ፤

ክርስቶስ እንደ መሠረተው ምንም እንደ ሌሎች ምሥጢራት ግልጽ የሆነ ጽሑፍ እንኳን ባይገኝ ሐዋርያትን እንዳዘዛቸው ፣ እነርሱም ዘይትን እየቀቡ ብዙ ድውያንን እንዳዳኑ ከዚህ የሚከተለው ጽሑፍ ያስረዳል ፤



«በወጡም ጊዜ አስተማሩ ፤ ንስሓ ይገቡ ዘንድ እጅግም ሰይጣናትን አወጡ ፤ በዘይትም ብዙ ድውያንን ቀቡ ፤ አዳኗቸውም» (ማር፡ ፮ ፡ ፲፯)፤ ሐዋርያት ግን ይጠቀሙበት እንደ ነበር ከላይ የተዘረዘረው ብቻ ሳይሆን ቅዱስ ያዕቆብ፤«ማንም ከእናንተ ቢታመም የቤተ ክርስቲያን ቀሳውስትን ይጥራ ፤ ይጸልዩበትም ፣ በዘይትም ፣ ይቅቡት ፤ በጌታ ስም ፤ የሃይማኖትም ጸሎት ድውዩን ትፈውሰዋለች ፡ ጌታም ያስነሣዋል ፤ ኃጢአትም ሠርቶ እንደሆነ ትሰረይለታለች - - - - » ተገቢ መሆኑን (ያዕ፡ ፭ ፡ ፲፭—፲፮) ሲል ክርስቲያን ሁሉ ሊጠቀሙበት አስፈላጊና በሰፊው ያስረዳል ።

የማዳን ኃይል አለው ስንል ከዘይቱ የተገኘ ኀይል አይደለም፤ በእግዚአብሔር ጸጋ በቄሱ ጸሎት ነው ፤ ስለዚህም ያዕቆብ «የእምነት ጸሎት በሽተኛውን ያድናል ፤ ኃጢአቱንም ያስተሰርያል» ሲል በቅን ልቡና በንጹሕ ሰብእና ሆነው አምነው የጸለዩበት ዘይት ታምራት እንዲሠራ ፤ ኀይለ እግዚአብሔርም እንደሚገለጥ ያስረዳል ።

## ፫/ የምሥጢረ ቀንዲል አገልግሎት ፤

ምሥጢረ ቀንዲል እንደ ሌሎች ምሥጢራት በካህን ብቻ የሚፈጸም ምሥጢር ነው ። የተወሰነውን ጸሎት ካህኑ በሚገባ አድርሶ የበሽተኛውን አካል በመስቀል ምልክት ግንባሩን ፣ ሁለቱን ወገን ፊቱን ፣ ሸንጎበቱን ፤ የቀኝና የግራ እጁን በውጭም - በውስጥም ፪ እግሩን ፣ ቢቻል ታላላቅ ሕዋሳቱን ያለዚያም ለጊዜው የሚያመውን አካሉን ይቀባዋል ፤ በዚህ ጊዜ በሽታው ይለቀዋል ፤ ኀጢአቱም ይሰረይለታል ። ደዌ ሥጋ ለደዌ ነፍስ ፣ ደዌ ነፍስም ለደዌ ሥጋ ይተርፋልና ማለት ንጽሕናቸውን ባለመጠበቃቸው ሰውነታቸውን በማጎሳቆላቸው ነፍሳቸውንም አብረው ያጎሳቁላሉ ፤ ሥጋቸው በታመመ ጊዜ ነፍሳቸውም አብራ ትታመማለች ፤ ግን ንስሐ ገብተው ፣ ተመልሰው ምሥጢረ ቀንዲልን የተቀበሉ እንደሆነ ድኅነተ ሥጋንም ድኅነተ ነፍስንም ያገኛሉ ።

## ፬/ የሚታይ አገልግሎት የማይታይ ጸጋ ፤

በምሥጢረ ቀንዲልም የሚታይ አገልግሎት የማይታይም ጸጋ አለው፤ ማለት በሽተኛው ወድቆ ድኅነትን ደጅ ሲጠና ፤ በንጹሕ ዘይት ላይ የሃይማኖት ጸሎት ሲጸለይ ፣ ቄሱ ሲባርከው ፣ ከጸሎቱም በኋላ አካሉን ሲቀባው ይታያል ፤ ይህ የሚታይ አገልግሎት ይባላል ። ደዌ ሥጋውም ደዌ ነፍሱም ሲለቀውና ሲፈወስ ፤ የእግዚአብሔር ጸጋ ሲሰጠው አይታይም ፤



www.ethiopianorthodox.org

ብዙ ጊዜ ግን ከደዌ ሥጋው ሲፈወስ ይታያል ፤ ይታወቃል ፤ ኹኖም በሽታው ሲለቀው እንጂ እንዴት እንደ ዳነ ራሱ ቅሉ አያውቀውም ።

### ፫/ የምሥጢረ ቀንዲል ጥቅም ፤

በምሥጢረ ቀንዲል የሥጋንና የነፍስን ድኅነት ፤ የኀጢአትን ስርየት ፤ የነፍስን መጽናናት እናገኛለን ። ምሥጢረ ቀንዲል ከጥምቀት በኋላ ለተሠራው ኀጢአት ማስተስረያ ሲሆን ከምሥጢረ ጥምቀትና ከምሥጢረ ንስሐ ጋር ኀጢአት በማስተስረይ ድኅነትን በመስጠት ፣ ጸጋን በማስገኘት ይተባበራል ።

## ክፍል ፫ ስብከት

ሁል ጊዜ ከቅዱስ ቊርባን የማይለየው ስብከት በካህኑ መነገር መሰበክም አለበት ፤ ይኸም ተግባር የማነጽ ተግባር በመሆኑ ምእመናኑን ለቅዳሴው ለቊርባኑ እንዲዘጋጁ ያደርጋቸዋልና ።

ምሥጢረ ቊርባን እንዲሁ ያለ ምክንያት አይፈጸምም ፤ በዓል ሁኖ ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ኑሮት ቅዱስ ቊርባን የተፈጸመ እንደሆነ ስብከቱ ከቅዳሴው አንደኛው ክፍል ስለሆነ በምንም መልክ መቋረጥ የለበትም ። የቀደሰው ካህን ወይም ረዳቱ የሆነው ማስተማር አለበት ፤ የጠባቂነቱን ኃላፊነት የሚወጣው በዚሁ በስብከት ሥራው ነውና ።

በስብከት ምእመናኑ በየጊዜው ይታነጻሉ ፤ ለምሥጢረ ቊርባን በቂ ሁነው ይቀርባሉ ፤ እንዲሁም በምሥጢረ ቊርባን አማካይነት ምእመናን ድኅነተ ነፍስን ያገኛሉ ፤ በዚህን ጊዜ ካህኑ ከሸክሙ አንደኛውና ሁለተኛው ቀለለለት ማለት ነው ።

ስብከት ለአመኑት ማጽናኛ መጠበቂያ ነው ፤ እንዲሁም ላላመኑት ደግሞ መሳቢያ ማቅረቢያ ጥሪ ነው ፤ ስለዚህ ስብከት በሁለት ዓይነት ይከፈላል ፤

ይኸውም ፥—፩/ የውስጥ ስብከት ፤ ፪. የውጭ ስብከት በማለት ነው።

፩. የውስጥ ስብከት ፣ በእምነት በትምህርት አንድ ሁነው በአንድ ጠባቂ ለሚመሩት ምእመናን የሚሰጠው ትምህርት የውስጥ ስብከት ይባላል ፤ ትምህርቱ እነርሱን ለማነጻት ፤ ለማጽናናት የሚሰጥ ይሆናልና ።

፪. የውጭ ስብከት ፤ ይኸም ከእምነት ውጭ ሁነው የሚገኙትን ሕዝቦች መጥራት ለክርስቲያናዊ እምነት ጥሪ የሚደረገው ነው ።



ይኸም ሁለት ዓይነት ትምህርት በአንድ አገር ውስጥም በሌላ በተለያየ አገርም ሊሆን ይችላል ።

በዚህ መልክ ካህኑ በሁለቱም ወገን የተለያየ ትምህርት በመስጠት ሁለቱንም ወገን እጅ ሊያደርግ ይችላል ፤ ይኸውም በተለያየ ቦታ በተለያየም አጋጣሚ እየተገኘ ያስተማረ እንደሆ ነው ።

ሁሉንም በአንድ ላይ አድርጊ አስተምራለሁ ያለ እንደሆነ «ዘኀሠሠ ፪ኤ ኢይረክብ ፩ደ» እንደተባለው ሁሉንም ያጣል ፤ ግን በተለያዩ ቦታዎች አጋጣሚዎች ሁሉንም በየቦታቸው ያስተማረ እንደሆነ ሁሉንም ሊያተርፍ ፣ ሁሉንም ሊያገኝ ይችላል ።

ቤተ ክርስቲያን ከመቋቋሙ ፤ ጸሎተ ቅዳሴውም ከመጀመሩ በፊት ስብከት ያስፈልጋል ፤ ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያኑን የሚሠራው ማነው? አስቀድሞ ምእመናንን ማነጽ፤የምሥጢራቱም ሁሉ ተካፋይ እንዲሆኑ ለማቅረብ አስቀድሞ በቂ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋልና ። ያልዘራ አያጭድም፤እንዲሁም ምእመናንን ለማትረፍ ፣ የቤተ ክርስቲያንን አባላት ለማብዛት፤የቅዱሳት ምሥጢራት ተሳታፊዎችንም ለማግኘት በየዕለቱ በየጊዜው ሰፊ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል ።

አንድ ገበሬ ወቅቱን ጠብቆ እንዲዘራ ፣ ተግቶና ነቅቶ አዝመራውን እንዲከባከብ የምእመናኑ ጠባቂ አበ ነፍስ ነቅቶ ተግቶ ማስተማር ተቀዳሚ ተግባሩ ይሆናል ።

ካህኑ የሰው ሁሉ ጠባቂ እንደመሆኑ ሕፃናትን ፣ ጉልማሳዎችን ፣ ሽማግሌዎችን ፣ በጾታም በኩል ወንዶችን ሴቶችን ሁሉንም በትክክል ለመጠበቅ ይችል ዘንድ ሁል ጊዜ መስበክ አለበት ። ስብከቱም ሁሉንም የሚመለከት አጠቃሎም የሚይዝ መሆን አለበት ፤ ይኸም ማለት ፣

፩ኛ/ የዕድሜን ደረጃ እየለዩ ከላይ እንደገለጥነው ማስተማር ፣
፪ኛ/ የጾታውንም ሁኔታ ለይተው የሚያስተምሩበትን ጊዜ ማወቅ፣
፫ኛ/ የዕውቀት ደረጃውን ለይቶ ዐውቆ ተመጣጣኝ የሆነ ትምህርት ማስተማር ፣

ይኸም ሁናቴ በየአጥቢያው ጊዜንና ቦታን ለይቶ የሚሠራበት መሆን አለበት ፤

ሕዝብ በተሰበሰበበት ቦታ የሆነ እንደሆነ ግን ሁሉንም እንዲያገኝ ለሁሉም እንዲያዳርስ አማካይ የሆነ ትምህርት መስጠት አለበት ፤ ያለ



www.ethiopianorthodox.org

ዚያ ሁሉም አፍረው ሊመለሱ ይችላሉ ፤ በዚህም ጊዜ ካህኑ ከዓላማው ውጭ ሆነ ማለት ነው ። ለእያንዳንዱ ምእመን የተለየ ጉብኝትና ጥበቃ ካህኑ ካደረገ የነዚህን ወገኖች ኑሮ ዕውቀት በጠቅላላም ሁኔታ ሊያውቅ ይችላል ። ካህኑ የሁሉም አባት እንደመሆኑ ሁሉም አቅንተው የሚመለከቱ ወደ እርሱ ነውና ፤ ርእሱ አእምሮውን አዘንብሎ ወደ እነርሱ መመልከት፤ ጩኸታቸውንም ማዳመጥ አለበት ። «ዘቦ ዕዝን ሰሚዓ ለይስማዕ» የሚያሰኘው እንደ ዕድሜው እንደ ዕውቀቱ እንደ ኑሮው ደረጃ ተስማሚ የሚሆነውን ትምህርት ከሰጡ በኋላ ነው ።

በጠቅላላ ስብከቱ ሰውን የሚያንጽ ሰውን የሚስብ ፣ ክርስቲያናዊ እምነትን የሚያጸና እንዲሆን ትልቅ ጥንቃቄ ያስፈልጋል ።
የንግግር ፈሊጥ የስብከት ዘዴ ስለሚያስፈልግ ይኽን በስብከት አቅድ የተሰጠውን ትምህርት መከታተል ያስፈልጋል ።

ምእመናኑን በስብከት ሥራ የማይጎበኝ ካህን ኃላፊነቱን የዘነጋ ከጠባቂነት ሥራው ውጭ የሆነ ነው ። ከቅዳሴው ክፍል አንደኛው አካል ስለሆነ ቅዳሴው መታጎል እንደ ሌለበት ሁሉ ስብከቱም ከቶ መታጎል የለበትም ።

አንድ ካህን ምእመናንን በትክክል የሚያገኛቸው በስብከት ሥራው ነው ። «የሾም ሰነፍ ፤ ባይለፈልፍ» እንደተባለው የካህንም ስንፍና ሳይሰበክ ፤ ሳይናገር ቢቀር ነውና፤ ከፍ አድርጎ ጩኾ አሰምቶ መስበክ አለበት ።

## ክፍል ፬ ለሕሙማንና ለሙታን የሚደረግ አገልግሎት

ሀ/ በሽተኛው ምሕረትን ከእግዚአብሔር የሚያገኝበትን ጸሎት ካህኑ በየጊዜው መጸለይ አለበት ። የካህኑ ጸሎት ድውዩን ይፈውሳል፤ ኃጢአተኛውን ያነጻልና ( ያዕቆ ፭ ፡ ፲፭) ። ካህኑ አምኖ የሃይማኖት ጸሎት ስለበሽተኛው ሲጸልይ በሽተኛው እግዚአብሔር ይቅርባይ እንደሆነ ምሕረትና ጸጋ ሁሉ ከእርሱ የሚገኝ መሆኑን አምኖ ከተቀበለ ድኅነተ ሥጋን ድኅነተ ነፍስን ያገኛል ፤ ክርስቶስም ሐዋርያትን ሲልክ ከአዘዛቸው ትእዛዛት ውስጥ አጋንንትን እንዲያስወጡ ፣ ደዌንና ሕማምንም ሁሉ እንዲፈውሱ ሥልጣን ሰጥቶ ነው (ማቴ ፲ ፡ ፩) ።

ቤተ ክርስቲያናችን ስለድውያን የሚደረግ ምልጃ ፣ ስእለት ፤ አስተብቍዖት አዘጋጅታለች፤ይኽን በየጊዜውና በየቦታው ካህኑ በትጋት መፈጸም በግድ አለበት ።



በሽተኛውም ሳይሰቀቅ በትዕግሥት ሕመሙን መከራውንም እንዲቀበል ማጽናናት ማረጋጋት የካህኑ ዋና ተግባር ነው ። የጻድቁን የኢዮብን መከራና ትዕግሥት ምሳሌ እያደረገ ማስረዳት ማጽናናት አለበት (ኢዮ ፩፡ ፲፫ — ፲፱) ።

በሽታ በኃጢአትም ምክንያት ይመጣል ፤ ጻድቁም በሰይጣን ፈታኝነት ሊታመም ይችላል። እንዲሁ በአጋጣሚ የተለያየ ፈተና የሚገጥመው ሰው ይገኛል ፤ ስለዚህ ሁሉ በትዕግሥት የፈጣሪያቸውን ይቅርታ ደጅ እንዲጠኑ እንጂ እንዳይመረሩ ተስፋም እንዳይቈርጡ ካህኑ ነቅቶ ተግቶ ማጽናናት ማረጋጋት አለበት ። ካህኑ የእግዚአብሔር እንደራሴ እንደመሆኑ በሥቃይ የተያዘው ሰው ካህኑን ሲመለከት በተስፋ ይጽናናል ፤ ይፈወሳልም ፤ ስለዚህ ካህኑ በጧትም በማታም ይኽን ተግባር አድርጎ መያዝና መፈጸም አለበት ። ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ድኅነት ከቶ ሊገኝ አይችልም ፤ ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህኑ ከምእመኑ መለየት የለበትም ።

ለ/ ሙታን ፣ ሙታንም የእግዚአብሔር ወገኖች ናቸው ፤ እግዚአብሔር አምላክ የሙታንም የሕያዋንም አምላክ ነውና ፤ ሕያዋንንም ሙታንንም ይገዛልና (ጸሎተ ሃይ ፡ ፩) ።

ሙታን ወደ እግዚአብሔር ቀረቡ እንጂ አልራቁም ፤ ዐረፉ እንጂ አልሞቱም ፤ ስለዚህ ወደ መቃብር በድናቸው ከመውረዱ በፊት ልዩ ክብር ይሰጣቸዋል ፤ የተለየ ጸሎትም ይደረግላቸዋል ፤ እንደቤተ ክርስቲያን በዓል ሁኖ የምእመኑ አማኝነት ሠራተኛነት ፣ ተጋዳይነት እየተነገረለት ፤ እንደአቸናፊነቱ እንደ ድል አድራጊነቱ የአበባ ጉንጉን ተደርጎለት በክብር ይሸኛልና ።

ቤተ ክርስቲያናችን ስለዚህ ፍትሐተ ጸሎት ፣ ወይም ጸሎተ ሙታን ብላ የወሰነችው ስላላት በትክክል መፈጸም አለበት ፤ ካህኑ ይኽን የፈጸመ እንደሆነ የጠባቂነቱን ኃላፊነት ተወጣ ፤ እውነተኛ የእግዚአብሔር ካህንነቱን ገለጠ ማለት ነው ።

## ክፍል ፭ የቤተ ክርስቲያን ዶግማ

ካህኑ ደህና አድርጎ ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረውን የራሱን ቤተ ክርስቲያን መሠረተ እምነት (ዶግማ) ማወቅ ለሌላውም ማሳወቅ አለበት ።



www.ethiopianorthodox.org

የቤተ ክርስቲያን ዶግማ በአጠቃላይ በ፮ ክፍል ይከፈላል ፤ ይኸውም

፩/ የእግዚአብሔርን ህልውና ማወቅና ማመን ፥ ይኸም ማለት እግዚአብሔር አምላክ የነበረ ያለ ፥ የሚኖር አምላክ እንደሆነ ሁሉ በእርሱ የሆን ያለ እርሱ አንድም የሆነ የሌለ አምላክ እንደሆነ ማመንና ማሳመን ነው ፤ይኸም እምነት በቅ/ መጽሐፍ እየተደገፈና በሥነ ፍጥረት አማካይነት የተረዳ እውነተኛ እምነት መሆኑን ማወቅና ማሳወቅ አለበት ። (ሮሜ ፥ ፩ ፥ ፳፩) ።

፪/ <u>እግዚአብሔር</u> በሦስትነት፤እግዚአብሔር በአንድነቱ በሦስትነቱ ጸንቶ ያለ አምላክ ስለሆነ ሦስትነቱ በአንድነቱ ሳይጠፋ በሦስትነቱም ርባኤን ሳያመጣ የሚኖር አምላክ መሆኑን ጠንቅቆ ማወቅና ማመን ሌላውንም በዚሁ ማሳመን የካህኑ ተግባር ነው ።

፫/ <u>ዓለም በጠቅላላ</u> ፤ ሰማይና ምድር በውስጣቸው የሚገኙ ሁሉ የሚታየውም የማይታየውም የራቀውም የቀረበውም ሁሉ በእግዚአብሔር ፈጣሪነት እንደተፈጠረ ማመንና ማሳመን ፥ ይኸም ለተቀደሰ ዓላማ እንጂ በከንቱ ለከንቱ ያልተፈጠረ መሆኑን ካህኑ ደኅና አድርጎ ማወቅ ማመን ሌላውንም ማሳመን አለበት ።

፬/ <u>ድኅነተ ዓለም</u> ፤ ዓለም ከተፈጠረ በኋላ በሰው በደል ምክንያት ለጥፋት ተዳርጎ መኖሩ የታወቀ ነው ፤ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ምሕረቱ ብዙ ነውና ስለታረቀው ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው አንድያ ልጁን እንደላከ ፥ ግልጥ የሆነ ክርስቲያናዊ ትምህርት ነው ። የእግዚአብሔር ፍጹም ፍቅር የተገለጠው በዚህ ዓለም ድኅነት ነው። የዘለዓለም ተስፋቸው ከዚሁ ጋር የተያያዘ ስለሆነ ካህኑ ይኸን ማወቅና ማሳወቅ አለበት ።

፭/ <u>ምሥጢረ ተዋሕዶ</u> ፤ ክርስቶስ ሰው የሆነ አምላክ ስለሆነ አምላክ ወሰብእነቱ በተዋሕዶ መሆኑን ማመን ተገቢ ነው ፤ ይኸውም መለኮት ከሥጋ አካልና ከሥጋ ባሕርይ ጋር ፥ ሥጋም ከመለኮት አካልና ባሕርይ ጋር ተዋሕዶ አምላክ ወሰብእ መባሉ ረቂቅ ምሥጢር እውነተኛም ሃይማኖት መሆኑን ፥ ቤተ ክርስቲያናችንም በዚሁ ምክንያት የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እየተባለች የምትጠራ መሆኗን ካህኑ መረዳትና ማስረዳት አለበት ፥ ይኸንንም ኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ ሃይማኖት ካህኑ መጠበቅ ማስጠበቅም ግዴታው ነው ።

፮/ <u>ምሥጢረ</u> ምጽአት ፥ ክርስቶስ ለሁለተኛ ጊዜ ወደዚህ ዓለም እንደሚመጣ፥ይኸንም ዓለም አሳልፎ ሌላ አዲስ ዓለም እንደሚተካ ኦርቶዶክሳዊ እምነታችን ነው ። ስለዚህ ካህኑ ይኸን የመጨረሻ የማጠቃለያ እምነት ከፍተኛ ግምት ሰጥቶ ሊጠብቀው ሊያስጠብቀው ይገባዋል።

ከተናገርናቸው አምስቱ የዶክትሪን ትምህርቶች የተገለጡና የተፈጸሙ ናቸው ፤ የመጨረሻው ስድስተኛው ትምህርት ግን ገና በተስፋ የምንጠብቀው ስለሆነ ካህኑ በሚያጓጓ ምእመናን እንዲጠብቁ ተስፋም አድርገው ደጅ እንዲጠኑ ማስተማር አለበት ።

በዚህ ዓለም ሳለን ስለሠራነው ሁሉ ምስጋና የምናገኝበት ፤ ዋጋ የምንከፈልበት በሁለተኛ ጊዜ መምጣቱ ስለሆነ ይኸን አምኖ ተስፋም አድርጎ መጠበቅ ተገቢ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

ደብረ ሊባኖስ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን ቤተ መጻሕፍት

# የካህናት ተልእኮ

## ማውጫ

ገጽ

መቅድም ፡ . . . . . . . ፶፭

## ክፍል ፩ እውነተኛው ካህን

፩/ የክህነት ትርጉም ፶፯
፪/ የክህነት አጀማመር ፶፰
፫/ የብሉይ ኪዳን ካህን ፶፱
፬/ የሐዲስ ኪዳን ካህን ፷፩
፭/ ለክህነት አገልግሎት መጠራት ፷፫
፮/ ክህነት ቅዱስ አገልግሎት መሆኑ ፷፯
፯/ የካህኑ መለያ ምልክት ፷፰

## ክፍል ፪ ሥርዐተ አምልኮ

፩/ ሥርዓተ አምልኮን መፈጸም ፸፯
ሀ/ ለጸሎት ጽሙድ መሆን
ለ/ ጸሎተ ቅዳሴን በየጊዜው መፈጸም
ሐ/ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን መፈጸም ፸፰

## ክፍል ፫ የማያቋርጥ ስብከት መስበክ ፹

ሀ/ የዕድሜን ደረጃ በመለየት መስበክ
ለ/ ልዩ ልዩ አጋጣሚዎችን በመጠበቅ መስበክ

## ክፍል ፬ ለሕሙማንና ለሙታን የሚደረግ አገልግሎት ፹፪

## ክፍል ፭ ትምህርተ ሃይማኖትን ማስተማር ፹፫

ደብረ ሊባኖስ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን ቤተ መጻሕፍት

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org